# ምዕራፍ ዐሥር

# ኃጢአታችንን መናዘዝ

*«ኸደልህን አምነህ ንስሐ ብትገባ እግዚአብሔር ይረሳልሃል። በድለህ እንዳልበደለ ብትሆን ግን አስቦ ይቀጣሃል።»*

ከወዳጃችን ጋር ብንጣላና ከእርሱ የምንፈልገው ነገር ቢገጥመን ቅድሚያ መስጠት ያለብን ለይቅርታው ነው ወይስ ለፍላጎታችን? ብንል ከኅሊና አንፃር እንኳ ብንመለከተው የሰውዬው የሆነውን ከመፈለጋችን በፊት ለውዬውን ማትረፍ አለብን። ለውዬውን ካልፈለግን የሰውዬው የሆነውን ብንፈልግም አናገኘውም። ይህንን ለማስተዋል መንፈሳዊነት ብቻ ሳይሆን ኅሊናም በቂ ነው። ከሰው ጋር ላለን ግንኙነት ይቅርታ ቀዳሚ ነገር ነው። ይቅርታ ቃሉ ይቅር ማለት ሲሆን ትርፉ ግን ከሚቀረው ቂምና በቀል በላይ ነው።

ለሰው የምንጠነቀቀውን ያህል ለእግዚአብሔር አለመጠንቀቃችን ያሳዝናል። ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልተን ንስሐ ከመግባት ፍላጎታችንን በጸሎት መደርደር እንመርጣለን። ለሰው የምናደርገውን ለእግዚአብሔር ማድረግ አለመቻል ትልቅ ምስኪንነት ነው። ጸጋውን እንጂ ባለ ጸጋውን አንፈልግም የምንል ይመስላል። «ኸረ እንዴት እንደዚህ ይባላል? እግዚአብሔር ይቅር ይበልህ እንዴት እግዚአብሔርን አልፈልግም ይባላል?» እንል ይሆናል። ነገር ግን እንዲህ ባንልም በተግባር እናደርገዋለን። ትልቅ ንግግር ተግባር ነውና። ስለዚህ ይቅርታ መቅደም አለበት። እርሱ ይቅር ካለን ደግሞ የሚቀርብን ጸጋ የለም። ለዚህ ነው ከጸሎት ክፍሎች አንዱ ኃጢአትን መናዘዝ የሆነው።

ንስሐ ማለት ጥልቅ ትርጉሙ አሳብን መቀየር መንገድን መለወጥ ማለት ነው። ንስሐ አሳብን መቀየር መንገድን መለወጥ ከሆነ ሦስቱን የነፍስ እውነቶች ይነካል ማለት ነው። ሦስቱ የነፍስ እውነቶች የምንላቸው አእምሮ፣ ስሜትና ፈቃድ ናቸው። አእምሮ የቃሉ ትርጉም እውቀት ማለት ሲሆን ማንኛውንም ነገር የምንገነዘብበት



ክፍል ነው። ስሜት ደግሞ በሚያስደስት ነገር የምንደሰትበት በሚያሳዝን ነገር የምናዝንበት ክፍል ነው። ፈቃድ የሚባለው ውሳኔና ምርጫ የምናደርግበት ክፍል ነው።

ሰው አስቀድሞ ኃጢአቱን በአእምሮ ይገነዘባል። ቃሉን ሲሰማ፣ መንፈስ ቅዱስ ሲወቅሰው ኃጢአት መሥራቱን ይረዳል። በጥፋቱ ትክክል ይቆማል። ሕመም እንዲሰማው ካልፈቀደ ምክንያትን በመደርደር መጽናናት ይፈልጋል። ይህ ራስን ይቅር የማለት ሥርዓት ነው። ግን እስረኛን ምሕረትና እውነት ይለቀዋል እንጂ ራሱን አይለቅም። ኃጢአቱን በአእምሮ የተገነዘበው ወገን ራሱን በዚሁ ማቆም ስለሚፈልግ «መሥራቱን ሠርቻለሁ ግን ሥርዓቱ፣ ወጣትነቱ፣ ፓለቲካው፣ ... አስገድዶኝ ነው የበደልኩት» ይላል። ይህ ወገን እየተናዘዘ ያለው ኃጢአቱን ሳይሆን ምክንያቱን ነው። እውነተኛ ንስሐ ግን ለጥፋታችን ሙሉ በሙሉ ኃላፊነቱን እንድንወስድ ያደርገናል። ኃጢአትን መገንዘብ ቀላል ባይሆንም ኃጢአትን መገንዘብ ብቻውን ግን ንስሐ አይደለም።

ሰው ኃጢአቱን በአእምሮ ከተገነዘበ በኋላ ቀጥሎ በስሜቱ ይነካል። ስለዚህ ያዝናል፣ ያለቅሳል፣ ይፀፀታል። በደለኛነቱን ይናገራል። ሲወቅሱትም «ልክ ነው የምረባ ሰው አይደለሁም» ይላል። ኑዛዜው ግን ከስሜት መነካት ስለማያልፍ ተመልሶ በኃጢአት ውስጥ ይገኛል። ራሱን እየገዘተ፣ ቀጠሮ እየሰጠ፣ እየፎከረ ይኖራል። ግን ቆይቶ ሁሉንም ይረሳል። ይህ ሰው ጭቃ ውስጥ ተቀምጦ እጠቡኝ የሚል ይመስላል። በስሜት መነካት ማዘንና ማልቀስ ቀላል ባይሆንም በስሜት መነካት ብቻውን ንስሐ አይደለም። ንስሐ በስሜት ከመነካት ያልፋል።

በአእምሮው ኃጢአቱን የተገነዘበው፣ በስሜቱ የተነካው ሰው ያንን ስህተት ላለ መድገም ውሳኔ ሲያደርግ ንስሐው የተሟላ ይሆናል። በፈቃድ ክፍል ውስጥ እግዚአብሔርን መርጦ ዓለምን ይክዳል። ጥልቅ ውሳኔ አድርጎ ኃጢአትን ይጥላል። ንስሐ ማለት አሳብን መለወጥ መንገድን መቀየር ማለት ነው ስንል ውሳኔ ነው ማለታችን ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በኃጢአታቸው ንስሐ የገቡ ነገር ግን ንስሐቸው እውነተኛነት ስላልነበረው ተቀባይነት ያላገኙ ሰዎች አሉ። የመጀመሪያው አዳም ነው። የሰው ዘር መነሻ የነበረው አዳም እግዚአብሔር ለንስሐ ሲጋብዘው *«በገነት ድምፅህን ሰማሁ፤ ዕራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ፤ ተሸሸግሁም»* (ዘፍ. 3፥10) ብሏል።

አዳም ግን ሰጥፋቱ ምክንያት ያደረገው ሔዋንን ነው:: ለጥፋቱ ሙሉ በሙሉ ኃላፊነቱን ራሱ አልወሰደም:: የአዳም አሳብ ሔዋን ባትፈጠርብኝ ኖሮ እኔ አልሳሳትም የሚል ነው:: ስለዚህ አዳም ራሱን ነጻ አድርጎ ሔዋንን የፈጠረበትን እግዚአብሔርን ጥፋተኛ አደረገ:: የተናዘዘው ኃጢአቱን ሳይሆን ምክንያቱን በመሆኑ ንስሐው ተቀባይነት አላገኘም:: እውነተኛ ንስሐ ራስን ሙሉ በሙሉ ተጠያቂ ማድረግ ነው::

ንስሐው ተገቢ ያልነበረውና ሌላው ሰው ቃየን ነው:: ቃየን ወንድሙን ከገደለ በኋላ ፊቱ ጠቍሯል፣ አዝኗል:: ያዘነው ግን ወንድሜን በደልኩ ብሎ ሳይሆን ለኛሜን ምን ወሰደው ብሎ ነው (ዘፍ. 4፥1-15):: ቃየን ራሱን ኃጢአትን አልጠላውም:: ውጤቱ ግን አሳዘነው:: እውነተኛ ንስሐ ግን ኃጢአትን መጥላትና በኃጢአት መመረር ነው:: ዛሬ ሰዎች ኤድስን እንጂ ዝሙትን እንደማይፈሩት ማለት ነው:: ሰኃጢአት ማልቀስና ለቅጣት ማልቀስ ልዩነት አለው::

ንስሐው ተቀባይነት ያላገኘው ሦስተኛው ሰው ኤሳው ነው (ዕብ. 12፥16-17):: ኤሳው ብኵርናውን ናቀ:: በኋላ ባጣው ጊዜ አዘነ አለቀሰ:: ግን አላገኘውም:: ኤሳው የእግዚአብሔርን በረከት አጣሁ ብሎ ስለ ጥቅሙ አለቀሰ እንጂ ራሱን እግዚአብሔርን ስለ መበደሉ አላለቀሰም:: እውነተኛ ንስሐ ግን «አባቴን እግዚአብሔርን አሳዝኜዋለሁ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ጦር እንደ ወረወረው ሰው ሆኛለሁ፣ በቁስሉ ውስጥ ጠጠር ሞልቻለሁ:: አይሁድ አንድ ጊዜ ሰቀሉት እኔ ግን ብዙ ጊዜ ሰቀልኩት» ብሎ ማዘንና ማልቀስ ነው::

ንስሐው ተቀባይነት ያጣው አራተኛው ሰው ፈርዖን ነው:: ፈርዖን ብዙ ጊዜ ንስሐ የገባ መስሏል (ዘፀ. 8፥8):: ፈርዖን ንስሐ የገባው ቀጣዩን መዓት በመፍራት እንጂ ወደ ዙፋን ያወጣኝን ጌታ እንዴት ደፈርኩት? ብሎ አይደለም:: ቅጣትን ስለ መፍራት የሚደረግ ንስሐ እውነተኛ አይደለም:: አንድ ሰው ሲናገር:- «ፖሊስን ስለ ፈራ የማይሰርቅ አልሰረቀም ማለት አይደለም» ብሏል::

ንስሐው ተቀባይነት ያጣበት ሌላው ሰው ይሁዳ ነው:: ይሁዳ ተጸጽቷል ግን ፀፀቱ ምሕረት አላስገኘለትም (ማቴ. 27፥3-5):: የተመኘት ዓሰም ከኢየሱስ በላይ ልታረካው ስላልቻለች አለቀሰ:: እውነተኛ ንስሐ ግን የጌታን ፍቅር እያሰቡ ማዘንና ማልቀስ ነው::



እግዚአብሔር በየዘመናቱ የሰው ልጆችን ወደ ንስሐ ጠርቷል:: ሰዎችን ወደ ንስሐ የጠራበት ቃልም ማራኪና አስደሳች ፍቅር የተሞላ ነው:: ከዚያ ውስጥ አንዱ በነቢዩ በሕዝቅኤል የተላለፈው የንስሐ ጥሪ ነው:- *«የእስራኤል ቤት ሆይ፥ ስለዚህ እንደ መንገዱ በየሰው ሁሉ እፈርድባችኋለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር! ንስሐ ግቡ ኃጢአትም ዕንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ:: የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ለእናንተ አድርጉ፤ የእስራኤል ቤት ሆይ፥ ስለምን ትሞታላችሁ? የምዋቹን ሞት አልፈቅድምና ይላል ጌታ እግዚአብሔር! ስለዚህ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ»* (ሕዝ. 18፥30-32)::

ኃጢአተኛ ነኝ ማረኝ ማለት በራስ ላይ መፍረድ ነው:: ስህተቱን ያመነ ምስክር አይጠራበትም:: በተማረከ ላይ ጀግንነት አያሳዩም:: በራሱ በፈረደ ላይ ማንም አይፈርድበትም:: አንድ የጥንት የቤተ ክርስቲያን አባት:- «በደልህን አምነህ ንስሐ ብትገባ እግዚአብሔር ይረሳልሃል:: በድለህ እንዳልበደለ ብትሆን ግን አስቦ ይቀጣሃል» ብሏል:: እንደ ሥራችን እንዳይፈረድብን ያለ ሥራችን ምሕረትን የምንቀበልበት መንገድ ንስሐ ነው::

ለንስሐ የሚጠራን እግዚአብሔር ነው:: መዓቱም ምሕረቱም በእጁ ሲሆን ሊምረን ይፈልገናል:: ኃጢአት እንቅፋት ነው:: እንቅፋት ያቆስላል፣ ያሰናክላል፣ ከመንገድ ያስቀራል:: ኃጢአትም ሥጋን፣ ነፍስንና መንፈስን የሚያቆስል እንቅፋት ነው:: በኃጢአት ምክንያት በበሽታ የተለከፉ፣ ኢኮኖሚያቸው የተናጋ፣ ትዳራቸው የፈረሰ፣ ልጆቻቸው በጎዳና የወደቁ፣ በወንኒ የተጣሉ ብዙዎች ናቸው:: ኃጢአት ሥጋንም ያቆስላል:: በኃጢአት ምክንያት ሰላማቸው የደፈረሰባቸው፣ በጸጸት የሚሰቃዩ አሉ:: ኃጢአት ነፍስን ያቆስላል:: በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይተው የሚኖሩ ብዙዎች ናቸው:: ኃጢአት መንፈስን ያቆስላል::

ኃጢአት ከክርስትና፣ ከራእይ ጎዳና ሊያሰናክል የሚታገል ነው:: ብዙዎችንም በጅምር አስቀርቷቸዋል:: ከኃጢአት ትልቁ ተስፋ መቍረጥ ነው:: ከዚህ በኋላ ዋጋ የለኝም በሚል ስሜት ብዙዎች በመንገድ ቀርተዋል:: ኃጢአት እንቅፋት የሚሆነው ላለፈው ብቻ አይደለም ለሚመጣውም ነው:: ኃጢአት በንስሐ እስካልተወገደ ድጋሚ ይጥላል:: ስለዚህ በንስሐ መወገድ አለበት:: «ጠዋት ወደ ሥራ ስትሄድ የመታህ ድንጋይ ማታ ስትመለስ ቢመታህ፣ ድንጋዩ ሳይሆን ድንጋይ አንተ ነህ ድንጋዩ» የሚባለው አባባል ይህን አሳብ

ያብራራልናል:: «ተመለሱ» የሚለው ቃል አስደናቂ ነው:: ወደ ገደል የሚንዝን ሰው መንገድህን አትጨርሰው የሚል ነው:: በጎ ሥራ እንጂ ኃጢአት ሲጨርሱት መልካም አይደለምና:: ክፉ አሳብን በጅምሩ፣ ክፉ ንግግርን በጅምሩ፣ ክፉ ተግባርን በጅምሩ ማቆም እንጂ መጨረስ አይገባም:: ሌላው አስደናቂ ቃል *«ንስሐ ግቡ»* የሚለው ቃል ነው:: ንስሐ ግቡ የሚለው ቃል ቀጥተኛ ትርጉሙ ኃጢአታችሁን አምናችሁ ተናዘዙ ማለት ነው:: ግቡ የሚለው ቃል ግን ተሰብሰቡ፣ መሽጉ ማለት ነው:: በጦር ሜዳ ከምሽጉ ወጥቶ የሚንጎማለል ወታደር ሲወድቅ ይችላል:: ኃጢአትም ድንገት ይጥላልና በንስሐ ወደ ምሕረት አጥር ግቡ ማለት ነው::

ኃጢአት ሸክም ነው:: ስለዚህ ያጎብጣል፣ ያንገዳግዳል፣ ያደክማል:: ቀና ብለን ለማየት የሚረዳን ወንድነት ወይም ድርቅና አይደለም:: ይህን ነጻነት የሚሰጠን የጽድቅ አኗኗር ነው:: ሸክምን እንደ ተሸከሙ ማረፍ አይቻልም:: መጀመሪያ ሸክምን መጣል ቀጥሎ ማረፍ ይገባል:: እንዲሁም ምንም ደልዳላ ወንበር ብንዘረጋ፣ ትልቅ ቤት ብናንጣልል፣ የውሃ ፍራሽ ብንገዛ የኃጢአት ሸክም ካልወረደ ዕረፍት የለንም:: ማንኛውም ሸክም አይጥምም:: ከዚህ ሁሉ በላይ የቆሻሻ ሸክም ትንሹም ከባድ ነው:: እንዲሁም ኃጢአት የቆሻሻ ሸክም ነውና ካልወረደ ነጻነት አይሰጥም:: *«የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ»* (ሕዝ. 18፥31)::

ንስሐ ከሚያጎናጽፈን ጸጋ አንዱ አዲስ አስተሳሰብና አዲስ ራእይ ነው:: ኃጢአት መንፈስን ያዝጋል:: የዛገ መንፈስ ተስፋ አይታየውም:: ስለዚህ ንስሐ አዲስ ልብና አዲስ መንፈስን ያጎናጽፋል:: *«አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ለእናንተ አድርጉ!»* (ሕዝ. 18፥31)::

ኃጢአት ይገድላል:: የኃጢአት ኑሮ የመቃብር ታሪክ ነው:: የበሽታ መጨረሻው ሞት ነው:: የኃጢአትም ፍጻሜው ሞት ነው:: ማንም በሽተኛ መዳንን ብቻ ነው የሚናፍቀው:: ግድ ካልሆነበት ሞትን አይፈልግም:: የመዳኑ ዕጣ ያለው በሐኪሙ እጅ ቢሆን እንዴት ይማፀነው ይሆን? ግን አይደለም:: የመዳናችን ዕጣ ግን ያለው በእግዚአብሔር እጅ ነው:: እርሱ ደግሞ የምዋቹን ሞት አይፈቅድም:: *«ተመለሱና በሕይወት ኑሩ»* እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጠው ሁለተኛ ዕድል፣ የሕይወት አማራጭ ንስሐ ነው:: እግዚአብሔር በማንም ላይ ሲኦልን አይፈርድም:: የገዛ ምርጫችን ግን ይፈርድብናል:: ሰው ራሱን በሲኦል ቢያገኘው ሙሉ በሙሉ ተጠያቂው ራሱ ነው:: እንግዲህ የንስሐ ዕድልም ያለን በሕይወት ሳለን ነው:: ከሞትን በኋላ ዕድሉ የለንም:: ከሞትን በኋላ በጎ የመሥራትም



ሆነ ክፉ የመሥራት ዕድል የለም:: ከሞት በኋላ ያለው በምድር ላይ የመረጥነው ዋጋ ነው:: እግዚአብሔር የንስሐ ዕድልን ባያዘጋጅ ኖሮ በመጀመሪያ የምንፈራው ዐቃቤ ሕግን ሳይሆን የገዛ ሕሊናችንን ነበር:: ሕሊና የእኛ አይደለም:: ሕሊናን የእኛ ለማድረግ ብዙ እንጥራለን:: ሕሊና ግን የእግዚአብሔር ወኪል ነው:: ስለዚህ የፀፀት ስስ መርፌዎች መንፈሳችንን ሲወጉት የመርፌው ማርገፊያ ንስሐ ነው:: ንስሐ ባይኖር አንኖርም ነበር:: ታጥቦ ጭቃዎች፣ የተፋነውን የምንልስ ብላሽ ሰዎች ነን:: አቅም የለኝም የምንለው ለጽድቅ እንጂ ለኃጢአት አቅም አጥተን አናውቅም:: የዘወትር በደለኞች ነን:: ቶሎ የምንቆሽሽ ነን:: የእግዚአብሔርን ምሕረት በንስሐ ባናገኝ ሰላምና ደስታን ተርበን በቀረን ነበር:: ታዲያ እንዲህ እንደ ውሃ የሚያስፈልገንን ንስሐ የምንፈጽምበት መንገዱ ጸሎት መሆኑ ይገርማል:: ለዚህ ነው የጸሎታችን አንዱ ክፍል ንስሐ የሆነው:: በዳዊት መዝሙር ውስጥ የምናገኘው አንዱ ጸሎት «ማረኝ፣ ይቅር በለኝ» የሚል ነው:: ከዚህ ውስጥ መዝሙር 50 የታወቀው የንስሐ ጸሎት ነው::

# ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

## የምንለምነውን ማወቅ

*«ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቷል»* (ሆሴዕ 4፥6)::

ሕጻን ልጅ እሳት ካልያዝኩ ብሎ ያለቅሳል:: ወላጆቹ ግን ለልቅሶው ሳያዝኑ ይከለክሉታል:: ባለ ማወቁ የሚለምነው ሞትን ነውና:: እሳት የማያቃጥል ነው፣ ከዚያ ባሻገር ግን እሳት በጣም ውብ ነው:: ያደጉት ሰዎች የእሳቱ ማቃጠል እንጂ ውበቱ አይታያቸውም:: ሕፃኑ ደግሞ ማቃጠሉን አያውቅም፣ ስለዚህ በውበቱ እየተማረከ ከተቀመጠበት ስፍራ ወደ እሳቱ ይንሸራተታል:: ወላጆቹም ሲያርቁበት ይበሳጫል፣ ሲከለክሉት ያለቅሳል:: የሕፃኑ ልቅሶ ትክክለኛነቱንና ለራሱ መምረጥ መቻሉን አያሳይም:: ወላጆቹም ስለከለከሉት ክፉዎችና የሕጻናትን መብት የሚጋፉ አያሰኛቸውም:: ሕፃናት ግን በጣም ችክ ሲሉ ወላጆች ክፍሙ ሳይሆን ከወላፈኑ ያስነኳቸዋል:: ከዚያ በኋላ ሕፃናት እሳትን ይፈራሉ:: በዓይን ብቻ ከተመዘነ እሳት ውብ ነው:: በጥልቀት ሲመረምሩት ግን እሳት ያቃጥላል:: የእሳትን ማቃጠል ያወቅነው ደርሶብን ወይም ሞክረነው ሳይሆን በማደግ አውቀት ተረድተነዋል::

እንዲሁም እንደ እሳቱ በዓይናችን ፊት ብዙ ነገሮች ውብ ሆነው ሲታዩን ካልያዝናቸው ብለን እናለቅሳለን:: ምንም እንኳ እግዚአብሔር ሩኅሩኅ ቢሆንም እሳት ለሚለምኑት ልጆቹ ግን እሳት አይሰጥም:: እሳትን የከለከሉ ወላጆች ንፉጐችና ክፉዎች አይደሉም:: ከልጆቻቸው ይልቅ ለልጆቻቸው የሚያስቡ ናቸው እንጂ:: እግዚአብሔርም ከእኛ ይልቅ ለእኛ ቸር ሆኖ የሚጎዳንን ነገር ይከለክለናል:: የእግዚአብሔር የፍቅሩ ጥልቀት ካልገባን በማየት ብቻ ለራሳችን የምናጨው ነገር የሚያቃጥለን እሳት ነው:: ወላጆች ልጆች ሲያስቸግሩ እሳቱን እንዲነኩ ያደርጓቸዋል:: እግዚአብሔርም በጣም ችክ ስንል የምንፈልገውን ይሰጠናል:: ግን እሳት ነው:: የእስራኤል ልጆች የጐመጁት *ሥጋ* በአፋቸው ውስጥ ሲገባ ሞት ሆነባቸው:: *ሥጋ* አምሮታቸው ነበር ነገር ግን እግዚአብሔር ያውላችሁ ብሎ የሰጣቸው ስለ ነበር ሞት ሆነባቸው (*መዝ*.77/78/፥29-31/)::



እግዚአብሔር በደስታ ሲሰጠን እንጂ ያውላችሁ ብሎ ሲሰጠን መልካም አይደለም:: እግዚአብሔር ልዩ አባታችን መሆኑን ካላወቅን በከለከለን ነገር ውስጥ ፍቅሩን ማየት ያቅተናል::

በርግጥ አስተውለን ካየነው ለምነን ከተቀበልነው ሳንለምን የተቀበልነው ይበዛል:: የዛሬ የፀሐይ ብርሃን፣ የምንተነፍሰው አየር በጸሎት ያገኘነው አይደለም:: ስለዚህ የሚበልጠውን ነገር ያለ ልመና ካገኘን ልመናዬ አልተመለሰም ብለን በእግዚአብሔር ማኩረፍ ሞኝነት ነው:: እግዚአብሔር የሚከለክለን ለምንድነው?

1. የምንለምነው ነገር አሁን ስለማይጠቅመን፣
2. የምንለምነው ነገር መቼም ስለማይጠቅመን፣
3. በረከቱን ለመቀበል አሁን ብቁ ስላልሆንን ፣
4. ጸጋውን ሳይሆን ባለ ጸጋውን ማየት እንድንችል፣
5. የምንቀበለውን ነገር አክብረን እንድንይዝ ነው::

አባቱ የመቶ ብር ኖት ይዞ የሚያየው ልጅ ካልሰጠኸኝ ብሎ ሲያስቅስ አባቱ ይከለክለዋል:: አባቱ የሚከለክለው መቶ ብሩ ስለማይጠቅም አይደለም:: ለልጁ ግን አሁን ስለማይጠቅመው ነው:: በመከልከል ውስጥ የሚታየው የስጦታው አለመጥቀም ብቻ ሳይሆን ሰውዬው ለአጠቃቀም ብቁ አለመሆኑም ይታያል::

ደቀ መዛሙርቱ በልባቸው ውስጥ የሹመት ፍቅርና በአፋቸው ደግሞ የሹመት ልመና ነበር:: ደቀ መዛሙርቱ ያገኙትን ተሿሚው የሚበሉ፣ ነጻነት ተርፏቸው በየመንገዱና በየዱሩ የሚያድሩ፣ ዘበኛ የማይፈልጉ ሌባ እንኳ አዝኖ የሚመጸውታቸው ነበሩ:: እነዚህ ደቀ መዛሙርት ሰሰው ባይተርፉም ለራሳቸው የሚበቃ ኑሮ ነበራቸው:: እንቅልፍ የሚነሣ ጉዳይም የለባቸውም:: በሐሙስ ምሽት እንኳ ተኝተው ነበር:: ጌታም በተእምራት እየመገበና እየፈወሰ አብሮአቸው ይኖር ነበር:: ነገር ግን ሹመትን ተመኙ፣ ሹመትን ለመኑ:: ሹመትን ካገኙ የሚበሉትን ምግብ እንኳ ይጠራጠራሉ:: ነጻነት የሌላቸው እንቅልፍ የተነፈጉ ይሆናሉ:: ራሳቸው በፍርሃት ደክመው ዘብ ያደክማሉ:: ትንሿ ስህተታቸው እየጎላች ቡና መጠጫ ይሆናሉ:: ደቀ መዛሙርቱ ግን ከሰላማዊ ኑሮ ሁከትን፣ ከነጻነት የደለበ ባሪያ መሆንን መረጡ:: ስለዚህ ለራሳቸው የመጨረሻ ደግ ሆነው የመረጡት ሹመት ሺሞት ነበር:: ሰው ለራሱ መምረጥ አይችልም::

የታላቅነት ኑሮ፣ የፕሮቶኮል ዓለም እንደሚያደክም ደቀ መዛሙርቱ አልተረዱም:: ከደቀ መዛሙርቱ ኃይለኞች የነበሩት

ያዕቆብና ዮሐንስ እናታቸውን አስተባብረው ለልመና መጡ:: እነርሱም ሆኑ ማንኛውም ደቀ መዝሙር ያሰብ የነበረው ኢየሱስ ክርስቶስ የጦር ሰዎችን አሰባስቦ ሮማውያንን ድል ከነሣ በኋላ መንግሥቱን በኢየሩሳሌም መሥርቶ ወልደ ዳዊት ተብሎ ነግሦ እኛ የእርሱ የቅርብ ባለሟሎች እንሆናለን ብሎ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ከምድራዊ ገዢ ከሥጋ እስራት ነጻ ሊያወጣቸው ሳይሆን ከነፍስ ባርነት ሊያድናቸው ነበር የመጣው:: ይህን አስተሳሰባቸውን ይዘው ያዕቆብና ዮሐንስ እናታችን ሆይ ልመናችንና ጥያቄአችን ከእኛ ይልቅ ባንቺ ክብደት ያገኛልና ለምኚልን:: ካለመናገር ደጃዝሜችነት ይቀራል አሏት:: እናት ጳጳስ ቢነግራት እንኳ አትሰማም ልጇ ከነገራት ግን ትሰማለችና በልጅ ምክር ልጅ ሆና አደባባይ ወጣች:: እየወደቀችና እየተነሣች ወደ ጌታ መጣች:: ጌታም «ምን ትፈልጊያለሽ?» አላት:: እርስዋም:- እነዚህ ሁለቱ ልጆቼ አንዱ በቀኝህ አንዱም በግራህ በመንግሥትህ እንዲቀመጡ እዘዝ አለችው:: ኢየሱስ ግን *«የምትለምኑትን አታውቁም»* አላት (ማቴ. 20፥20-22)::

የጌታችን ክብሩና ዙፋኑ የቀራንዮ መስቀል ነው:: ዙፋን ጥሎ የመጣ፣ የሰንፔር ዙፋን ያለው እርሱ የእንጨት ዙፋን የሚጨስ የሚያቃጥል በመጨረሻ የሚቃጠል ዙፋንን እንዴት ይሻል? እርሱ ሰው ባለበት ዘመን ሳይሆን ሰው በሌለበት ዘመን ከዘላለም የነገሠ ነው:: ለእርሱ ድንቅ ነገር ክብር አይደለም:: የሚደንቀው ያለ ባሕርዩ ወራዳ ሥጋ ለብሶ መዋረዱ ነው:: ሰው ለራሱም ለጌታውም ልክ አያውቅም:: የሚሰፋው ቀሚስ ሁልጊዜም ጠባብ ነው:: ጌታ በኢየሩሳሌም የሚነግሠው በመስቀል ላይ ነው::

ይህች ሴት ለልጆችዋ የለመነችው በግርማዊ መንግሥትህ በተቀመጥህ ጊዜ አንዱን ልጄን ደጃዝማች አንዱን ልጄን ፊታውራሪ አድርገህ በቀኝ በግራህ አስቀምጥልኝ ብላ ነው:: ልመናዋ ግን እንዳሰበችው ሹመት ሳይሆን ሞት ነበር:: ልመናዋ በመልሱ ቋንቋ ስንሰማው «በቀራንዮ በተሰቀልህ ጊዜ አንዱን ልጄን እንደ ቀኙ ሽፍታ፣ ሁለተኛውን ልጄን እንደ ግራው ሽፍታ ስቀልልኝ» የሚል ነበር:: ለዚህ ነው ጌታ:- *«የምትለምኑትን አታውቁም»* በማለት የገሰፃቸው:: ሰው:-

- የሚለምነውን አያውቅም (ማቴ. 20፥22)::
- የሚሠራውን አያውቅም (ሉቃ. 23፥34)::
- የክብርን ጌታ አያውቅም (1ቆሮ. 2፥8)::

ለዚህ ነው በነቢዩ በሆሴዕ *«ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቷል»* (4፥6) በማለት እግዚአብሔር የልቡን ሀዘን የገለጠው::



የሚለምኑትን አለማወቅ ሞትን ያስለምናል:: የሚሠሩትን አለማወቅ በአደባባይ ያራቁታል:: የክብርን ጌታ አለማወቅ የሚሰገድለትን ልስቀለው ያሰኛል:: ሰይጣን የሰውን ልጅ የሚገዛው ባለ ማወቅ መጋረጃ ሸፍኖ ነው (2ቆሮ. 4፥4 )::

ጌታ የእነ ዮሐንስ እናት የለመነችውን በመከልከል ጸሎቷን ሰማ:: የለመነችው ነገር እንኳን ለልጅ ለባዕድም የማይለመን ነበር:: ባለ ማወቋ ግን የመጨረሻውን ጥቅም ለመንኩ ብላ የመጨረሻውን ጉዳት ለመነች:: ጌታ ልመናዋን ሰምቷት ቢሆን ኖሮ ዓርብ ዕለት ይህችን ሴት ማየት ነበር:: ጆንያ ታጥቃ፣ አመድ በላይዋ እየነሰነሰች፣ በልቅሶ ያልተባበራትን ሁሉ እየተቀየመች፣ የማርያም ልጅ የሠራኝን ሥራ እዩልኝ እያለች ትውልና ትኖር ነበር:: ጌታ ግን እስከ ሽምግልና በእርሱ ፊት ገና ልጅ እንደ ሆንን ያውቃል:: በጌታ ፊት:-

- ሽምግሎ ጠቢብ የሚሆን፣
- ሽምግሎ ራሱን የሚችል የለም:: ሁሉን እንደ ቋንቋው እንደ ልጅ ይቀበለዋል::

የዕብራውያን መልእክት ፀሐፊ *«እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፣ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት!»* (5፣7) ይላል:: ጌታችን እንዲህ ባለ ሁኔታ የጸለየው መቼ ነው? ስንል በጌቴሴማኒ ጫካ ውስጥ ነው:: ጸሎቱ ብርቱ ጩኸት ነበረው:: እንዲህ ያለ ታላቅ ጩኸት በመስቀል ላይ ተሰምቷል:: ይኸውም:- *«ኤሎሄ ኤሎሄ፥ ስለ ምን ተውኸኝ?»* ሲልና ነፍሱን ሲሰጥ ነው (ማቴ. 27፥46፤ ሉቃ.23፥46):: በጌቴሴማኒ ጫካ ብርቱ ጩኸት የጮኸው ለምንድነው? ሞትን ፈርቶ ነውን? በፍጹም አይደለም:: ወደዚህ ዓለም የመጣው ሊሞት (ቤዛ ሊሆን) ነው:: ወደ ኢየሩሳሌምም በታላቅ አጀብ የገባው እንደሚሞት እያወቀና እየተናገረ ነው:: ታዲያ በጌቴሴማኒ ጫካ ከሞት ሊያድነው ወደሚችል አባቱ ለምን ብርቱ ጩኸት ጮኸ? ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ቤዛ ዓለም ሊሆን ነው:: ቤዛ ወይም ምትክ የሚሆን ደግሞ የበደለኛውን በደል ይሸከማል:: የበደለኛውን በደል ከተሸከመ የበደልን ዋጋ ይከፍላል:: ኃጢአት የሚያስከትለው የመጀመሪያው ቅጣት ከመለኮታዊ መጽናናት መለየት ነው:: እግዚአብሔር ኃጢአተኛው ኃጢአት ሲሠራ ይተወዋል:: ያም ኃጢአተኛ ብቸኛ ይሆናል:: ኢየሱስ ንጹሐ ባሕርይ ቢሆንም የሰውን ኃጢአት ተሸክሟልና የኃጢአት ዋጋ እስኪከፍል የመተውን ዕዳ ይቀበላል:: እርሱ ከዘላለማዊ የፍቅር አባቱ ለአንዲት ቅጽበት ተለይቶ አያውቅም:: አሁን ግን የኃጢአትን ዋጋ እስኪከፍል አባቱ ይተወዋል::

ኢየሱስ ይህን ባሰበ ጊዜ ተጨነቀ:: የደም ላብ አላበው:: ይህ የከፍተኛ ጭንቀት ምልክት ነው:: ከፍተኛ ጭንቀት በሚሰማን ጊዜ በቆዳችን አካባቢ ያሉ ጥቃቅን የደም ሥሮች ይበጠሳሉ:: በዚህ ጊዜ ደም በቆዳችን ይታያል:: ይህ በጣም በጥቂት ሰዎች ሊታይ የሚችል ነው:: የኢየሱስ ጭንቀት ምን ያህል ብርቱ እንደ ነበር የሚያስረዳ ነው:: እርሱ ግን የተጨነቀው ሞትን ፈርቶ ሳይሆን ከአባቱ መለየትን ፈርቶ ነው:: ከሞት በላይ ይህ ከባድ ነው:: የዕብራውያን ፀሐፊ ይህን ወቅት አንሥቶ ነው:- «እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፣ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት!» ያለው (ዕብ. 5፥7):: ታዲያ ጌታችን በጌቴሴማኒ «አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ! ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን» (ማቴ. 27፥39) እያለ ደጋግሞ ጸልዮአል:: የአባቱ ፈቃድ ግን መሞቱ ነበር:: ታዲያ የዕብራውያን ፀሐፊ «ተሰማለት» የሚለው ምኑን ነው? አባቱ «ልጄ ሆይ መሞት አለብህ አንተ ካልሞትክ ዓለም አይድንም» ማለቱን ነው::

በጸሎታችን «አይሆንም» መልስ ነው:: ይህ ግን እግዚአብሔር አልሰማንም ማለት አይደለም:: አንድ ልጅ ከአባቱ አንድ ጥያቄ ሲያቀርብ አባቱ ጊዜና ጆሮ ሰጥቶ ይሰማውና «አይሆንም» ይለዋል:: አይሆንም መልስ ነው:: በጸሎታችን ላይ አንዳንድ ጊዜ በሕይወት እንድንቆይ እየተማፀንን ልናልፍ እንችላለን:: ምክንያቱም ከዚህ በኋላ መቆየታችን ለራሳችንም ለእግዚአብሔርም አሳዛኝ ሊሆን ስለሚችል ነው:: ስለታመሙት ወገኖቻችንም እንደ ፈቃድህ ይሁን ብለን መለመን መልካም ነው:: አንዳንድ ሰዎች ማለፋቸው ከመኖራቸው በላይ ትርፍ አለው:: ስለ አንድ አገልጋይ በቅርበት ሰምቻለሁ:: ይህ ሰው በጠና ታሞ ሚስቱ ቀንና ሌሊት እያነባች ስትጸልይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገለጸላት:: ለካ ግንባርዋ ያለው በእርሱ ጉልበት ላይ ነው:: እንባዋም ቀሚሱን እያራሰ ወደ ታች ይወርዳል:: ጌታም «ልጄ ሆይ ልውሰደው» አላት:: እርሷ ግን እ እ አለች:: መኖሩ ለአንቺም ለራሱም ለእኔም አይጠቅምም አላት:: አልሰማም አለች:: ያም ሰው ዳነ:: በወራት ውስጥ ወደ አሜሪካ ሀገር ሄደ:: የሰይጣን እምነት ተከታይ ሆነ:: እግዚአብሔርን ካደ ሚስቱንና ልጆቹንም ካደ:: ሚስቲቱም ከሸኘችው ቀን ጀምሮ አላየችውም:: ይህ እውነተኛ ታሪክ ነው::

ንጉሥ ሕዝቅያስ ሞቱ ሲነገረው መራራ ልቅሶ በማልቀሱ እግዚአብሔር በዕድሜው ላይ ዐሥራ አምስት ዓመት ጨመረለት:: ከዚያ በኋላ ግን የኖረበት ዕድሜ ያለማበት ዕድሜ ሳይሆን ለእስራኤል



ምርኮ ምክንያት የሆነውን የይሁዳን ምሥጢር ለባቢሎናውያን ያሳየበት አሳዛኝ ዕድሜ ነው (ኢሳይ. 38፥1-22፤ 39፥1-8):: በእግዚአብሔር ፈቃድ መኖር ብቻ ሳይሆን በእርሱ ፈቃድ መሞትም መልካም ነው:: ጸሎት ሁሉ ንጹሕ አይደለም:: የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን ጸሎትን ያጣራዋል:: አንድ ወዳጄ በድንገት ሞቱ:: እኔም እንዲህ ያለ የእግዚአብሔር ሰው መሞቱ ከራሱ ይልቅ ለምድር ስለሚያጎዳ አዘንኩ:: ከእኔ ይልቅ ለሚቀርቧቸውና ለሚወዷቸው ወዳጄ:- «የእኚህ አባት መሞት በጣም አሳዘነኝ» አልኳቸው:: እኚህም ወዳጄ:- «ልጄ ደስ ይበልህ! እግዚአብሔር ሰውን በሞት ሲጠራ ‹ይህ ልጄ ከዚህ በኋላ ቢቆይ የሚያየውንና የሚሰማውን አይቋቋምም:: ስለዚህ እርሱን እሰበስባለሁ ሥራዬን እኔ ራሴ እሠራለሁ› ብሎ ነው:: እግዚአብሔር እንደ ምንም ሆኖ ሥራዬን ብቻ ይሥራልኝ አይልም:: ‹ሥራዬን እኔ እሠራለሁ፣ ልጄን ግን እሰበስባለሁ› ይላል» ብለው ሲነግሩኝ ተስፋ ትንሣኤን ያላገናዘበው ሀዘኔ ተገፈፈ:: ዳግመኛ /ኢሳ.57፥1/አንብበ::

ሐዋርያው ጳውሎስም በደዌ የሚሰቃይ ሰው ነበር:: ከዚህ የሥጋ ድካም ለመዳን መላልሶ ቢጸልይም መልስ አላገኘም:: ይህንን ሁኔታ ሲገልጥ 2ቆሮ. 12፥6-10 እንደዚህ ይላል:- «ልመካ ብወድስ ሞኝ አልሆንም፥ እውነትን እላለሁና! ነገር ግን ማንም ከሚያይ ከእኔም ከሚሰማ የምበልጥ አድርጎ እንዳይቆጥረኝ ትቼአለሁ:: ስለዚህም በመገለጥ ታላቅነት እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ፥ እርሱም የሚጎስመኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ! ይኸውም እንዳልታበይ ነው:: ስለዚህ ነገር ከእኔ እንዲለይ ሦስት ጊዜ ጌታን ለመንሁ:: እርሱም:- ጸጋዬ ይበቃሃል፥ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ:: እንግዲህ የክርስቶስ ኃይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ:: ስለዚህ ስለ ክርስቶስ በድካም በመንገላታትም፣ በችግርም በስደትም በጭንቀትም ደስ ይለኛል! ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝና::»

አንድ ወንድሜ «ጉዳዩ እንዴት ነው?» ስለው «ያው ነው» ካለኝ በኋላ «ወይ ሁኔታውን ለውጥ፣ ወይ እኔን ለውጥ ብዬ እየጸለይኩ ነው» አለኝ:: በሌላ ጊዜ ስጠይቀው «ጉዳዩ ያው ነው፣ እኔ ግን ተለውጫለሁ:: ደስተኛ ነኝ» አለኝ:: እግዚአብሔር እሳቱ እያለም ጥፋት እንዳያደርስ ማድረግ ይችላል:: አንዳንድ ጊዜ ችግሩን በመለወጥ ይረዳል:: ሌላ ጊዜ ደግሞ ችግሩን ትቶ እኛን በመለወጥ ይሰማናል:: ብቻ የምንለምነውን ማወቅ ከዚያም ፈቃድህ ይሁን ማለት ይገባናል::

# <u>ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት</u>

## <u>ትዕግሥት</u>

*«ለናከብረው የሚያከብረን፣ ስንሰማው የሚሰማን፣ ስንኖርለት የሚኖርልን፣ እሺ ስንለው እሺ የሚለን አምላክ ነው።»*

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *«ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል»* (ማቴ. 18፥19) በማለት የተናገረው ቃል ልብ ይነካል። ጌታ በተስማማችሁበት እስማማለሁ፣ ሁለትና ሦስት ሆናችሁ በስሜ ብትሰበሰቡ በሁለተኛው ላይ ሦስተኛ፣ በሦስተኛው ላይ አራተኛ ሆኜ እገኛለሁ ማለቱ ነው። በየዘመናቱ ለእርሱ ክብር በሚኖሩ ልጆቹ አሳብ ተስማምቷል።

ኤልያስ ንጉሥ አክአብን ከገሰፀ በኋላ፡- *«በፊቱ የቆምሁት የእስራኤል አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን! ከአፌ ቃል በቀር በእነዚህ ዓመታት ጠልና ዝናብ አይሆንም»* (1ነገ. 17፥1) ብሎ ዝናብ ለዘር፣ ጠል ለመከር እንዳይሆን ሲከለክል ከእግዚአብሔር ይህን አድርግ ተብሎ ታዝዞ አይደለም። እግዚአብሔር ግን ኤልያስ ለአምልኮተ እግዚአብሔር ቀንቶ የተናገረውን ቃል አፀና። ኤልያስ ሰማይን በግዝት ለጉሞ ሕዝቡ በረሀብ ሲያልቅ እርሱ በበረከት እየኖረ በረሀብ የሚያልቀውን ወገን ረሳ። እግዚአብሔር ግን ሕዝቡን አልረሳም፡- «በልቶ ቢክደኝ ይሻላል» በሚል ስሜት ይመስላል፡- *«ሂድ፥ ለአክአብ ተገለጥ፥ በምድር ላይም ዝናብ እሰጣለሁ»* አለው (1ነገ. 18፥1)። እግዚአብሔር ዓለምን ከመነናት ከኤልያስ አሳብ ጋር ተስማምቶ ሰማይን ለጐመ። ኤልያስን ትቶ ዝናብ አልሰጠም። ሂድና ተገለጥ አለው። እንደ ቃሉ ለሚኖሩ አገልጋዮች እግዚአብሔር እንደ ቃላቸው ያደርግላቸዋል።

ቅዱስ ገብርኤል ወደ ዘካርያስ የተላከው ሊያበሥር ነው። ዘካርያስ ግን እግዚአብሔርን ሳይሆን ራሱን በማየቱ ስለ ተጠራጠረ



ገብርኤል ዲዳ ትሆናለህ አለው። የብሥራቱ ልጅ እስኪወለድ ድረስ ዘካርያስ ዲዳ ሆነ። በየዘመናቱ እግዚአብሔር ለክብሩ በሚኖሩ ልጆቹ ቃል ተስማምቷል። ስናከብረው የሚያከብረን፣ ስንሰማው የሚሰማን፣ ስንኖርለት የሚኖርልን፣ እሺ ስንለው እሺ የሚለን አምላክ ነው። ጌታችንም *«ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል»* በማለት የኅብረት ጸሎት ሥልጣን እንዳለው ተናገረ። በአንድ ርዕስ ላይ እንደ ቃሉ በሆነ ልመና ባለ ኅብረቶች ቢስማሙ እግዚአብሔር በሰማይ ያጸድቀዋል። የኅብረት ጸሎት የተከበረ መሆኑን አባቶች ይናገራሉ። ስለ አንዱም ልበ ንጹሕ ሌሎች ይባረካሉ። በኅብረት ጸሎት ላይ የግል ጸሎት ስለሚፀልዩ ሰዎች አባቶች ሲናገሩ፡- «በፀሐይ ላይ ሻማ እንደ መለኰስ ነው» ይላሉ። ይህ የሚያሳየን የኅብረት ጸሎት ኃይል እንዳለው ነው።

*«ቢስማሙ»* የሚለው ቃል ወሳኝ ቃል ነው። ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ብዙ ችግሮች እንዳሉ ይነገራል። ትልቁ ችግር ግን አለመስማማት ነው። ስንስማማና ስንጸልይ የችግሮች ዕድሜ ያጥራል። ጸሎታችን መስማማት ስለ ሌለው መልሱ ርቋል። ሰሌን ሻጭና ሹሩባ የምትሠራ ሴት ተጋብተው ይኖራሉ። ሰሌን ሻጩ፡- «ሰው በሞተና ሰሌኔን በሸጥኩ» ብሎ ይጸልያል። ሚስቲቱ ደግሞ «ሴቱ ሁሉ ደስ ባለውና ሹሩባ በሠራሁ» እያለች ትጸልያለች። የሚሰማው ልጅ፡- «የእናቴና የአባቴ ጸሎት ለብቻ ለብቻ» አለ ይባላል። ዛሬም በመንፈሳዊ ኅብረቶቻችንና በአብያተ ክርስቲያናት የልብ መስማማት ስለ ሌለ ጸሎታችን ግዳጅ የሚፈጽም፣ ለትውልድ በረከት የሚያመጣ አልሆነም።

አንድ ልብ ሆነን በምንጸልየው ጸሎት እግዚአብሔር ይስማማል። መልሱም ፈጣን ነው። ለዚህም በቂ ምሳሌ የሚሆኑን የነነዌ ሰዎች ናቸው።

ጸሎት በሰማይ ሸንጎ በሥላሴ ዙፋን ፊት ጉዳይን ማቅረብ ነው። ጉዳዩ በጥበበ ሥላሴ ተመርምሮ እስኪፀድቅ ትዕግሥት ያስፈልጋል። ጸሎት ትዕግሥትን የሚጠይቀው ለምንድነው? ስንል፡-

1. እግዚአብሔር ሥራን የሚሠራበት የራሱ ጊዜ ስላለው፤
2. ነገር ሁሉ ውብ የሚሆነው በጊዜው ስለሆነ፤
3. እምነታችን እንዲጠነክር፤
4. ጸጋውን ሳይሆን ባለ ጸጋውን ማየት እንድንችል ነው።

## 1. ጊዜ አለው

እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ወደ መጨረሻው የሚሠራ አምላክ ሳይሆን ከመጨረሻው የሚጀምር አምላክ ነው:: ይህን ስንል በፊቱ ሁሉም ነገር በታቀደለት የጊዜ ገደብ እየሄደ ነው ማለታችን ነው:: ጸሎታችን ለእግዚአብሔር ጊዜ የሚገዛ (የሚታዘዝ) እንጂ ለእግዚአብሔር ቀን ቆራጭ ሊሆን አይገባውም:: እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን የሚያዋርድበት ለትሑታን ጸጋ የሚሰጥበት፣ ጽዋ የሚያስዋውጥበት፣ ምስኪኑን ቁእመድ ላይ አንሥቶ ወርቅ የሚያሰብስበት የጊዜ ቀጠሮ አለው:: እኛ ግን የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አሳብ ስለማናውቅ፣ የአሁኑን እንጂ የሚመጣውን ስለማናስብ፣ እግዚአብሔር ለኢያሱ እንዳደረገው ያሰቀውን ቀን ፀሐይን አቁሞ ሊሠራበት እንደሚችል ስለምንዘነጋ፣ አንድ ቀን በፊቱ እንደ ሺህ ዓመት እንደሆነች ማለት በአንድ ቀን የሺህ ዓመት ሥራ መሥራት እንደሚችል ስለማንረዳ ጊዜዬ አለቀ እያልን በጸሎታችን ላይ እናጕረመርማለን:: ያለቀው የእኛ እንጂ የእግዚአብሔር ጊዜ አይደለም:: ደግሞም እግዚአብሔር እንደ አልዓዛር ከሞት በኋላም ሊሠራልን የሚችል በጊዜ የማይወሰን ጊዜን ግን የሚወስን አምላክ ነው:: የእኛንና የሁኔታዎችን አካሄድ ማሰብ ትዕግሥት ቢነሣንም አቅሙ የማይለካው ጌታ ግን ለሁሉም ጊዜን እንደ መደበ መረዳት እጅግ መልካም ነው:: ጠቢቡ ሰሎሞን *«ለሁሉ ጊዜ አለው፤ ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው»* (መክ. 3፥1) ብሏል:: ብዙ ሰዎች ይህን ጥቅስ ይጠቅሳሉ:: የሚጠቅሱት ግን ጊዜ ራሱ እንደሚቸራቸው በማሰብ ነው:: ጊዜ ግን የማንም ውለታና ፍቅር ስለ ሌለው ማንንም አይክስም፣ ለማንም አይፈርድም:: ጊዜ የእግዚአብሔር ሎሌ ነው:: በጊዜ ውስጥ ፍርድን የሚያደላድል እግዚአብሔር ነው::

## 2. በጊዜው ውብ ነው

ዘር ያለ ጊዜው ጮርቃ ነው:: በጊዜው ግን መብል ነው:: ጽንስ ያለ ጊዜው አስፈሪ ነው:: የሚታቀፉት አይደለም:: በጊዜው ግን ተወዳጅ ልጅ ነው:: ያለ ጊዜው የሆነ በረከት ለናፋቂው እንኳ አስፈሪ ነው:: እግዚአብሔር የሚዘገየው ጉዳዩን እየሠራ እንጂ ረስቶት አይደለም:: በዝምታው ውስጥ ይሠራል:: በረከቱን ከመስጠቱ በፊት ትከሻችን እስኪጠነክር ይጠብቃል:: እንዳንረሳውና እንደ ቀላል እንዳንቆጥረው የሚፈልገውን ስጦታ የትዕግሥትን ደጅ ጥናት እንድንጠናበት ያደርጋል:: ቢሆንም መዘግየቱ ለመልካም ነው:: ጠቢቡ ሰሎሞን *«ነገርን ሁሉ በጊዜው ውብ አድርጎ ሠራው»* (መክ.3፥11) ብሏል::



## 3. እምነታችን ይጠነክራል

እምነት በትዕግሥት ካልተፈተነ እውነተኛና ጠንካራ አይደለም:: በክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች በተግባር ሲለማመዱ እርግጠኛ ይሆናሉ:: ስለ እምነትም የተማርነውን በሕይወታችን ስናከናውነው ይጠነክራል:: ትዕግሥት መራራ ቢመስልም ፍሬው ግን ጣፋጭ ነው:: በመታገሣችን የምናተርፈው ትዳራችንን፣ ወዳጆቻችንን ብቻ ሳይሆን ነፍሳችንንም ነው:: በትዕግሥታችን ውስጥ ያለው ትልቁ ቁምነገር የነገሮች መለወጥ ሳይሆን የእኛ መለወጥ ነው:: ብዙ ጊዜ የደረሱብንን መከራዎች እንዲያስወግድ ወደ እግዚአብሔር እንጸልያለን:: ነገር ግን ከመከራው መወገድ በላይ ትዕግሥትን ብንለምን ይሻላል:: ምክንያቱም ይህ መከራ ቢያልፍ ሌላ መከራ ይተካል:: ትዕግሥት ግን ካለን በሁሉ እንጸናለን:: ኢዮብን ስንተርክ ስለ ልብ ወለድ እያወራን አይደለም:: ኢዮብ በእግዚአብሔር ላይ ፍቅራችንና ተስፋችን ጽኑ እስከ ሆነ የፈተና ጎርፍ እንደማይወስደን የሚናገር ቋሚ ምስክር ነው:: ምናልባት ሁሉን ከስረን ተቀምጠን የትዕግሥት ዋጋው እንሶብን ይሆናል:: ነገር ግን ድል ውጫዊ ሳይሆን መንፈሳዊ መሆኑን መረዳት አለብን::

ለምሳሌ:- በዓላውያን ነገሥታት አደባባይ የሚሰየፍ አንድ ሰማዕት ያመንኩትን ከመተው ሞትን መርጫለሁ ብሎ ሲሞት የሚያዩት ወገኖች ተሸነፈ ሳይሆን አሸነፈ ይሉታል:: ግን እርሱ ወድቆ ጠላቱ ይንጎማለላል:: ቢሆንም አሸነፈ ይባላል:: የገዳይ ወገኖች ሳይቀር በልባቸው ያደንቁታል:: ድል መንጎማለል ውጫዊ እሴት ሳይሆን ድል መንፈሳዊ መሆኑን እስተዋላችሁን? እንዲሁም ብዙ ነገሮችን ብንከስርም ትዕግሥት ግን በትምህርት የማናገኘው ድል ነው::

በእውነት ለምነን ከተቀበልነው ሳንለምን የተቀበልነው ይበልጣል:: ሚሊዮን ዓመት ብንኖርና ሚሊዮን ጊዜ ቢደረግልን ከተደረገልን አይበልጥም:: የተደረገልን መዳናችን ነው:: በራሳችንና በምንወዳቸው ላይ እንዲሆን የምንፈልገው በረከት አንዳንድ ጊዜ ጊዜ ያለፈበት ይመስለናል:: እግዚአብሔር ግን ሲነሣ አይረፍድበትም በሰዓቱ ይደርሳል:: ስለዚህ በትዕግሥት መጠበቅ አለብን:: አዎ ትዕግሥት እምነታችንን ያጠነክረዋል::

## 4. ባለ ጸጋውን እንድናይ

መልካም ሕይወትን የምንጠብቀው በራሱ በእግዚአብሔር ሳይሆን እግዚአብሔር በሚያደርግልን ነገር ላይ ነው:: ለብዙዎቻችን

እግዚአብሔር ማለት ያለ ሂሳብ አስቤዛችንን የምናነግበት የገበያ ማዕከል ነው። ለብዙዎቻችን እግዚአብሔር የጥቅማችን አገልጋይ ነው። በዛሬው ዘመን እንደ ሦስቱ ወጣቶች ያለ የእምነት ቃል የሚሰማ አይመስልም፦ *«የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል፤ ከእጅህም ያድነናል፥ ንጉሥ ሆይ! ነገር ግን፥ ንጉሥ ሆይ፥ እርሱ ባያድነን፥ አማልክትህን እንዳናመልክ ላቆምኸውም ለወርቁ ምስል እንዳንሰግድለት እወቅ አለ።»* (ዳን. 3፥ 17-18)። በዛሬ ዘመን ባያድነንም እናመልከዋለን የሚል መኖሩ ያጠራጥራል። ብዙዎቻችን እግዚአብሔርን ሳይሆን የምናመልከው ጥቅማችንን ነው። በዛሬው ዘመን በልጆችና በወላጆች መካከል ያለው ድምፅ አልባ ቅሬታ ልጆች ወላጆቻቸውን የሚወዱት ጥቅማቸውን ለአንድ ደቂቃ እንኳ እስካላጎደሉ ድረስ ነው። እኛም ለእግዚአብሔር እንዲህ እየሆንን ነው ያለነው። እግዚአብሔር እሴታችን ሳይ ደስታችንን እንዳንመሠርት፣ በሚሄድና በሚመጣ ነገር እንዳንደገፍ፣ ባጠቃላይ ፍላጎታችን ጣዖት እንዳይሆንብን ያዘገየዋል። ጸጋውን ረስተን ባለ ጸጋውን ማየት ስንጀምር እግዚአብሔር ማከናወን ይጀምራል። ይህን በደንብ የሚገልጥልን በመዝ. 45፥10 ላይ ያለው የእውነት ቃል ነው፦ *«ዕረፉ፥ እኔም አምላክ እንደ ሆንሁ እወቁ፥ በአሕዛብ ዘንድ ከፍ ከፍ እላለሁ፥ በምድርም ላይ ከፍ ከፍ እላለሁ።»*

እግዚአብሔር የለመነውን ከመስጠቱ በፊት ልባችን ማረፉን ያረጋግጣል። ለእግዚአብሔር ጉዳያችንን ካሳወቅን በኋላ ልባችን በፍጹም ሲያርፍ እግዚአብሔር የከፍተኛነቱን ሥራ ይሠራል። ልባችን የተጋጋለበትን ነገር እግዚአብሔር አያደርግልንም። አስተውለን ከመያዝ እናብድበታለንና። ጉዳዩን ትተን እግዚአብሔርን ብቻ ስናይና «ጌታዬ ይበቃኛል» ስንል እግዚአብሔር ያከናውንልናል። በደመ ነፍስ የሚገባን ነገር አለ። ደግሞም እንዲህ ብለን እንናገራለን፦ «ያንን ጉዳይ ስተወው ተሳካ» እንላለን። ነገር ግን ስንተወው ራሱ አልተሳካም። ስናርፍ ግን እግዚአብሔር ሠራው። *«ዕረፉ፥ እኔም አምላክ እንደ ሆንሁ እወቁ፥ በአሕዛብ ዘንድ ከፍ ከፍ እላለሁ፥ በምድርም ላይ ከፍ ከፍ እላለሁ።»*

ሕፃናት አንድ ነገር ይዘን መግባት ካለመድናቸው ሁልጊዜ ይጠብቃሉ። ስንገባ እኛን ሳይሆን የያዝነውን ለመያዝ ይሮጣሉ። ማንኛውም ወላጅ «መጀመሪያ እኔን ሳመኝ» ይላል። ልጁ ግን የሚታየው የለመደው ነገር ነው። ወላጆች ደግሞ መጀመሪያ እኔን ከዚያ በኋላ እኔ የያዝኩትን ትወስዳለህ እያሉ ይከራከራሉ። ለእግዚአብሔርም እንዲህ ሆነንበታል። እኛ የሚታየን እግዚአብሔር የያዘው ነው። እግዚአብሔር



ደግሞ ልጄ ሆይ፥ መጀመሪያ እኔን እየኝ ከዚያ በኋላ የያዝኩት ላንተ ነው ይለናል።

ጸሎታችን ተለሚ እንዲሆን ትዕግሥት ያስፈልገናል። ትዕግሥት መራራ ይመስላል። ፍጻሜው ግን ጣፋጭ ነው። ትዕግሥት የሚያስፈልገን ለአጠቃላይ ሕይወታችን እንጂ ለጸሎታችን ብቻ አይደለም። በመታገሣችን እግዚአብሔርን፣ ነፍሳችንን፣ ትዳራችንን፣ ወዳጆቻችንን፣ ራእያችንን እናተርፋለን። ትዕግሥት የሌለን ወፈፌ ሰዎች ከሆንን ግን ትዝብትን ከማትረፋችንም በላይ ዘመን ካለፈ በኋላ ራሳችንንም እንታዘበዋለን። ትዕግሥት በማጣት በዓመት የገነባነውን በዕለት ማፍረስ ሊሰለቸን ይገባል። ሁልጊዜ በአዲስ መሠረት የምንኖር የጀመርነውን የማንፈጽም ከሆነ የመኖር ብቃታችን ከንቱ ነው ማለት ነው። በመታገሥ የተፈታውን ትዳራቸውን መልሰው ያሠሩ፣ ያለቀለትን ወዳጅነት እንደ ገና ያተረፉ፣ ራእያቸውን ከመጥፋት ያዳኑ ብዙዎች ናቸው። እግዚአብሔርም ለሚታገሡት ቸር ነው (መዝ. 144፥9)።

ከዛሬ ስምንት ዓመት በፊት እግዚአብሔርን ለአንድ ዓመት ያህል ስላልሆኑ ነገሮች ማመስገን ጀምሬ ነበር። በጊዜው ልቤ የተወጠረባቸው፣ ካልሆኑ ሰላም የለኝም ያልኩባቸው፣ እንቅልፍ ያጣኹባቸው ነገሮች ነበሩ። እነዚያ ፍላጎቶቼ ያን ጊዜ ሆነው ቢሆን ኖሮ ግን ዛሬ በሕይወት እንደማልቆይ ገባኝ። እኔ በፊቴ ያለውን ፍላጎቴን ብቻ አየሁ። እግዚአብሔር ግን ማንነቴን፣ አካባቢዬን፣ ዘመኑን፣ አስፈላጊነቱን አየና ከለከለኝ። በጊዜው አኩርፌአለሁ። ወደ ማስተዋል ስመለስ ግን የምስጋና ርእስ ሆኖልኛል። የለመንነው ሁሉ ቢሰጠን ኖሮ ጸሎታችን የአደጋ መጫሪያ በሆነ ነበር። የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን ጸሎታችንን ያርማል።

በሕይወታችን እግዚአብሔር ያልኩትን ለምን አልፈጸመልኝም? የሚል ኩርፊያ አለን። መለስ ብለን ግን እኔስ እርሱ ያለኝን ፈጽሜአለሁ ወይ? ብለን አንጠይቅም። እግዚአብሔርን ሲለምኑ ከቆዩ በኋላ ትንሽ ሲዘገይባቸው የመታገሡ ምሥጢር አልገባ ይላቸውና ወደ ዓለም የሚመለሱ፣ ወደ ሰይጣናዊ አምልኮ የሚሄዱ ሰዎች ብዙ ናቸው። ስንጠይቃቸውም እግዚአብሔር ይዘገያል ጠንቋይ ግን ቶሎ ይፈርዳል ይላሉ። ለሆዳቸው ወይም ለጊዜያዊ ጉዳያቸው ብለው የሰይጣን ባሪያ ይሆናሉ። ነገር ግን እንኳን ቢዘገይ ቢገድለንም እግዚአብሔር ይሻለናል።

የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ምድር አውጣን ብለው ጮኹ:: ካወጣቸው በኋላ በምድረ በዳ መቃማጠል ጀመሩ:: ለእግዚአብሔር ጥቅም የወጡ መሰላቸው እንዳልተቀጡ ሥርዓት አልባ ልጆች እስኪሰጣቸው ፍላጎቶቻቸውን በልቅሶ ማስከበር ጀመሩ:: ነቢዩ ይህንን ሲታዘብ:- *«ፈጥነውም ሥራውን ረሱ፥ በምክሩም አልታገሡም»* (መዝ 105፥13) ብሏል:: የእስራኤልን ልጆች ታሪክ ስንመለከት ጸሎትን በተመለከተ አንዳንድ ነጥቦችን እናገኛለን::

የመጀመሪያው:- የምንጸልየው ለእግዚአብሔር ብለን ሳይሆን ለራሳችን ብለን መሆኑን ነው:: ሌላውን የሚለምን ሰው ጠይቄ ባጣ አኮርፋለሁ ቢል ትክክል አይደለም:: እንዲሁም እግዚአብሔርን የሚለምን ቢሰጠው ደስ ሊሰኝ ባይሆንም ሊያመሰግን ይገባዋል:: ባለ መጸለዩ የሚጎዳው እርሱ እንጂ እግዚአብሔር አይደለም:: ቢሆንም እግዚአብሔር እንድንጸልይ በብዙ መንገዶች ያበረታታናል:: ሁለተኛ:- የእስራኤል ልጆች ለመጠየቅ ጊዜ እንዳስፈለጋቸው ለመቀበልም ጊዜ መውሰድ ነበረባቸው:: እግዚአብሔር ምን ያደረግላቸው እያለ ሲመክር እነርሱ ከጸሎት ስፍራቸው ተነሡ:: እኩራፊ ልጅ ጦሙን እንደሚያድር እስራኤልም እንዲሁ ሆኑ:: ሦስተኛ:- ሥራውን ረሱ:: እንዲደረግላቸው የሚፈልጉት ከተደረገላቸው አይበልጥም:: የተደረገላቸው የ430 ዓመት የባርነት ቀንበር መሰበር፣ ከፈርዖን አገዛዝ ነፃ መውጣት፣ በዓለም ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ባሕር ተከፍሎ መሻገር ... ነው :: የተደረገላቸውን ቢያስቡ በሚደረግላቸውም ተስፋቸው የፀና በሆነ ነበር:: በእውነት ዛሬም ቢሆን እንዲሁ ነው:: ያለፈውን አድራጎቱን ብናስታውስ የለመነውን እንደሚሰጠን ልባችን ሙሉ ይሆናል::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ትዕግሥት ወይም ሳይታክቱ ስለ መጸለይ የተናገረው ምሳሌ ልብ ይነካል:- *«ሳይታክቱም ዘወትር ሊጸልዩ እንዲገባቸው የሚል ምሳሌን ነገራቸው፥ እንዲህ ሲል:- በአንዲት ከተማ እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰውንም የማያፍር አንድ ዳኛ ነበረ:: በዚያችም ከተማ አንዲት መበለት ነበረች:: ወደ እርሱም እየመጣች:- ከባላጋራዬ ፍረድልኝ ትለው ነበር:: አያሌ ቀንም አልወደደም፤ ከዚህ በኋላ ግን በልቡ ምንም እግዚአብሔርን ባልፈራ ሰውንም ባላፍር ይህች መበለት ስለምታደክመኝ ሁልጊዜም እየመጣች እንዳታውከኝ እፈርድላታለሁ አለ:: ጌታም አለ:- ዓመፀኛው ዳኛ ያለውን ስሙ:: እግዚአብሔር እንኪያስ ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮኹ ለሚታገሣቸውም ምርጦቹ አይፈርድላቸውምን? እላችኋለሁ፥ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል:: ነገር ግን የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኝ ይሆንን?»* (ሉቃ. 18፥1-8)::



ዓመፀኛው ዳኛ ስለ ርኅራኄው ሳይሆን ስለ ጭቅጭቋ ልፍረድላት አለ:: እግዚአብሔር ከዓመፀኛው ዳኛ ይልቅ ቸር ነው:: ስለ ጭቅጭቃችን ሳይሆን ስለ ፍቅሩ ያደርግልናል:: እግዚአብሔር አንድ ጊዜ የነገርኩትን ሰምቷል ብሎ ማረፍ እምነት ነው:: ሳይታክቱ መጸለይም እምነት ነው:: ከልጆች አንዳንዶቹ የሚፈልጉትን ወዲያው ይናገራሉ:: ከዚያ ወዲያ ብንረሳው እንኳ ዳግም ማስታወስ አይወዱም:: ያልተደረገው ስላልተቻለ ነው ብለው የሚያስቡ ይመስላል:: አንዳንዶች ግን ካልተሰጣቸው አይላቀቁም:: ስለ ውትወታቸው ብቻ ሳይሆን የሚወተውቱበት ነገር ትክክለኛ ስለ መሆኑ ይደረግላቸዋል:: እነዚህ የሚወተውቱ ልጆች አፍቃሪ እንደ ሆኑና ራሳቸውን እንደ ጣሉብን ስናስብ አባታዊ ስሜት ይሰማናል:: ከልጆቻችን ባሻገር እንዲህ ያሉ ሰዎች የሚገጥሙን አልፎ አልፎ ነው:: ብዙዎች ወላጆቻቸውን ይወተውቱ ይሆናል:: እግዚአብሔርን እንደ ወላጅ ቆጥረው የሚወተውቱ ግን ጥቂቶች ናቸው:: እግዚአብሔር ግን ውትወታቸው ደስ ይለዋል:: *«እግዚአብሔር እንኪያስ ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮኹ ለሚታገሣቸውም ምርጦቹ አይፈርድላቸውምን?»* (ሉቃ. 18፥7) የሚለውን ቃል ማስተዋል ያስፈልገናል:: እኛ እግዚአብሔርን የታገሥነው የሚመስለን ጊዜ ብዙ ነው:: የታገሠን ግን እርሱ ነው:: ጸሎታችንን የሚፈጽምልን በትዕግሥቱ ፍጹምነት ነው:: እኛ የበደሉ ሰዎችን ለማረም የምንነሣው የምናደርግላቸውን ቸርነት በማቆም ነው:: እግዚአብሔር ግን በመስጠት የኃጢአተኞችን ልብ ለንስሐ ያስገዛል:: ኃጢአት ሠርተን የምንጠብቀው መዓት ቀርቶ ትልቅ ቸርነት ሲደረግልን እናያለን:: ይህ እግዚአብሔር ከክፉ ሥራችን ጋር መተባበሩ ሳይሆን ስሜታችንን በመንካት ለንስሐ ማነቃቃቱ ነው (ሮሜ 2፥4):: ዳግመኛም ጌታችን:- *«ነገር ግን የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኝ ይሆንን?»* (ሉቃ. 18፥8) ያለው አስፈሪ ቃል ነው:: ይልቁንም የተነገረው ሲፈጸም ስናይ ይበልጥ ያስፈራል:: ዛሬ አማኝ ነኝ የሚለው እየበዛ ቢመስልም ነገር ግን የእውቀት እምነት እንጂ እውነተኛ እምነት እየጠፋ ነው:: እንኳን አማኝ የእምነት ትምህርት እየጠፋ ነው:: ለምናየውና ለምንሰማው የዓለም ክፍተት መፍትሔ በእግዚአብሔር እጅ አለ ብሎ የሚጸልይ ምእመንና የሚያጸልይ የሃይማኖት አባት ጠፍቶ ስናይ የጌታችን ቃል እየደረሰ መሆኑን እንገነዘባለን::

ለጸሎታችን ትዕግሥት አስፈላጊ ነው ስንል የማይረሱ ሁለት ታሪኮች አሉ:: ይኸውም ከብሉይ ኪዳን ያዕቆብ፣ ከአዲስ ኪዳን ከነናዊቷ ሴት ናቸው:: ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር ሲታገል እንዳደረ ተጽፎአል:: ዘፍ. 32፥22-32 ይህን አስደናቂ ክፍል ይዞአል:: ያዕቆብ *«ካልባረክኸኝ አልለቅህም»* አለው:: ያዕቆብ በረከት ብሎ የጠራው

በወቅቱ እንደ ገንዘብ የሚቆጠረውን ክብት፣ ወይም ቤት ንብረት አይደለም። በረከት ያለው በእግዚአብሔር ብቻ መደሰትን ነው። ያዕቆብ እነዚህ ሁሉ የተሟሉለት ሰው ቢሆንም በሕይወቱ ግን እርካታ አልነበረውም። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ታገለ። *«አለመርካቴን ተሸክሜ መኖር አልችልም። ጌታ ሆይ ገላግለኝ»* ብሎ ሙጥኝ አለ። እግዚአብሔርም ጩኸቱን ለማለት። ያዕቆብም *«እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ ሰውነቴም ድና ቀረች»* አለ። እውነተኛና ጥልቅ ጥያቄውን ያዕቆብ አቀረበ። እንደ ያዕቆብ የሆንን ብዙዎች ነን። ለሰዓታት የከበዱን የጭንቀት ጊዜዎች ለወራት ቢሆኑ ኖሮ የምንፈርስ መስሎን ነበር። እግዚአብሔር ግን ሲያስፋልንንና ከብቸኝነት ሲገላግለን አይተናል።

እንደ ያዕቆብ ቀጥር ልመናን በማቅረብ የምትታወቀው ከነናዊቷ ሴት ናት። ይህች ሴት ከአሕዛብ ወገን ብትሆንም ጥልቅ እምነት ግን ታይቶባታል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእምነታቸው ትልቅነት ከተደነቀባቸው ሁለት ሰዎች አንዷ ይህች ሴት ናት (ማቴ. 8፥5-13፣ 15፥21-28)። ይህች ሴት ጸሎቷ በእልፍኝ ወይም በድብቅ ሳይሆን በአደባባይ ነበር። ጸሎቷን ያቀረበችው በዝምታ ወይም በለሆሳስ ሳይሆን በጩኸት ነበር። ጸሎት ጥልቅ ከሚሆንባቸው መንገዶች አንዱ ጩኸት ነው። ጩኸት ከቤት ወጥቶ ድምፄ አማረ አላማረ ሳይሉ ያለ ይሉኝታ የሚደረግ የድረሱልኝ ጥሪ ነው። ይህች ከነናዊት ሴት በአደባባይ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እሪ አለች። ይህ ትልቅ እምነት ነበር። ዛሬ በአደባባይ ሰላማዊ ሰልፎች፣ ተቃውሞዎች ይሰማሉ። በአደባባይ ወደ ጌታ የሚጮኽ ግን ጠፍቷል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዚህች ሴት ጩኸት ፈጣን መልስ አልሰጠም። ጭካኔ የሚመስል ዝምታ፣ የተዋት የሚመስል ንግግር ተስተውሎበታል። ይህች ሴት የታመመችው ልጇ ስትሆን የምትለምነው ግን «ማረኝ» እያለች ነው። ከልመናዎች ሁሉ ትልቅ ልመና «ማረኝ» ነው። እግዚአብሔር ከማረን የሚቀርብን ጸጋ የለም። ይህን ጽሑፍ እየጻፍኩ ሳለሁ በውጭ አገር የሚኖር አንድ ወንድሜ ደወለልኝ። እኔም እግዚአብሔር አሳሰበኝና፦ «ጌታ ሆይ ራስህን ስጠኝ ብለህ ለምነው። ባለ ጸጋውን ከያዝህ ጸጋው አይጎድልብህም» አልኩት።

ይህች ሴትም ማረኝ አለች። ከዚህ ሁሉ በላይ የታመመች ልጇ ስትሆን ማረኝ የምትለው ግን ሴቲቱ ናት። ዓይኔ ይህን ስቆቃ የሚያየው፣ ጆሮዬ ይህን ስቃይ የሚሰማው ኃጢአቴ በዝቶ ነው እኔን ከማርከኝ የልጄ ታሪክ ይለወጣል ማለቷ ነው። ይህ ወደ ጥልቅ ጸሎት የሚያደርስ የንስሐ መንፈስ ነው። እኔን ከማርከኝ አገሬ ትድናለች የሚል ጸሎተኛ ወደ ጸሎት ምሥጢር የደረሰ ነው።



ለዚህች ከነናዊት ሴት ጩኸት ጌታ መልስ አልሰጠም። ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው ቢለምኑትም እንደማይሆን ነገራቸው። በመጀመሪያ ጩኸቷን ባለ መስማቱ ቀጥሎ የደቀ መዛሙርቱን ጥያቄ ባለ መቀበሉ ተስፋ አልቆረጠችም። ይበለኝ ይገባኛል እኔ ኃጢአተኛ ነኝ። ግን በፍቅር አሸንፈዋለሁ ብላ የወጣች ትመስላለች። በመንገዱ ትክክል ወድቃ አላሳልፍም አለችው። ጌታ ግን ታጥቦ ጭቃ ለሆኑ ሰዎች ጸጋውን እንደማይሰጥ ተናገረ። እርሷም ለልጆችህ የሚገባውን ጸጋ በረከት ሳይሆን ከልጆችህ የተረፈውን ፍርፋሪ ምሕረት አትንሣኝ። እኔ ውሻህ ነኝ የሚል ጥልቅ ንስሐ አሰማች። ጌታ ኢየሱስም፦ *«አንቺ ሴት፥ እምነትሽ ታላቅ ነው፤ እንደ ወደድሽ ይሁንልሽ»* አላት (ማቴ. 15፥28)።

ያዕቆብና ከነናዊቷ ሴት ቀጥር ልመናቸውን አቀረቡ። የልመናቸውን በረከት ታቅፈው ተመለሱ። እነዚህ ሰዎች ሳንታክት መጸለይ እንደሚገባን ያስተምሩናል። የእነዚህን ሰዎች ልምምድ በመያዝ እግዚአብሔር የጸሎቴን መልስ እስኪመልስ ጾሜን አልፈታም፣ ሱባዔዬን አልከፍትም የሚሉ ሰዎች ይኖራሉ። ከእግዚአብሔር የልመናቸውን መልስ የሚቀበሉት እግዚአብሔርን በማስጨነቅ ይመስላቸዋል። ያዕቆብን ብንመለከት እግዚአብሔርን የሚያስጨንቅ ጸሎት አላቀረበም። ባዶነትን መሸከም ስላቃተው፣ ከዚህ በኋላ እየበላሁ የሚርበኝ፣ እየጠጣሁ የሚጠማኝ፣ እየለበስኩ የሚበርደኝ፣ በቤት እያደርኩ የምፈራ ሰው መሆን አልፈልግም ከዚህ ባዶነቴ ገላግለኝ የሚል ነበር። ዛሬም ሰዎች ቀን በሚሰጥና ቀን በማይሰጥ ችግር ውስጥ ያልፋሉ። ቀን ከማይሰጥ ችግሮች አንዱ ባዶነት ነው። ከዚህ ለመገላገል መጮኽ መማፀን ይቻላል። እግዚአብሔርም እንዲህ ያለውን ጩኸት ፈጥኖ ይሰማል። ያዕቆብ እግዚአብሔርን አስጨንቆ ለመቀበል ሳይሆን የራሱን አለመቻልና ያለቀ ጉልበቱን ለማስረዳት ጥሯል። ከነናዊቷ ሴትም ጸሎቷን የከለከለው ጣኦታዊ ኑሮዋ በመሆኑ ኢየሱስ ወደ ንስሐ እስክትመጣ ልመናዋን አልመለሰም። ማንነቷ ታይቷት ውሻ ነኝ ባለች ጊዜ ግን ጥያቄዋ ተመለሰላት።

በተለያየ ምክንያት የጸሎታችን መልስ ሲዘገይ በጾም በጸሎት መጠየቅ፣ የጽሞና ጊዜ መውሰድ ተገቢ ነው። እግዚአብሔርን ግን በማስገደድ መቀበል አንችልም። እግዚአብሔር ፈቃድ ያለው አምላክ ነውና። በሕይወታችን ብዙ ግራ የሚያጋቡን፣ መልሳቸው የራቀብን ጸሎቶች አሉ። ስለ መዘግየታቸው ጥርት ያለ መረጃ ባይኖረንም የዘገዩት ግን ለኛ መልካም በሚያስበው በእግዚአብሔር እጅ ላይ በመሆኑ በትዕግሥት መጠበቅ ይገባናል።

ዳንኤል ለሃያ አንድ ቀን ሱባዔ ገብቶ ነበር:: ሱባዔ በገባ ዕለት እግዚአብሔር ለምቶት መልአኩ ወደ ዳንኤል ተላከ:: ነገር ግን የፋርስ መንግሥት አለቃ የተባለው ሰይጣንና ሠራዊቱ ከመልአኩ ጋር ተዋጉ:: ውጊያው ለሃያ አንድ ቀን ስለ ቀጠለ ዳንኤል ሃያ አንድ ቀን መልሱን አላገኘም ነበር:: በሃያ አንደኛው ቀን ግን መልአኩ መልሱን ይዞ መጣ (ዳን. 10፥1-13):: ዳንኤል በጸለየ ቀን ተሰምቷል:: ነገር ግን ሃያ አንድ ቀን በሰይጣን ውጊያ መልሱ ዘገየበት:: ሰይጣን መልሱን ቢያዘገይም ዳንኤል ግን ትዕግሥትን ተማረ:: እንዳንጸልይ የሚዋጋን ጠላት አለ:: ደግሞም የጸሎታችንን መልስ እንዳንቀበል የሚዋጋን ጠላት አለ:: እግዚአብሔር የጸሎታችንን መልስ ይዞ ሲመጣ ከጸሎት በታችን እንዳንታጣ በትዕግሥት መጠበቅ ይገባናል::

አዎ ጸሎታችን ተሰሚ፣ መሥዋዕታችን ግዳጅ ፈጻሚ እንዲሆን:-

1. እምነት
2. እንደ ፈቃዱ መጸለይ
3. በስሙ መጸለይ
4. ኃጢአታችንን መናዘዝ
5. የምንለምነውን ማወቅና
6. ትዕግሥት አስፈላጊ ናቸው::



# ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

## ምስጋና

*አይሁዶች «ተቀብሎ የማያመሰግን ከቀማኝ ይቆጠራል» ይላሉ::*

እግዚአብሔር አባታችን ነው:: እግዚአብሔር አባታችን የሆነው በሁለት ዋጋ ነው:: በመፍጠርና በማዳን:: ወላጆቻችን ወልደውናል እንጂ አልፈጠሩንም:: እግዚአብሔር ግን የፈጠረን አባታችን ነው:: እግዚአብሔር በተፈጥሮ ብቻ ሳይሆን በማዳኑ ሥራም እንደ ገና ልጆቹ አድርጎ ተቀብሎናል:: *«እኛ ፍጥረቱ ነንና! እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን»* (ኤፌ. 2፥10):: በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን የሚለው መዳናችንን ነው:: ሰው ታላቅ እድል ሲያገኝ «ዛሬ ነው የተፈጠርኩኝ» ይላል:: የክርስቶስ ማዳንም እንዲህ ያለ ታላቅ ዕድል ነው::

ወላጆች ልጆቻቸውን በሁለት ዋጋ ልጆች አድርገው የሚቀበሉበት ጊዜ ጥቂት ነው:: የወለዱትን ልጅ ከልደቱ ቀን በላይ በታላቅ ደስታ የሚቀበሉት ከታላቅ አደጋ ወይም ከሞት በተረፈ ጊዜ ነው:: ከዚያ በኋላ «የሞት ትራፊ ልጄ ነው» እያሉ በታላቅ ፍቅርና ስስት ይቀበሉታል:: እግዚአብሔርም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት አድኖ በታላቅ ፍቅር እንደ ገና ልጆቹ አድርጎ ተቀብሎናል:: በሁለት ዋጋ እኛን የተቀበለበት አባትነቱ ይህ ነው::

ወላጆቻችን ወለዱን እንጂ አልፈጠሩንም:: እግዚአብሔር ግን ፈጣሪ አባታችን፣ መነሻ ምንጫችን ነው:: ወላጆቻችን ኖረው ሲያኖሩን ያስባሉ:: እርሱ ክርስቶስ ግን ሞቶ አድኖናል:: አዎ የእግዚአብሔር አባትነቱ ልዩ ነው:: ከምድራዊ አባት ልዩ መሆኑን ለመግለጥ *«በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ»* የምንለው ለዚህ ነው:: አንድ በቤተ ክርስቲያን ደጃፍ ላይ ተቀምጦ የሚለምን ለማኝ እንዲህ እያለ ይለምናል:-

*እግዚአብሔርን አንተ አልኩት አንቱ ማለት ትቼ፣*
*አፍቃሪ አባቴ መሆኑን አይቼ!*

ታላቅ ሰው፣ ታላቅ ንጉሥ አንቱ መባሉ ወግ ነው:: እግዚአብሔር ግን ንጉሥ ብቻ ሳይሆን አባታችን ስለሆነ አንተ እንለዋለን:: በአገራችን አንቱ የክብር፣ አንተ የፍቅር ነው:: እግዚአብሔር የምናፈቅረው አባታችን ስለሆነ አንተ እንለዋለን:: ይህ ሣንቲም የሚለምን ለማኝ እንዲህ እያለ ይመሰክራል:: ጥበብ ክደሃ ዘንድ እንዳለች ማን ያስተውላል!

ብዙ ሰዎች የፈጣሪ ደጁ በቅርብ አይገኝም ብለው ይናገራሉ:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን እግዚአብሔር ቅርብ ነው ይላል (ፊልጵ. 4÷5):: ያውም ከእስትንፋሳችን ይልቅ ቅርብ ነው:: እነዚህ ሰዎች ምሳሌ ሲሰጡ አንድ ንጉሥ ጋ በቀጥታ ይገባል ወይ? መጀመሪያ ዘቦቹን ቀጥሎ የደጎንነት ሹሙን ቀጥሎ ፀሐፊውን፣ ... ማነጋገር ያስፈልጋል:: ወደ እግዚአብሔርም ዝም ብሎ አይገባም ይላሉ:: ልክ ነው ባለ ጉዳይ እነዚህን ሁሉ መስመሮች በትዕግሥት የማለፍ ግዴታ አለበት:: ካላደረገም የሚገጥመው አደጋ ነው:: የንጉሡ ልጅ ግን እነዚህን ሁሉ መስመሮች እያለፈ ነው ወይ አባቱን በየዕለቱ የሚያገኘው? ሰንል በፍጹም አይደለም:: አባቱን በቀጥታ ያገኛል:: እግዚአብሔርም ለእኛ አባታችን ነው:: እንደ ምድራዊ ንጉሥ እኛን ደጅ የማስጠናት ዓላማ የለውም:: የሚናፍቀን አባት ነው:: እኛን ለመቀበልም ደጆቹ በቀንና በሌሊት ክፍት ናቸው (ራእይ. 21÷25):: እኛ እርሱን ከምንወድበት ፍቅር እርሱ እኛን የሚወድበት ፍቅር ይበልጣል:: ስለ ወደደን ወደድነው እንጂ ስለ ወደድነው አልወደደንም:: የፍቅር ጀማሪ እግዚአብሔር ነው::

በአንድ አገር የሚኖር አንድ ንጉሥ ጠላቶቹን በጦር ሜዳ ድል ነሥቶ ሲመለስ ሕዝቡና ሠራዊቱ «እንኳን ደስ አለህ» የሚል ሠልፍ ያሳዩት ነበር:: ንጉሡም በአደባባዩ ላይ ሆኖ ሰላምታ እየሰጠ ሰልፈኛውን በሩቅ ሲያስተናግድ የንጉሡ ልጅ አባቱን ካገኘው ረጅም ጊዜው ነውና አባቱን ለማግኘት ወደ አደባባዩ ሲሮጥ ሲል ወታደሩ ይይዘዋል:: ልጁም ሲታገል አባቱ በሩቅ ያየውና ልቀቀው ይለዋል:: ልጁም ብርር ብሎ ሮጦ ሄደ:: የአባቱንም እግር አቅፎ አለቅም አለ:: ሌላ ወታደርም እየሮጠ መጥቶ «አንተ ልቀቅ ንጉሡ ናቸው እኮ» ቢለው ልጁም ቀና ብሎ «ላንተ ንጉሥህ ነው ለእኔ ግን አባቴ ነው» አለው ይባላል:: ለእኛም እግዚአብሔር አባታችን ነው:: በነጻነትና በፍቅር ደግሞም በቅዱስ ፍርሃት ልንቀርበው ይገባል:: ለእርሱ የምንሰጠው ትልቁ የሙገሳችን



ቃል «ንጉሥና አባት» የሚለው ነው:: አዎ የእግዚአብሔር ብርሃናዊ ውበት:-

- በንጉሥነት ላይ አባትነት፤
- በአምላክነት ላይ ትሑትነት፤
- በጌትነት ላይ አዛኝነት መሆኑ እንደ ደነቀን ይኖራል::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን «አባታችን ሆይ» ብለን እንድንጠራው አስተምሮናል:: እግዚአብሔር አምላክ ነው፣ ጌታ ነው:: ነገር ግን አምላካችን ሆይ፣ ጌታችን ሆይ ሳይሆን «አባታችን ሆይ» ብለን እንድንጠራው ለምን አስተማረን? ስንል ለእኛ ቅርብ የሆነ ወዳጅ መሆኑን ሲገልጥልን ነው:: እስራኤላውያን አምላካቸው ኃያል ገናና ከጠላት የሚታደግ መሆኑን ያምኑ ነበር:: ስለ እነርሱ ግድ የሚለው ቅርብ አባት መሆኑን ግን አይረዱም ነበር:: ለጌትነቱ ያላቸው ፍርሃት የአባትነቱን ቅርበት ጋርዶባቸው ነበር:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ወደዚህ ዓለም የመጣበት አንዱ ዓላማ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሰዎች ሊገልጥ ነውና እግዚአብሔር አባት መሆኑን አስረዳ:: ይህንንም በይበልጥ የገለጠልን «አባታችን ሆይ» በሚለው የጸሎት ትምህርቱ ነው::

የአቡነ ዘበሰማያትን ትርጓሜ በዚህ ርዕስ ተንትነን መፈጸም አይቻለንም:: አቡነ ዘበሰማያትን ግን በቁሙ ስንመለከተው ስለ ጸሎት የሚሰጠን ትርጉም አለ:: አቡነ ዘበሰማያትን በማየት ብቻ ጸሎት:-

- *መስጠት በሚችለው በሥላሴ ጌትነት ማመን መታመን፤*
- በመስቀል ላይ ወደ ተሠራው ሥራ መመልከት፤
- የክርስቶስን የምትመጣ መንግሥት መጠባበቅ፤
- ልብን ወደ ሰማይ ማቅናት፤
- ተስፋን በእግዚአብሔር ብቻ ማድረግ፤
- ፀንቶ መጠበቅ፤
- በቅድስና መበርታት፤
- ለሚለምኑን መራራት፤
- ግራና ቀኝ ሳንመለከት ጌታን ብቻ መጠበቅ (ማየት) መሆኑን ያሳያል::

የአቡነ ዘበሰማያትን ሙሉ ንባብና ጭብጥ ትርጉም ቀጥሎ መመልከት እንሞክራለን (ማቴ. 6÷9-13):-

*በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ* / እንድንወደው መፈለጉን/

| | |
|---|---|
| *ስምህ ይቀደስ* | / ክብር እንደሚገባው/ |
| *መንግሥትህ ትምጣ* | /ሁሉን የሚሰበስብ ሰፊ ቸርነት እንዳለው/ |
| *ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን* | /ውስን እውቀታችን የወደደው እንዳይሆን ታላቁን አማካሪ መጠየቂያ/ |
| *የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን* | /መስጠት መንሣት የእርሱ መሆኑን ማመን/ |
| *እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን* | |
| | /ይቅርታ መድኃኒት መሆኑን መማር/ |
| *ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን* | / ማሻገር ልማድህ ነው/ |
| *መንግሥት ያንተ ናትና* | /መግዛትህን አምናለሁ/ |
| *ኃይልም ክብርም ለዘላለሙ አሜን::* | /ነዋሪነትህን አምናለሁ::/ |

የአቡነ ዘበሰማያት ጸሎት ለጸሎት አራት ክፍሎች እንዳሉት ያመለክታል:: እነዚህም የጸሎት ክፍሎች:-

1. ምስጋና
2. ልመና
3. ንስሐ
4. ምልጃ ናቸው::

ማንኛውም ልከኛ ጸሎት እነዚህን አራት ክፍሎች ማሟላት አለበት:: ምስጋና የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቡ ነው:: ልመና የባለጠግነቱ ምስጋና ነው:: ንስሐ የመሐሪነቱ ውዳሴ ነው:: ምልጃ የፍቅሩ ማወጃ ነው:: *«በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ስምህ*



*ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤ ... መንግሥተ ያንተ ነውና ኃይልም ክብርም ለዘላለሙ አሜን»* ይህ የምስጋና ክፍል ነው:: *«የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፤»* ይህ ልመና ነው:: *«እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን»* ይህ ደግሞ ንስሐ ነው:: የአቡነ ዘበሰማያት ጸሎት እኛ እንጂ እኔ አይልም:: ለምሳሌ:- አባታችን ሆይ እንጂ አባቴ ሆይ አይልም:: ይህ ደግሞ ምልጃ ነው::

## <u>ምስጋና</u>

የአቡነ ዘበሰማያት *መክፈቻና መዝጊያ* ምስጋና *ነው::* *መክፈቻው «በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ÷ ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን» ሲል መዝጊያው ደግሞ «መንግሥት ያንተ ነውና ኃይልም ክብርም ለዘላለሙ አሜን»* ይላል (ማቴ. 6፥9-10፤ቁ. 13):: በእግዚአብሔር ፍቅር የተቃኙት አባቶቻችን «ጸሎታችንን ስንጀምር በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን እንላለን ለምን? ቢሉ ሥላሴ የበጎ ነገር ሁሉ ጀማሪ ስለሆኑ፤ ስንፈጽምም ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋናና ክብር ይሁን እንላለን ሥላሴ የነገሮቻችን ፍጻሜ ስለሆኑ ነው» ብለው ያስተምሩናል:: *መነሻ* ድፍረት፣ ፍጻሜ ውበት ይፈልጋል:: የ*መነሻ* ድፍረት፣ የፍጻሜ ውበት እግዚአብሔር ነው:: እንዲሁም የጸሎታችን መክፈቻ ምስጋና መሆኑ እግዚአብሔር የህልውናችን *መነሻ*፣ የጸሎታችን ጉልበት፣ የምናመሰግንበትን እንደበት የሰጠን መሆኑን ማሰብ ነው:: በምስጋና መፈጸማችንም ሰምቶ የሚመልሰውን ደግነቱን ማሰባችን ነው::

እነዚህ አባቶች አቡነ ዘበሰማያትን ከፋፍለው የመጸለይና የማስተንተን ልማድ ነበራቸው:: ለምሳሌ:-

> *«በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ÷ ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን» ይሉና «የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን» ካሉ በኋላ «መንግሥት ያንተ ነውና ኃይልም ክብርም ለዘላለሙ አሜን» ይላሉ::*

አገላለጻቸው የመጀመሪያው «እንደ ራሳችን ንብረት አምጣ የምንልህ አባትነትህ ቢሰማን ነው» የሚል ሲሆን *«መንግሥት ያንተ ነውና ኃይልም ክብርም ለዘላለሙ አሜን»* የሚሰውን ከመጨረሻው ላይ አምጥተው መጸለያቸው:- «የዕለት ፍላጎታችንን ለመሙላት ሥልጣንና

አቅም አለህ:: በየትም አቅጣጫ ብታደርግልን የለጪነት ምስጋናህን ማንም አይወስድብህም:: ለመስጠት አባታዊ ፍቅርህ ግድ ይልሃል:: ለማድረግ ኃይልህ ይቻለዋል:: ፈቃድና ችሎታህ ሳይነጣጠሉ ይኖራሉ» ማለታቸው ነው:: በመቀጠልም እነዚህ አባቶች *«በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤»* ይሉና *«እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን»* ሲሉ ማሰሪያውም እንደ ተለመደው *«መንግሥት ያንተ ነውና ኃይልም ክብርም ለዘላለሙ አሜን»* ይላሉ:: በአንድነት ብናቀርበው፦

> *«በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፥ ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን መንግሥት ያንተ ነውና ኃይልም ክብርም ለዘላለሙ አሜን::»*

እነዚህ ደጋግ አባቶች አሳባቸው «ሁሉን እንደ ልጅ እያየህ ይቅር የምትል አባት ሆይ፥ የይቅርታህ ብርሃን ተስሎብን ይኑር:: እምቢተኛ ውን ልብ እሺ ለማሰኘት ሥልጣንና ጸጋ አለህና የማያቋርጥ የይቅርታ ሕይወትን ስጠን አሜን» ማለታቸው ነው::

በመቀጠልም *«በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፥ ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን»* ይሉና *«ከክፉም አድነን እንጂ»* የሚለውን ልመና አቅርበው *«መንግሥት ያንተ ነውና ኃይልም ክብርም ለዘላለሙ አሜን»* ይላሉ:: አሳባቸው «ልጆችህ እንድንማር እንጂ እንድንሰቃይ የማትፈልግ ደግ አባት ሆይ ክፉውን ወደ ደግ በሚለውጥ ሥልጣንህ እናምናለን:: ሁልጊዜም መቻልህ አይጠረጠርም አሜን» ማለታቸው ነው:: ዳግመኛም *«በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፥ ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን»* ካሉ በኋላ *«ወደ ፈተና አታግባን»* በማለት መዝጊያውን *«መንግሥት ያንተ ነውና ኃይልም ክብርም ለዘላለሙ አሜን»* ይላሉ:: አሳባቸው «አስተምረህ የምትፈትን፣ ደረጃንም ከፍ የምታደርግ መምህርና አባት ሆይ የፈተናውን መውጫ መንገድ ታሳያለህ:: የከበደውን ማቅለል ሥልጣንህ ነው:: የመምህር ልጅ ፈተና ሲከብደው ደግ አይደለምና ለስምህ ስትል እርዳኝ አሳልፈኝ» ማለታቸው ነው::

እነዚህ አባቶች ምስጋናን እያስቀደሙ ኃይሉን በማወጅ ጸሎታቸውን ያከናውናሉ:: የጸሎት ዋነኛ ኃይሉ እግዚአብሔር ሲረዳን



ፈቃድና ኃይል አለው ብሎ በአመስጋኝ ልብ መቆም ነው:: የአቡነ ዘበሰማያትም ጸሎት መክፈቻውና መዝጊያው ምስጋና ነው:: ወደ ምስጋና ምርምር ውስጥ ስንገባ ምስጋና ሦስት ዓይነት ነው:: እርሱም፦ ስብሐት፣ ውዳሴ፣ አኰቴት በመባል ይጠራል::

<u>ስብሐት</u>፦ ትርጓሜው ክብር መስጠት ማለት ነው:: እግዚአብሔርን ስለ መለኮታዊ ባሕርዩ፣ ስለ ዘላለማዊ መንግሥቱ፣ ስለማይጠቀለል ሦስትነቱ፣ ስለማይለያይ አንድነቱ፣ ፍጻሜ ስለሌለው አነዋወሩ፣ ስለማይጨረስ ቸርነቱ፣ ሁሉን ስለሚቀበል ፍቅሩ፣... ማክበር ስብሐት ይባላል:: ስለ እግዚአብሔር የምንለው ሁሉ የሆነውን ከሆነውም ያነሰውን እንጂ በውዳሴ ከንቱ ወይም በደጋፊነት ስሜት አናገነውም:: የሆነውን ጠንቅቀን ለማወቅና ለማመስገን ዘላለም አይበቃንም:: «እግዚአብሔር ሆይ አንተ ራስህን በምታውቀው ልክ ተመስገን:: እኔ ግን በታየኝ መጠን እለግድልሃለሁ» ልንለው ይገባል::

<u>ውዳሴ</u>፦ ትርጉሙ ማድነቅ ነው:: እግዚአብሔርን ስለተቀደሱት ባሕርያቱ፣ ልዩ ስለሆኑት ጠባያቱ፣ የመለኮታዊ ውበቱ ድምቀት ስለሆኑት ስለፍቅሩ፣ ስለምሕረቱ፣ ስለቸርነቱ፣ ... ማድነቅ፣ ማዜም፣ መቀኘት፣ በቅድስና ውበቱ በብርሃናዊ ፊቱ እየተመሰጡ መጥፋት፣ ራስንና ጠፊውን ዓለም ትቶ ወደ ሰማይ ማደሪያ መብረር ውዳሴ ይባላል::

እግዚአብሔር የፈጠረውን ለማወቅ አትኩሮትና አንክሮ (መደነቅ) ያስፈልጋል:: የሰማይን ድባብነት፣ የምድርን ክብነት፣ ምድር ራሷ በውሃ ዳር ያለች ውብ ቦታ መሆኗን ለማየት፣ የአበቦችን ቀለም፣ የቅጠሎችን መዓዛ . . . ለማድነቅ የጽሞና ዕይታ ያስፈልጋል:: ፈላስፎችን ፈላስፋ ያደረጋቸው እኛ ረግጠን የምናልፈውን እነርሱ አትኩረው መመልከታቸው ነው:: የፍጥረቱ ውበት በፍለጋ ከተገኘ የፈጠረውማ ጌታ እንዴት ባለ የእምነት ዓይን ይታይ ይሆን? የውዳሴ መፍለቂያው ይህ ተመስጦ ነው::

<u>አኰቴት</u>፦ ትርጉሙ ምስጋና ማቅረብ ማለት ነው:: ስላደረገልን ነገር፣ በነጻ ስለሰጠን በረከት፣ በዙሪያችን ስላለው ድንቅ ሥራው፣ የጣቱ አሻራ ስላለበት ፍጥረታችን፣ ስለዛሬይቱ ቀን፣ የነገርነውን ስለሰማን፣ የጠየቅነውን ስለመለሰልን ምስጋና ማቅረብ አኰቴት ይባላል::

እያንዳንዱ ቀን በእግዚአብሔር ተአምራት እየታጀበ ይመጣል:: የእግዚአብሔርን ተአምራት ያላየች ነፍስ የለችም::

ተአምሩ ገብቷት የምታመሰግን ግን የታደለች ናት። እኛ ራሳችን የማናውቀው እግዚአብሔር ግን እንዳደረገልን የሚያውቀው ብዙ ተአምራት አሉ። «አንተ ለእኛ እንዳደረግህልን በምታውቀው መጠን ተመስገን» ከማለት በቀር የምንለው የለንም። ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን ከሰው ብንቀበለው ኖሮ የውለታው ክብደት ያለ ጊዜአችን እንድንሞት ባደረገን ነበር። የሰው ስጦታ ሰቀቀን አለው። ሲቀበሉት የማያሳቅቅ፣ ለመክፈልም የማያሳስብ የእግዚአብሔር ውለታ ብቻ ነው። በእውነት ያስገባነውን አየር የምናስወጣው፣ የዘረጋነውን እጅ የምናጥፈው እግዚአብሔር ሰፈዳን ብቻ ነው። የገባው ክረምት የሚወጣው፣ የመሸው ሌሊት የሚነጋው በፓርላማው ስምምነት ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። በሕይወታችን ሰው በማይገኝበት የሕይወት ምድረ በዳ የተገኘልን፣ እናት እንኳ ድምጻችንን ሰምታ በማትመጣበት በኑሮ ሽለቆ ደርሶ የረዳን እግዚአብሔር ብቻ ነው። ለዚህ ጌታ የምስጋና አምኃችን (እጅ መንሻችን)፣ የቅኔው ነዶአችን፣ የውዳሴው ዝርግፍ ወርቃችን፣ የስግደት አክብሮታችን ይገባዋል። እርሱን ስናመሰግነው እኛም ደስተኞች እንሆናለን።

ይህን የምንተነፍሰውን አየር መዋዕለ ንዋያቸውን ያፈሰሱበት ባለጠጎች ቢሆኑ ኖሮ ብንከፍል እንኳ እዘጋዋለሁ የሚለው ማስፈራሪያቸው በገደለን ነበር። እግዚአብሔር ግን በነጻ ሰጥቶናል። እግዚአብሔር ይህን በነጻ መስጠቱ ብቻ ሳይሆን ከሕይወት ጋር ተያያዥ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ በራሱ እጅ ማድረጉ ይደንቃል። ለሕይወት የሚጠነቀቅ እርሱ ብቻ ነውና። በእውነት አፋችን ምስጋና ሊሞላ ይገባዋል። ከጎደለን ያለን ይበልጣል። የተደረገልንን መቍጠር ስንጀምር ምስጋና ይበዛልናል። በሕይወት ዘመናችን የምንታዘበው ሰዎችን ብቻ ሳይሆን ራሳችንንም መሆኑ ይገርማል። በራሴ ሕይወት ዘወትር የሚገርመኝ ነገር ቢኖር ልመናዬ ብዙ ምስጋናዬ ግን ጥቂት መሆኑ ነው። እንደ ልመናዬ ስምስጋናዬ አልተጋም። አይሁዶች «ተቀብሎ የማያመሰግን ከቀማኛ ይቆጠራል» ይላሉ። ስለዚህ ይህ ቀማኛነቴ በታሰበኝ ቍጥር ንስሐ እገባለሁ።

ጸሎታችን መልስ ሲያጣ ሁለት ነገሮች ማድረግ አለብን። የመጀመሪያው ስለከለከለን ነገር እግዚአብሔርን ማመስገን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የራሳችንን ልመና ትተን እኛ በምናልፍበት የሕይወት ገጽታ ለሚያልፉ ሰዎች መማለድ መጀመር ነው። ያን ጊዜ መልሳችን ይፈጥናል። እግዚአብሔር ሥራህ ትክክል ነው ሲሉት ይወዳል። አባት ስንሆን ለሚሰምኑን ልጆቻችን የመራራት ተፈጥሮአዊ ጸጋ አለን። ስንከለክላቸው በሚያኮርፉ ልጆች ከማስረዳት እንበሳጫለን።



ዝርዝሩን ሳንናገር ጨክነን እንዳልከለከልናቸው እንዲያውቁልን ስለምንፈልግ ሳናስረዳ አይቻልም እንላለን። አንዳንድ ልጆች ደግሞ ስንከለክላቸው እንደ ቅድሙ ደስተኞች ናቸው። በዚህ ጊዜ ውስጣችን በርኅራኄ ይነካል። እግዚአብሔርም በደስታ ለሚያመሰግኑት ልጆቹ የፍቅር እጁን ይዘረጋል። አዎ ምስጋና የጸሎት የመጀመሪያው ክፍል ነው።

# ምዕራፍ ዐሥራ አራት

## ልመና

*«አብ ካልሰጠኝ ብዬ ምነው መናደዴ፣*
*ለወልድ አልነግርም ወይ? ለሥጋ ዘመዴ!»*

ጊዜው ርቋል:: ቢያንስ ፲ሥራ ስድስት ዓመት ይሆነዋል:: በክረምቱ ወራት ወደ ሰሜን ሸዋ የወዳጆቼ ዘመዶች ጋ በእንግድነት ተጋብዤ ሄድኩ:: በማግስቱ ጠዋት ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ማለድኩ:: በቤተ ክርስቲያኑ ደጃፍ ላይ ለማኙ ሣንቲሙን እያቃጨለ ግጥሙን ያወርደዋል:: ሣንቲሙን የሚያቃጭለው ለምን ይሆን? ብዬ ራሴን ጠየቅሁ:: «ሌሎችም የእኔ ጉዳይ አራርቷቸው ይኸው የምትሰማውን ሣንቲም ሰጥተዋል:: አንተም ራራ:: የመስጠት ጀማሪው አንተ አይደለህም» ማለቱ ይሆን? ብዬ ለራሴ መለስኩ:: የግጥሙን ቁምነገር ዛሬም ድረስ ሳስበው ምነው መቅረፀ ድምፅ በኖረኝ ያሰኛል:: ከግጥሙ አንዱ የታላቁ ጉዳዬ የመድኃኔዓለም ዜና ነበር:-

እብን ተወውና ንገረው ለወልድ፣
ተገርፏል ተሰቅሏል እርሱ ያውቃል ፍርድ!

ይላል:: ሰውን መለመንና እሺ ማስኘት የሚያውቅ ለማኝ እግዚአብሔርን መለመን በደንብ ያውቃል:: ለዚህ ለማኝ እግዚአብሔር ይታየዋል:: የሚመኩበት ነገር ለሌላቸው ምስኪኖች እግዚአብሔር ይታያልና:: ይህ ለማኝ ትምህርተ ክርስቶስን (ነገረ ሥጋዌን) በአጭር ቃል ገለጠው:: እግዚአብሔር ጸሎትን መስማት ብቻ ሳይሆን ችግራችን ይሰማዋል ማለቱ ነው:: ወልድ ሥጋ ለብሶ የሕይወትን ሕመም የኑሮን ቁስል አይቶልናል:: ዛሬ ጭንቃችንን ስንነግረው ያን ጊዜ በሥጋ ዘመኑ የደረሰበትን ሕመም ነው የሚያስታውሰው:: ሕመምን ሲነግሩት የሚሰማ ብቻ ሳይሆን የሚሰማው ጌታ ስላለን ልመናችን መጽናናት አለው:: በርግጥ የዚህ ለማኝ ግጥም የአገራችን ገበሬ የሚለው መሆኑን እስተውያለሁ:: የአገራችን ሰው ይህን ብቻ አይደለም የሚለው:-

አብ ካልሰጠኝ ብዬ ምነው መናደዴ፣
ለወልድ አልነግርም ወይ? ለሥጋ ዘመዴ!



በማለትም ነገረ ሥጋዌን ያደረድራል:: ይህን ግጥም ሳስብ ልቤ ይሸፍታል:: አንባቢ ሆይ! እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆኖ ኑሮአችንን እንዳየልንና የጸሎትን አስፈላጊነት ደግሞ ራሱ ጸልዮ እንዳሳየን ማስታወስ ያስፈልገናል:: የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆን ጸሎትን የማይሰበር ድልድይ አድርጎታል:: ስለ እኛ ያፈሰሰው ደምም ልመናችንን ፊት የማያስመልስ፣ አንገት የማያስቀልስ አድርጎታል:: *«ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም?»* (ሮሜ. 8÷32) እስክንል ትምክሕት ሆኖልናል:: ሳንለምነው አንድ ልጁን ሰጥቶናል:: እርሱ ከስጦታዎች በላይ የሆነ ስጦታ ነው:: ትልቁን የሰጠን በትንሹ አይጠረጠርም:: በዓለም ላይ የምንኖረው አንዱን አይተን አንዱን ረስተን ነው:: መልካሙን ሰው አይተን ክፉውን እያለፍን ነው የምንኖረው:: የምንወዳቸውን ሰዎች እያየን መልካም ያልሆኑ ቤተሰቦቻቸውን እናልፋለን:: የምንኖርበትና የልመናችንን መልስ የምንቀበልበት ምሥጢርም እግዚአብሔር ልጁን አይቶ እኛን የተወበት ምሥጢር ነው:: ከላይ የጠቀስናቸው የአገራችን ሰዎች ይህን ሁሉ የምሥጢር ባሕር ያስቀዝፋናል:: ጸሎት ከክርስቶስ ሕማምና መከራ ጋር ባጠቃላይ ከመሥዋዕትነቱ ጋር የማይለያይ ቊርኝት አለው::

የጸሎታችን የመጀመሪያው ክፍል ምስጋና ነው:: ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ልመና ነው:: የአቡነ ዘበሰማያት ጸሎት ከምስጋና ቀጥሎ ልመናን ያቀርባል:: *«የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን! ... ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን!»* ይላል (ማቴ. 6፥11፤ቊ.13):: ጸሎት ስለ እኛ ግድ ወደሚለው አምላክና «ለምኑ» ብሎ ወዳዘዘን ጌታ መማለል ነው:: ልመናን ስናነሣ የነቢዩ የዳዊት መዝሙር ልባችንን ይነካዋል:- *«በሰማይ የምትኖር ሆይ÷ ዓይኖቼን ወደ አንተ አነሣሁ:: እነሆ÷ የባሪያዎች ዓይኖች ወደ ጌታቸው እጅ እንደሆኑ÷ የባሪያይቱም ዓይን ወደ እመቤትዋ እጅ እንደሆኑ÷ እንዲሁ እስኪምረን ድረስ ዓይናችን ወደ አምላካችን ወደ እግዚአብሔር ነው»* (መዝ.122/123/÷1-2)::

የዛሬውን ትተን የጥንት አገልጋዮችን ስንመለከት ሰው ለሰው የተገዛውን ያህል ሰው ለእግዚአብሔር አለመገዛቱ ሳይገርመን አይቀርም:: በዚያ ዘመን አንድ አገልጋይ የአንድ ጌታ ነው:: ለጌታው ሠራተኛ ብቻ ሳይሆን ጠላት ከመጣም ከጌታዬ በፊት ብሎ የሚሞት ወታደርም ነው:: መኝታውን ሲዘረጋ ከጌታው ግርጌ፣ ድንኳኑንም ሲተክል ጌታውን ከብቦ ነው:: የራሱ የሆነ ጥሪት ወይም ሀብትና ንብረት የለውም:: የጌታውን ንብረት የራሱ አድርጎ የሚኖር ነው::

የኮንትራት ሠራተኛም አይደለም:: በዘመኑ ሁሉ ጌታውን የሚያገለግል ነው:: የተሰጠውን ያደራጃል እንጂ ጌታዬ ከየት ያመጣል? የሚል ስጋት የለውም:: ጌታውም ሲራራለት ንብረት ሰጥቶ ኵሉ ድሮ እግቢው ያኖረዋል:: ብቻ ጌቶቹ ያን ያህል ታማኝ ባይሆኑም ከባሮቹ ግን ልዩ መታመን ነበረ:: በጌታቸው ስም ይምላሉ:: ከጌታዬ በፊት ብለው ይሞታሉ:: እነዚህ አገልጋዮች ለክፉ ጌቶቻቸው ያደረጉትን ያህል እኛ ለመልካሙ ጌታ ብናደርግ የጸሎት ሕይወትና የመንፈሳዊ ኑሮ ትርጓሜ ይገባን ነበር:: ያች የድሮ አገልጋይ የእመቤትዋን ድምፅ ልትሰማ በምትችልበትና የጣደችው ሲያርር ልታሸት በምትችልበት ርቀት ተቀምጣ በንቃት ትሠራለች፡፡ ብዙ ሠርታ ጎሽ አትጠብቅም:: ግዴታዋን እንደተወጣች ይሰማታል:: ደሞዝተኛ አይደለችም፣ ይገባሻል የተባለችውን ለመቀበል ግን ዝግጁ ናት:: እመቤቷ ምን ጎደለ? እንድትላት የእመቤቷን ዓይን እያፈረች በቅዱስ ፍርሃት ትቆማለች:: እመቤቷም ለጋራ ቤታቸው የምትለምነውን ለማሟላት የደጅ ሰው በማያያቸው ጓዳ ውስጥ ስለማብቃቃት እየተመካከሩ ይሰፈርላታል:: ነቢዩ በፊቱ የሚቆሙትን አገልጋዮች አሰበና የእርሱና የጌታው ግን ኙነት ፊቱ ላይ ድቅን አለበት:: ባሪያ ቢቸግረው ጎረቤት አይሄድም:: ጌታው እንዳረገው ይሆናል:: ትዳሩም ጎረቤቱም ጌታው ነው:: ዳዊትም ሌላ አምላክ አላይም እስክትምረኝ እንተን እያለሁ እያለ ነው ያለው:: ጸሎት እግዚአብሔርን ብቸኛ አማራጫችን አድርገን የምናከናውነው ነው::

«ለምኑ» ብሎ እንድንጸልይ ያዘዘን ራሱ እግዚአብሔር ነው:: ጸሎት «አትስረቅ» «አትግደል» የሚሉትን ትእዛዛት ያህል ልንፈጽመው የሚገባ ትእዛዝ ነው:: ስለዚህ አለመጸለይ ኃጢአት ነው:: አንድ ንጉሥ ጋ ቀርቦ «የምትፈልገውን ለምነኝ እሰጥሃለሁ» የተባለ ሰው «ንጉሥ ሆይ የምፈልገው ምንም ነገር የለኝም» ቢል ከጨዋነት አይታይለትም:: የንጉሡን ቸርነት እንደ ናቀ ተቆጥሮበት ይቀጣል:: ይህ በአገራችንም ይደረግ የነበረ ልማድ ነው:: ንጉሥ ምን ልስጥህ? ሲል ለክብሩ አንድ ነገር ይጠየቃል እንጂ እንቢ አይባልም:: ዛሬም ንጉሡ እግዚአብሔር ለምኑ ብሎን ሳለ አለመለመናችን ቅጣት አለው::

የብዙ ችግሮቻችን ምንጩ ለማማረር፣ ሌሎችን ለመውቀስ መትጋት ለመጸለይ ግን መስነፍ ነው:: እግዚአብሔር ብዙ በጎ ነገሮችን ሊያደርግልን ይፈልጋል፤ እስክንጸልይ ግን ዝም ይላል:: በሕይወት ላይ ከሰዎች ጋ ያለንን ክርክር ከሚቀንሱ ነገሮች አንዱ «እግዚአብሔር ሰጥቶ የሚከለክለን፣ እግዚአብሔር ነሥቶንም የሚሰጠን እንደሌለ» ስናምን ነው:: እዚያ ጋ ያኛው ሰውዬ የያዘው የእኛን በረከት ስለሚመስለን ሳናውቀው በቅንዓትና በምቀኝነት እንያዛለን:: ስለዚህ



ጠብና ክርክር የበዛበት ኑሮ እንኖራለን:: ያዕቆብ በመልእክቱ:- *«በእናንተ ዘንድ ጦርና ጠብ ከወዴት ይመጣሉ? በብልቶቻችሁ ውስጥ ከሚዋጉ ከእነዚህ ከምቾቶቻችሁ አይደሉምን? ትመኛላችሁ ለእናንተም አይሆንም፤ ትገድላላችሁም በብርቱም ትፈልጋላችሁ፥ ልታገኙም አትችሉም፤ ትጣላላችሁ ትዋጉማላችሁ ነገር ግን አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም፤»* (ያዕ. 4፥1-2) ይላል::

የጦርና የጠብ ምንጩ ምንድነው? ስንል የእኔን ገንዘብ፣ የእኔን ድንበር ነካህብኝ የሚል ቁጣ እንጂ ከእኔ እኩል እንዴት መንግሥተ ሰማያት ትገባለህ? የሚል አይደለም:: ውስጣችን የሚፈልገው ምቾት አለ:: ያ ምቾትም ሰዎች ሁሉ ከበታቼ ተደልድለው እኔ ከበላያቸው ልቀመጥ የሚል ነው:: የበላይነትን ለማስከበር በዘመኑ አነጋገር «ተጽእኖ ማምጣት የሚችል ሰው» ለመሆን የእውቀትን፣ የገንዘብንና የሥልጣንን አቅም ማጠናከር ግድ ነው በማለት ኀሊና አሳብ ያቀርባል:: ሌሊትና ቀንም የሌሎች እሴት የእኔ ይሁን የሚል የምኞት ፍልሚያ ይጀመራል:: ምኞት በእጭሩ ካልተቀጨ ወይም ካልተገሰፀ ተግባርን ይወልዳል:: የምንመኘውን የያዘብን የሚመስለንን ሰው መጥላት ቀጥሎም ለሞት መመኘት እንጀምራለን:: ከዲያብሎስ የፍርድ መጽሐፍ ውስጥ የተወሰዱ ጥቅሶችን ለራሳችን መጥቀስ እንጀምራለን:: «ካልገደልህ አትኖርም» «ትልቅ ዓሣ ሁንና ትንሹን ዓሣ ዋጠው» «አንዱ ጉሮሮ ላይ ካልቆምህ አትበላም» የሚሉት ክፉ ጥቅሶች በውስጣችን መመላለስ ሲጀምሩ ድፍረት እያገኘን እንመጣለን:: ገድሎ መኖር እንደማይቻል ማሰብ እስኪያቅተን ዓለም የእኛ ብቻ ጫካ መስላ ትታየናለች:: የጦር መሣሪያ ይዘን፣ ወሬ ሰብቅ አንግበን፣ በሐሰት ከሰን አስፈርደን፣ ፈርመን ተፈራርመን ወንድማችንን እንገድላለን:: ውጤቱ ግን በወኅኒ መጣል ይሆናል:: በወኅኒ ባንጣል እንኳ በኅሊና ወኅኒ ቤት ውስጥ እንገባለን:: የምንሻውን በመቀማት ወይም በመግደል ሳይሆን በጽድቅ እንድናገኘው እግዚአብሔር ባዘጋጀልን የጸሎት መስመር አንጠቀምም:: ለዚህ ነው ያዕቆብ *«. . .ነገር ግን አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም!»* (ያዕ. 4፥1-2) ያለው:: አለመለመን በራሱ ኃጢአት ነው:: ከዚያ ባሻገር ወደ እቋራጭ መንገድም እየመራ በጠብና በቅጣት ያኖረናል::

ያልሠራበትን የሚጠይቅ ሠራተኛ፣ ያላስቀመጠውን አምጡ የሚል ጤነኛ ሰው የለም:: በጸሎት ግን ያልሠራንበትንና ያላስቀመጥነውን እግዚአብሔር ሆይ ስጠን እንላለን:: እንደውም ወደ ጸሎት ጥልቅ ምሥጢር ስንገባ እግዚአብሔር ሊሰጠን የሚፈልገውን ነገር አስቀድሞ ያጸልየናል:: ስለዚህ ልመናውም መልሱም የእግዚአብሔር ሆኖ እናገኘዋለን:: የእግዚአብሔር ስጦታ የማያሳቅቅ፣

ሊከፍሉት የማያሳስብ መሆኑን ሳስብ ዘወትር እነካሰሁ:: ስጦታ ዕዳ ባይሆንም የሕሲና ዕዳ ነው:: የእግዚአብሔር ስጦታ ግን የራስ ያህል የሚሰማ ነው::

ልመና ብዙ ቅርፆች አሉት:: ወደ ጸሎት ምርምር ስንገባ የልመና ዓይነቶች ዐሥራ ሁለት እንደሆኑ እንረዳለን::

1. መጠየቅ
2. ማስፈቀድ
3. ግድ ማሰት
4. መማፀን
5. መማሰል
6. መማሰድ
7. ማዘዝ
8. ስእሰት
9. ዝምታ
10. ጩኸት
11. አቤቱታ
12. የኀሲና ጸሎት ተብሰው ይጠራሉ::

## መጠየቅ

«ጌታ ሆይ ይህን አድርግልኝ» የሚል ተሰማማጭነት ያሰበት የጸሎት ዓይነት ነው:: በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ የእግዚአብሔር ሰዎች እግዚአብሔርን የመጠየቅ ልማድ ነበራቸው (1ሳሙ. 23÷6-13):: አገርን የሚወርር ጠላት ሲመጣ እንኳ ስልትና የክተት አዋጅ ከመንገራቸው በፊት እግዚአብሔርን እንውጣ ወይ? ብሰው ይጠይቁ ነበር:: እግዚአብሔር ባልቀደመበት ነገር ሽንፈት እንጂ ድል የሰምና «እንውጣን?» በማሰት ይጠይቁ ነበር:: እነዚህ ሰዎች ከመመሪያዎቻቸው ይልቅ እግዚአብሔርን በመጠየቅ ያምኑ ነበር:: ብዙ ጊዜ መልካም ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው ብሰን ስሰምናምን በጎ የሚባል ወይም የምንፈልገው ዕድል ሲመጣ ከመጸሰይ ይልቅ ተሽቀዳድመን መያዝ ነው የምንፈልገው:: ሰእኛ የተዘጋጀው ነገር ግን ዓሰም ሳይፈጠር በፊት የተሰናዳ በመሆኑ እስክንጸልይ የሚያልፈን አይደሰም:: ማንኛውም ትልቅ ዕድል ቢመጣ አገልግሎትም ቢሆን ቢያንስ አምስት ደቂቃ ሰመጸሰይ ጊዜ ያስፈልገናል:: ከእግዚአብሔር የሆነ እስክንጸልይ አይሄድም:: ከሰይጣን የሆነው ወርቅ የሚመስሰው ድንጋይ ግን የጸሎትን ጋሻ ስንጥል መትቶ ይጥሰናል:: ስሰዚህ ጌታ ሆይ በዚህ ነገር አሰህበትን? በሌሰህበት ነገር ውስጥ ከመትጋት



አድነኝ:: ያሳንተ መሰብሰብ መበተን ሆኖብኛል እያልን መጠየቅ አንዱ የጸሎት ክፍል ነው::

ሙሴ ከጸሰየው አስደናቂ ጸሎት አንዱ:- *«አንተ ከእኛ ጋር ካልወጣህስ÷ ከዚህ አታውጣን:: በምድር ፊት ካለው ሕዝብ ሁሉ እኔና ሕዝብህ የተሰየን እንሆን ዘንድ አንተ ከእኛ ጋር ካልወጣህ÷ እኔና ሕዝብህ በአንተ ሞገስ ማግኘታችን በምን ይታወቃል?»* (ዘፀ. 33÷15-16) የሚሰው ነው:: ጉዞ አሰ:: ማሽነፍ አሰ:: መና አሰ:: ውሃ አሰ:: እግዚአብሔር ግን የሰም:: ይህ ሲያስቡት እንኳ ይከብዳል:: ሀብት ያሰው ትዳር፣ ሽልማት የተሰጠበት እውቀት፣ ቆንጆ ልጆች፣ የሚከተል ብዙ ሕዝብ፣ ዲፕሎማሲያዊ ድል፣ ታላቅ ጀግንነት. . . ቢኖርና እግዚአብሔር ግን ባይኖርበት ከባዶ ቤት፣ ከተወረረ ከተማ፣ ከመቃብር ስፍራ፣ ፍቅር ከሌሰበት መተቃቀፍ በላይ ያስፈራል::

## ማስፈቀድ

«ጌታ ሆይ ይህ አሰኝ ይህን እንዳደርግ ፍቀድልኝ» የሚል የፍጹም ተገዢነት ጸሎት ነው:: ወታደር ቤተሰቡን የመጠየቅ ሕጋዊ መብት አሰው:: ግን አሰቃውን ያስፈቅዳል:: ሠራተኛ ዕረፍቱን የመጠቀም ሕጋዊ መብት አሰው:: መብቴ ነው ብሎ ግን እቤቱ አይቀርም:: አሰቃውን ያስፈቅዳል:: ልጅ የመጫወት መብት አሰው:: ነገር ወላጆቹን ያስፈቅዳል (የድሮ ልጅ):: ክርስቲያንም ማድረግ በማይችሰው ነገር ብቻ ሳይሆን ማድረግ በሚችሰውም እግዚአብሔርን ያስፈቅዳል:: እግዚአብሔር ሰእርሱ የጦር መሪው፣ የሥራው አስኪያጅ፣ የወሰደው አባቱ ነው:: ሰው ሰሰው የሚያደርገውን ያህል ሰው ሰእግዚአብሔር አላደረገም:: የማስፈቀድን ጸሎት በሕይወታቸው የተሰማመዱ ሰዎች ጥቂቶች ናቸው:: ማድረግ መቻል ግን አያረካም:: እግዚአብሔር ጣዕም ሲሰጥ ብቻ እርካታ አሰ::

«እግዚአብሔር ሆይ የሰጠኸኝ ይህ ነገር አሰ፤ ፈቃድህ ከሆነ ላድርገው ካልሆነ ጊዜዬን መሻቴን እንዳልከስር ከልክሰኝ:: ሰገዛ ፈቃዴ አሳልፈህ አትስጠኝ» እያልን መጸሰይ ይገባናል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ትልቅ ቅጣት እግዚአብሔር ሰገዛ ፍላጎታችን አሳልፎ ሲሰጠን ነው (ሮሜ. 1÷24 .26 .28):: ገበሬ ምንም ሳይነቅል ማሳውን አላየውም ከዛሬ ወዲያ በቃኝ ብሎ ሰራሱ ቢተወው የማይበቅልበት አረም የሰም:: እግዚአብሔርም ከነሙሉ ደሞዛችን፣ ከታፈረው ትዳራችን ጋር እንኳ ሰራሳችን ቢተወን የማይበቅልብን ነውር የሰም:: ሰራሳቸው የተተዉ ስንት ምእመናን፣ ስንት ቀሳውስት፣ ስንት ጳጳሳት ነውራቸው

ተዘርዝሮ የማያልቅ የጉድ ሙዳይ ሆነው የለምን? እግዚአብሔር አይልቀቀን እንጂ ከለቀቀን ምናችንም አያምርም:: እዎ የልመና አንዱ ክፍል ማስፈቀድ ነው::

## ግድ ማለት

ይህ ልመና ከራሳችን ባሻገር ስለ ወገናችን፣ ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ አገራችን ጌታ ሆይ እባክህ ይህን አድርግ ብለን ሙጥኝ የምንልበት የጠባብ ቀን ጸሎት ነው:: ልጆች የሚፈልጉት እስኪሆን ግድ የሚሉበት «የምፈልገውን እስክቀበል አልመለስም» ብለው የቆረጡ የሚመስሉበት ጊዜ አለ:: በታሪክም የሚታወቁ ብዙ የነገሥታት ሚስቶች ወይም እቴጌዎች ለንጉሡ የሚበጀውን ቍርጥ ልመናን በማቅረብ ንጉሡንና ወገናቸውን ሲያድኑ እናነባለን:: እንዲሁም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ብርቱ የሆነ ልመና አለ:: ይህ ልመና እግዚአብሔርን ያለ ፈቃዱ አስገድደን የምንቀበልበት ሳይሆን በፈቃዱ መሠረት እኛን የሚለመንበት ነው::

ይልቁንም በጭንቀትና በሚደጋግም የኃጢአት ውድቀት ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ እግዚአብሔርን ግድ እንለዋለን:: ከጎስቋላው ሰውነት እንዲያድነን በብርቱ እንጮሃለን:: ኤልያስ የብቸኝነት ጩኸት፣ ጳውሎስ የቅድስና ጩኸት እንዳሰሙ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (1ነገሥ. 19፥4-8፤ ሮሜ. 7፥13-25):: ይህ ጊዜ የማይሰጥ ጉዳይ በመሆኑ የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ጮኸዋል:: እንዲሁም በወገን ላይ ብርቱ መከራ ሲመጣ እግዚአብሔርን ግድ እንለዋለን:: ለምነን መልስ ብናጣ እንኳ ስለሞከርን ብዙ አንጸጸትም:: የሚቀጣው ቢቀጣ እንኳ ባለማወቅ የሚቀጣውን እናድናለን:: ቀጣይ መቅሰፍትን እናቆማለን:: ዳዊት በችነፈር ሰባ ሺህ ሕዝብ ባለቀበት ጊዜ ለእኔ ይሁን ብሎ በመጸለዩ መዓቱ ተመለሰ (2ሳሙ. 24.):: ዛሬ በምድራችን ላይ በሚደርሰው መከራና ስቃይ የእኔም ኃጢአት አለበት ብሎ የሚያስብ ሰው ይኖር ይሆን? ነቢዩ ሙሴ እስራኤል በበረሃ ከሚቀሩ እኔ ከሕይወት መጽሐፍ ልደምሰስ ብሎ በታላቅ የመሥዋዕትነት ፍቅር ጸልዮአል (ዘፀ. 32፥32)::

ቁርጥ ልመናዎች ብርቱ ኃይል አላቸው:: በእንብርክክ እየሄድን ዕንባን እንደ ጅረት እያፈሰስን ያስቀስንባቸውን ቀኖች አንረሳቸውም:: የማንረሳቸው ጥልቅ ጸሎት ትዝታ ስላለውና እግዚአብሔርም ፈጣን መልስ ስለ ስጠን ነው:: እግዚአብሔር ሁልጊዜ ፈጣን መልስ ሊሰጠን ይፈልጋል:: ነገር ግን ቍርጥ ልመናን



ይፈልጋል:: ቍርጥ ልመናዎች ብዙ ጊዜ ከራሳችን ባሻገር ስለ ወገን የሚቀርቡ ናቸው::

## መማጸን

ይህ ልመና እግዚአብሔር እንዲያስጠጋን ከችግሩ ውጤት እንዲያድነን በእንባና በምስኪንነት መንፈስ የምናቀርበው ነው:: የሰው ልጅ ኃጢአቱን እየሳቀ ቢያደርግ ውጤቱን ግን እየሳቀ መቀበል አይሆንለትም:: ታዲያ ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ ሲማጸን እግዚአብሔር ይራራለታል:: እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን ለነበሩት እስራኤላውያን በየከተሞቹ አቅራቢያ የመማጸኛ ከተማ አድርጎላቸው ነበር:: ነፍስ ገድሎ ሸሽቶ የሚሮጠው በመማጸኛ ከተማ ውስጥ ከገባ በኋላ ማንም አይበቀለውም ነበር:: ሊቀ ካህኑ በሕይወት እስካለ በመማጸኛው ውስጥ በሰላም ይኖር ነበር:: በአገራችንም ባሕል ጥፋት ያጠፋ ሰው የሚማጸነው ሰው አጥቶ ዛፍ እንኳ ቢማጸን ባላጋራው አይነካውም:: ተማጽኖ ሳለ ባላጋራው ቢበቀለው ታላቅ ነውር እንደሠራ ይቆጠርበታል:: ነውሩም ተሰምቶ በገበያ የሚሸጥለት በጎረቤት ሰላም የሚለው አያገኝም ነበር:: ምክንያቱም የተማጸነ ሰው ሕግ ሳይከሰው ራሱን ከስሷል:: በሥራውም አፍሯል:: አዳኝም ፈልጎ ሙጥኝ ብሏል:: ስለዚህ አይነካም:: ቤተ ክርስቲያን የተደበቀም ንጉሥ ቢፈልገው እንኳ ተላልፎ አይሰጥም:: በውትድርና ዓለምም እጁን ወደ ላይ ያለ ምርኮኛ አይነካም:: ምርኮኛ ገድሎ ማዕረግ የሚያገኝ ወታደር በፍጹም የለም:: ሰው ከተሸነፈ በኋላ በእርሱ ላይ ጀግና ልሁን ማለት በምድር በሰማይ ያስወቅሳል:: እግዚአብሔርም ከሦስት ሺህ ዓመት በፊት ለእስራኤል የመማጸኛ ከተማዎችን እንዲሠሩ አዘዘ (ዘኁል. 35፥9-13)::

የምንኖርበት ዓለም ብዙ አባራሪ ያለበት ዓለም ነው:: ሐሊና፣ የበደልናቸው ሰዎች፣ በቅንዓት ተነሣስተውብን ያሳድዱናል:: አባረህ ያዘው የሚል በበዛበት ዓለም እግዚአብሔር ትልቅ የመማጸኛ ከተማ ሠርቶልናል:: እርሱም ጸሎት ነው:: «ጌታ ሆይ የገዛ ሐሊናዬ ባላጋራ ሆኖብኛል:: ይህን አሳብ መተው እፈልጋለሁ:: ግን አቅቶኛል:: ከራሴም ሆነ ከሚያሳድዱኝ ሸሽገኝ» እያልን የምናቀርበው የልመና ዓይነት የመማጸን ጸሎት ይባላል::

## መማለል

ይህ ልመና እጅን እያርገበገቡ፣ ወገብን በአጭር ታጥቀው፣ በጉልበት እየሄዱ፣ ዋይታ በማሰማት ድረስልን ብለው የሚሰምኑበት የልመና ዓይነት ነው:: ወላዶች፣ በማስተዋል የበለጸጉ ሽማግሌዎች፣ በረከት ያላቸው አባቶች በአገር በወገን ላይ የመጣውን ክፉ ነገር ማየት አንችልም እባክህ አርቅልን ብለው ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡት ጸሎት ነው:: አንጀታቸው ቀጭኑ የሆነ፣ ርኅራኄ ቶሎ የሚሰማቸው ሰዎች ስለመጣው ብቻ ሳይሆን ሊመጣ ስላለውም መዓትና መከራ በጉልበት እየዳሁ፣ በደረት እየተሳቡ እንባቸውን እየረጩ አቤት አቤት የሚሉበት ጸሎት መማለል ይባላል:: በአገራችን እንዲህ ያለው ጸሎት መቅሰፍት ሲመጣ፣ ወራሪ ሲመጣ ኅበዙ ሲፎክር ኃይል ያንተ ነው እባክህ አርቅልን ብለው አስተዋዮች የሚያቀርቡት ጸሎት ነው:: እግዚአብሔርም በእውነተኛ መመለስ በታላቅ ተማጽኖ ወደ እርሱ የሚቀርበውን ምህላ ሰምቶ ፈጣን መልስ ሲሰጥ አይተናል:: በአገራችን በተደጋጋሚ በሚነሡት የእርስ በርስ ግጭቶች መፍትሔው ጸሎት እንደሆነ በሚናገር አንድ ስብሰባ ላይ አስተባባሪዋ እናት፡- «ወገኔ በአደባባይ ደሙ ፈስሶ፣ እርስ በርሱ ሲተላለቅ ቆሜ ማየት አልችልም:: ያንን ማየት ስለማልችል ነው ዛሬ አቤት የምለው» ስትል ሰምቻለሁ::

## መማለድ

ይህ ጸሎት ስለ ሌሎች ወገኖች ጉድለት እግዚአብሔርን እዘንላቸው እራራላቸው ብሎ የመጠየቅ የፍቅር ጸሎት ነው:: እግዚአብሔር የእኛን ችግር ከመስማቱ በፊት የጎረቤታችን ችግር ምን ያህል እንደሚሰማን ማየት ይፈልጋል:: እርሱ ለእኔ ለእኔ የሚል ጸሎትን አይወድም:: ስለ ሌሎች የምናቀርበውን የምልጃ ጸሎት መስማት ይፈልጋል:: የምልጃ ጸሎት ፈጣን መልስ ሲኖረው ለእኛም ትልቅ በረከት አለው:: ስለ ሌሎች በመጸለያችን ለእኛ አይጎድልብንም:: እግዚአብሔር ለእናንተ ጉድለት ደግሞ እኔ አለሁ ይላል::

አንድ ወንድሜ ሁልጊዜ «ወደ ላይ ፋክስ አድርግልኝ» ይለኛ ል:: ምን ማለቱ እንደሆነ ዘግይቶ ነው የገባኝ:: ለካ ጸልይልኝ ማለቱ ነው:: ፋክስን ሳስብ እጅ ጽሕፈታችንና ፊርማችን ሳይቀር እንዳለ ግልባጭ ሆኖ ሩቅ ቦታ ካለው ደንበኛችን ዘንድ የሚደርስ ነው:: ስለ ሌሎች የምንጸልየውም እንዲህ ግልባጭ ሆኖ በሥላሴ ዙፋን ፊት ሲቀርብ እግዚአብሔር «ስለ እኔ ልጅ ይህ ሰው እንዲህ ከተሰማው



እኔማ ከፍጡር ይልቅ እራራለሁ» ብሎ ለዚያ ሰው ሊያደርግለት ይንቀሳቀሳል:: ስለ ሌሎች የሚማልድ ጸሎት ከሌለን እግዚአብሔር ልጄ ምነው ብቻህን መጣህ የእኔ ቤት ሰፊ ነው ይለናል::

ድካሜን ባያውቁም ብዙ ወገኖቼ ጸልይልኝ ይሉኛል:: ታዲያ አንድ ምሽት አንድ አባት «ጸልይልኝ» ሲሉኝ ትሕትና የሚመስል ማጉረምረም ይሁን ብቻ አንድ ድምፅ ሳሰማ እኒያ መነኩሴ «ወንድሜ የጸሎት አንካሳ የለውም» አሉኝ:: አዎ ጸሎት ስለ ሰውዬው ማንነት ሳይሆን ጸልዩ ስላለው የተስፋ ቃሉ የሚፈጸም ነው:: የተቀባበሰ መሣሪያን ሕጻንም ቢተኩሰው አዋቂ ይገድላል:: ጸሎትም ደካማውም ሆነ ብርቱ ቢጸልየው ይሠራል:: አዎ የልመና አንዱ ክፍል ስለ ሌሎች መማለድ ነው::

## ማዘዝ

ይህ ልመና ለእገሌ ይህ ይገባዋል ብሎ የመፍረድ ጸሎት ነው:: እግዚአብሔር ከቃሉ ጋር ስንስማማ ከቃላችን ጋር ይስማማል:: ለሌሎች ወገኖቻችን በፍቅርና በርኅራኄ ሆነን ጌታ ሆይ ከእንግዲህ ወዲህ መገፋቱ ይበቃል ስንል እግዚአብሔር ቃላችን ላይ ያትማል:: የረሀቡ ዘመን ይለፍ ከእንግዲህ ወዲህ የእርሱን ጭንቅ አላይም እኔም ከእርሱ ጋር አምጣለሁ እኔን ማረኝ ስንል እግዚአብሔር ይሁን ይላል:: በጣም በምንወዳቸው ወዳጆቻችን ንብረት ላይ እናዝዛለን:: የምናዝዘው ግን ከእኛ ይልቅ ያ ወዳጃችን ለሚቀርበው ለልጁ ወይም ለወንድሙ እንዲያደርግ የምናስተላልፈው የውሳኔ ቃል ነው:: ይህን የምናደርገው ፍቅር ሥልጣን ስለሚሰጠን ነው:: እግዚአብሔር በቃሉ *«ስለሚመጣው ነገር ጠይቁኝ፥ ስለ ልጆቼና ስለ እጄ ሥራም እዘዙኝ»* (ኢሳ. 45፥11) ብሏል:: የማዘዝ ጸሎት የሚያቀርቡ ሰዎች ማዘዝ የልመና ዓይነት መሆኑን አጥንተው ሳይሆን በውስጣቸው ካለው መንፈስ ቅዱስ ጋር ተማክረው የሚቆርጡ ናቸው:: ይህን ጸሎት ለማድረስ ከእግዚአብሔር ጋር መላመድ ያስፈልጋል:: ምክንያቱም እንዲህ ያለውን ሥልጣን የሚሰጠን ፍቅር ነውና::

## ስእለት

ይህ የልመና ዓይነት እግዚአብሔር ለሚያደርግልን ነገር ለምስጋናው መታሰቢያ ይህን አደርጋለሁ የሚል ለውለታው ዋጋ የሚሰጥ ጸሎት ነው:: እግዚአብሔር እንዲሰጠን የምንጠይቀውና አመጣለሁ የምንለው አይመጣጠንም:: የስእለት ዓላማው ግን የእግዚአብሔርን ውለታ ማሰብ ነው:: ሰዎች አስልተው ዐሥር ሺህ

ብር ብትሰጠኝ አንድ ሺህ ብር አመጣለሁ ይሉ ይሆናል። ስእለት ግን ቅዱስ እንጂ ሰው ከፈጣሪው ጋር ሎተሪ የሚጫወትበት አይደለም። የምታደርግልኝን ላልረሳው ይህን አደርጋለሁ እንላለን። ስእለት ግዴታ አይደለም። ከተሳልን ግን ለስእለት አምላክ የመፈጸም ግዴታ አለብን። ስንሳል ግን ልናደርገው የምንችለውን እንጂ አይሆንም በሚል ጥርጣሬ ያለ አቅማችን መሳል መልሶ ጭንቀት ውስጥ ይከተናል። ስእለታችንን ተሰሚ የሚያደርገው የስጦታው ማነስና መብዛት ሳይሆን ቃል ኪዳናችን ነው። የእናንተን አላውቅም በሕይወቴ ለስእለት አምላክ ተስዬ ይዤ ስሄድ የሚሰማኝ ደስታ በቃላት ልገልጠው አልችልም። የተደረገልኝ ሰው ነኝ የሚል ስሜት ውስጤን ያቀጣጥለዋል። ታዲያ ስእለትን ስንሳል ሁለት ጥንቃቄዎች ያስፈልጋሉ። የመጀመሪያው በአቅማችን መሳል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የተሳልነውን በጊዜ መፈጸም ናቸው። ጠቢቡ ሰሎሞን፡- *«ሰነፎች ደስ አያሰኙትምና ለእግዚአብሔር ስእለት በተሳልህ ጊዜ ትፈጽመው ዘንድ አትዘግይ፤ የተሳልኸውን ፈጽመው። ተስለህ የማትፈጽም ብትሆን ባትሳል ይሻላል»* (መክ. 5፥4-5) ብሏል።

## ዝምታ

ይህ የልመና ዓይነት ያለ ቃላት በፀጥታ በእግዚአብሔር ፊት የምንሆንበት፣ ልባችንም ከቃላት ውጭ ሆኖ ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ መሆንን የሚፈልግበት የጸሎት ዓይነት ነው። ልጆች ከአባቸው ጋር ያለ ልመና በፀጥታ መሆን የሚፈልጉበት ጊዜ አለ። የሚፈልጉት ምንም ነገር የለም። አባታቸው አጠገብ መቀመጥ ከአባታቸው ጋር መሆን ብቻ ይፈልጋሉ። ያለ ንግግር በዝምታ ከአባታቸው ጋር የሚሆኑበት ጊዜ ጥልቅ ፍቅር የሚሰማቸው ወቅት ነው። ምእመንም ከእግዚአብሔር ጋር በዝምታ የሚቆይበት ጊዜ አለ። በአንደበቱና በልቡ ምንም የጸሎት ቃላት የሉም። ግን ከእግዚአብሔር ጋር መሆንን ብቻ ይፈልጋል። ከእግዚአብሔር የፍቅር ሙቀት የከዳተኛዋን ዓለም ብርድ ለማስወገድ፣ በአባትነቱም መዓዛ ይህን ዓለም ለመርሳት ይፈልጋል። በዝምታ ከእግዚአብሔር አጠገብ መቀመጥ የልመና አንዱ ክፍል ነው። ጸሎት ከልማድ ወጥቶ ናፍቆት ሲኖረው ደስታ አለው። በጣም የናፈቀንን ሰው ስናገኘው ቃላት አጥተን ዝም ብለን መመልከት ብቻ ይቀናናል። ፍቅር በዝምታ ውስጥ እንኳ ይግባባልና አፍቃሪያችን ይረዳናል። ነቢዩ ዳዊት፡- *«አምላኬ፥ አምላኬ፥ ወደ አንተ እገሠግሣለሁ፤ ነፍሴ አንተን ተጠማች፥ ሥጋዬ አንተን እንዴት ናፈቀች»* (መዝ. 62፥1) ያለው ለዚህ ነው።



## ጩኸት

ይሉኝታ የሌለው ድረሱልኝ የሚል ኡኡታ እሪታ በእግዚአብሔር ላይ ፍጹም ራስን የመጣል አልቻልኩም የሚል ፈጣን ምላሽ የሚፈልግ ጸሎት ነው። ጩኸት የሚያሰሙ ሰዎች ከቤታቸው ወጥተው በደጃፋቸው ቆመው ማንም ቢሆን ይድረስልኝ አሁን ከገጠመኝ ነገር ያድነኝ የሚል ሰሚውን ሁሉ የሚያራራና የሚያፈጥን ድምፅ ያሰማሉ። ጸሎት ጥልቅ ከሚሆንባቸው ነገሮች አንዱ ጩኸት ሲሆን ነው። ጸሎትን በጩኸት መልክ የምንጸልይበት ጊዜ ጥቂት ነው። ጸሎት ጩኸት ሲሆን ግን ለሰማኙ እርካታ አለው። ለሰሚው ደግሞ የሚያራራ ነው። እንዲህ ያለ ጸሎት የሚጸለይበት ጊዜ ጥቂት ነው። ጎናችን ሲሰበር፣ የመቆም ኃይላችን ሲከዳን፣ የምንሰማውንና የምናየውን መቋቋም ሲከብደን የጩኸት ጸሎት እናቀርባለን። ይህ ጸሎት ብርቱ እንደሆነ አውቃለሁ። በመሬት ላይ እየተንደባለሉ እንደሚጮሁ ሕጻናት በእግዚአብሔር ፊት እየወደቁ እየተነሡ የሚጮሁ ምእመናን እግዚአብሔርን ዘንበል ያደርጉታል። ነቢዩ፡- *«ይህ ችግረኛ ጮኸ፥ እግዚአብሔርም ሰማው፥ ከመከራውም ሁሉ አዳነው»* (መዝ. 33፥6) ብሏል። ለዚህ በርጤሜዎስን ማሰብ ይበቃል (ማር. 10፥46-52)።

## አቤቱታ

ይህ የልመና ዓይነት ፍርድን፣ የቅን ዳኝነትን ከእግዚአብሔር የምንጠይቅበት ጸሎት ነው። ብዙ ሰው እግዚአብሔር ቶሎ አይፈርድም ስለዚህ ያስጠቃኛል በማለት ጠንቋይ ቃልቻ ቤት ይሄዳል። አስፈርዳለሁ ብሎ ተፈርዶበት ይመጣል። እግዚአብሔር ግን ግፍን የማይታገሥ ለሁሉም እንደ ሥራው መስጠትን የሚያውቅበት የቅን ፈራጅ ነው። እርሱ ሲፈርድ ዐቃቤ ሕግ፣ ምስክር፣ የፖሊስ ማስረጃ አይፈልግም። የሁሉንም ስህተቱን በየግንባሩ ያነበዋል። በፍርዱም አያዳላም። በገንዘብ የሚበልጥ ባለጠጋ፣ በሥልጣን የሚበልጥ ኃይለኛ መግቢያ መውጫ ሲያሳጣቸው ለእግዚአብሔር አቤቱታ የሚያሰሙ ምእመናን አሉ።

እግዚአብሔር የሚሰጥ ባለጠጋ ብቻ ሳይሆን የሚፈርድም ንጉሥ ነው። የሰው ፍርድ አገር ለቀው ቢሄዱ ያመልጡታል። የእግዚአብሔር ፍርድ ግን ድንበር አያግደውም። ሰው ቢፈርድ በሥጋ እንጂ በነፍስ መፍረድ ስለማይችል ሰውዬው ሲሞት ክሱን ያነሣል። እግዚአብሔር ግን በነፍስ በሥጋ የሚቀጣ ጌታ ነው። ለእግዚአብሔር

የሚቀርብ አቤቱታ ከባድ ነው:: ክልመና ዓይነቶች አንዱ አቤቱታ ነው:: እግዚአብሔርን ዳኛ ማድረግ እንዴት ይልቃል!

## የኅሊና ጸሎት

አንደበት ሳይንቀሳቀስ ውስጣችን ግን ቃላትን እያዋቀረ የሚጸልየው ብርቱ የጸሎት ዓይነት ነው:: አንዳንድ ጊዜ ችግራችንን ለመግለጥ ቃላት እናጣለን:: ችግራችንን ብቻ አይደለም ምስጋናችንንም ለመግለጥ ቃላት የምናጣበት ጊዜ አለ:: ቃላት የሚገልጡት ጥቂት ነገሮችን ብቻ ነውና:: እግዚአብሔር ግን ለመጸለይ ቃላት ያጣንበትን ጉዳይ ከኅሊናችን አደባባይ ላይ ጸሎት ብሎ ይሰማዋል:: ስለዚህ ለመጸለይ ቃላት ስናጣ እንዳልጸለይን ሊሰማን አይገባም:: በመቃተት ሆነን በእግዚአብሔር ፊት እንጠባበቅ:: ሐኪም የምንነግረውን ብቻ አይደለም የሚያዳምጠው:: ሁኔታችንንም ይከታተላል:: በማዳመጫ ውስጣችንን ያዳምጣል:: ብቻ ተንፍሱ ይላል:: ከመተንፈስ ውጭ ቃላት አይጠይቀንም:: በትንፋሻችን እያዳመጠ ያክመናል:: እግዚአብሔርም ቃላት ባጣን ጊዜ በዝምታ ስንቃትት ውስጣችንን እያዳመጠ ያክመናል::

የልመና ዓይነቶች ዐሥራ ሁለት እንደሆኑ ለማየት ሞክረናል:: እኔ እንደደረስኩበት መገለጥ እንጂ ከዚያ በላይም ሊሆኑ ይችላሉ:: ነገር ግን ንውሳኑ ቢታለፉ እንጂ ዋና ዋና የልመና ዓይነቶች ተጠቅሰዋል:: ውድ አንባቢ ሆይ! እነዚህ የጸሎት ዓይነቶች የጸሎት ልምዳችን ውስጥ ያሉ እንጂ ዛሬ በዚህ የጸሎት ዓይነት ነው የምጸልየው ብለን የምንጠቀማቸው አይደሉም:: ጥልቀት ወዳለው የጸሎት ሕይወት ስንገባ ሁሉንም ሳናስባቸው እናደርጋቸዋለን:: ብቻ ጸሎት ልምምድ ነው::



# ምዕራፍ ዐሥራ አምስት

## ንስሐ

*«ማግኔት ተቃራኒውን እንዲስብ እግዚአብሔርም ቅዱስ ሳለ ኃጢአተኞችን ያቀርባል:: የብርሃን ባሕርይው ማራቆት ነው:: እግዚአብሔር ግን የሚሰውር ብርሃን ነው::»*

የጸሎት ሦስተኛው ክፍል ንስሐ ነው:: ልብሳችን በምን ሰዓት እንደ ቆሸሸ በትክክል መናገር እስከማንችል ድረስ ቆሸሾ እናገኘዋለን:: ሰውነታችንም እንዲሁ መቼ፣ እንዴትና የት ቦታ እንደ ቆሸሸ በውል ማወቅ እስኪያቅተን በኃጢአት ረክሶ እናገኘዋለን:: ዛሬ ንጹሕ ነኝ በምንልበት ቀን እንኳ ቆሻሻዎች ነን:: ውሃ ባይኖር ልብስን ማሰብ እንደሚከብድ ንስሐ ባይኖርም ሰብእናችንን ማሰብ በከበደን ነበር:: አንድ አባት «ሰው ባይበድልም በደለኛ ነው» ይሉ ነበር::

ኃጢአት ሠርተን ወዲያው ፀሐይ አትጠፋም፣ አየር አይቋረጥም:: የመሸው ሌሊት አልነጋም አይልም:: ኃጢአት ሠርተን ግን ወዲያው የሚወሰድብን ጸጋ አለ:: ኃጢአት በሠራን ቅጽበት እግዚአብሔር መጽናናቱን ይወስድብናል:: እርግጠኝነት እናጣለን:: በደመቀ ከተማ የማንቋቋመው ባዶነት ይገጥመናል:: የጸጸትን መርፌ ታውቁት ይሆን? በጣም ቀጭንና መንፈስን የሚወጋ ነው:: በዚያ መርፌ ኅሊናችን መጠቅጠቅ ይጀምራል:: ኃጢአትን እንድንሠራ ያደፋፈረን ሰይጣን አሁን ሊያጽናናን ፈቃደኛ አይደለም:: እንደውም ይህ ካንተ ወይም ካንቺ አይጠበቅም በማለት ይከሰናል::

በራሳችን ፊት መቆም የፈራንበት ጊዜ ጥቂት አይደለም:: እግዚአብሔር ያየብንን ለሰዎች ቢያሳይብን እርሱ የሰማውን ለሰዎች ቢያሰማብን ኖሮ በምድር ላይ እንድንኖር እንኳ ማንም አይፈቅድልንም ነበር:: እርሱ ግን አበሳን ሸፋኝ፣ ጉድን ሰዋሪ አምላክ ነው:: ታላቅ የሕይወት ቅሬታ፣ የወንጀለኝነት ስሜት፣ ሌሊትና ቀን ዕረፍት የማይሰጥ ክስ ብዙ ጊዜ ገጥሞናል:: በእግዚአብሔር ፊት ወድቀን ንስሐ ስንገባ ግን ይህ ሁሉ በኗል:: የእግዚአብሔር ይቅርታ ሕጋዊ

በመሆኑ ኀሊናም ሆነ ሰይጣን ሲቃወሙት የማይችል በክርስቶስ ደም የተከበረልን መንፈሳዊ መብት ነው።

የሮሜ. 2፥4 ያለውን ንባብ ብዙ ጊዜ ሳንረዳው እናልፋለን። ቃሉ፦ *«ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን?»* ይላል። በራሳችን በኩል ልክ ኃጢአት እንደሠራን የምንጠብቀው ውጤት አለ። የምንሄድበት መኪና አደጋ የሚደርስበት፣ የምንወጣበት ሊፍት መሐል ላይ የሚቆም፣ የጀመርነው ሥራ የሚበላሽ፣ ሰው ሁሉ አውቆብን የሚያሳድደን፣ ስብከት የሚጠፋን. . . ይመስለናል። ነገር በተቃራኒው መንገዳችን የተሳካ፣ ሥራው የሰመረ፣ ስብከቱም ብዙ ምሥጢር የፈለቀበት ይሆናል። የዚህ ነገር ምሥጢሩ ምንድነው? ስንል እግዚአብሔር ከክፉ ሥራችን ጋር መተባበሩ ሳይሆን ስጦታውን ወይም ቸርነቱን በማብዛት ልባችንን ለንስሐ ማለዘቡ ነው። እኛ ያጠፉ ሰዎችን ማስተማር የምንፈልገው የምናደርግላቸውን ቸርነት በመቀነስ ነው። እግዚአብሔር ግን ቸርነቱን በማብዛት የኃጢአተኞችን ልብ ለንስሐ ያለዝባል። ይህ ገብቶት ፈጥኖ የተመለሰ ምሕረቱ ይበዛለታል። ይህ ሳይገባው ግን በኃጢአቱ የገፋበት ሰው ፍርዱ ታላቅ ነው። ስለዚህ ኃጢአት ሠርተን ቸርነት ሲበዛልን ፈጥነን ንስሐ ካልገባን መፍራት አለብን። ለዚህ ነው፦ *«ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን?»* (ሮሜ. 2፥4) የሚለው።

በታሪክ ውስጥ ሰው ከመበደል እግዚአብሔር ይቅር ከማለት ያረፋበት ጊዜ የለም። የሰውን ደካማነት አይቶ እግዚአብሔር ንስሐን የሕይወት ውሃ አድርጎ ባይሰጠን ኖሮ ሰው ሰው ለመባል ባልበቃ ነበር። ኃጢአተኛ እግዚአብሔርን መፈለግ ስለማይችል ኃጢአተኛውን በመጀመሪያ የፈለገው ራሱ እግዚአብሔር ነው። ፈልጎ ለንስሐ ቢጋብዘው አዳም ኃጢአቱን ሳይሆን ምክንያቱን ተናዘዘ። የእግዚአብሔርንም የምሕረት ጥሪ ችላ በማለቱ ተፈረደበት።

በብሉይ ኪዳን ድንኳን ውስጥ ዕለታዊ ከነበሩት አገልግሎቶች አንዱ ስለ ኃጢአት የሚቀርበው መሥዋዕትና የምስጋና መባ ተጠቃሽ ናቸው። መሥዋዕቱ ስለ ኃጢአት የሚቀርብ ነው። መባው በእግዚአብሔር ምሕረት የተደሰተው ሰው ስለ ነጻነቱ ምስጋና የሚያቀርብበት ነው። ይህ ዕለታዊ አገልግሎት ነበር። በብሉይ ኪዳን ድንኳን ውስጥ የነበረው ይህ ሥርዓት ለእኛ ያለው ትርጉም ዘወትር ስለ ኃጢአታችን ንስሐ መግባትና እግዚአብሔርን ስለ ምሕረቱ ማመስገን እንዳለብን ነው። «ከሎሌ ስህተት፣ ከጌታ ምሕረት



አይታጣም» እንዲሉ ከእኛ በደል ከእግዚአብሔር ምሕረት አልታጣም። የእግዚአብሔር ምሕረት የመኖራችን ምሥጢሩ፣ ምድር የቆመችበት ዋልታ፣ የቤታችን ምሰሶ ነው። እግዚአብሔር ብዙ ነገሮችን አድርጎልናል። ከዚህ ሁሉ አድራጎቱ በላይ ያበዛልን ምሕረት ይደንቃል።

*መሥዋዕት* ዕለታዊ አገልግሎት እንደሆነ ንስሐም በየዕለቱ የምንፈጽመው ነው። ለዚህ ነው የአቡነ ዘበሰማያት ጸሎት *«እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን»* (ማቴ. 6፥12) የሚለው። ንስሐ የእምነትና የበጎ ተግባራት መጀመሪያው ነው። የመጀመሪያው እምነት ኃጢአተኝነትን ማመን ሲሆን ኃጢአተኝነትንም አምኖ ንስሐ መግባት የመጀመሪያው የቅድስና ተግባር ነው። በአቡነ ዘበሰማያት ጸሎት ንስሐ ሁለት ክፍል እንዳለው እንረዳለን። *«እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን!»* (ማቴ. 6፥12)። አንደኛው ክፍል እግዚአብሔርን ሲመለከት ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ጎረቤታችንን ይመለከታል። ንስሐ ሰላም መፍጠር ነው። የምንኖረው ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር ሲሆን ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት ሲበላሽ የምናስተካክለው በንስሐ ወይም በይቅርታ ነው።

እግዚአብሔርን በንስሐ ይቅርታ ለመጠየቅ ብዙ ጊዜ እንቸገራለን። ለንስሐ የመደብነው ጊዜ የዕድሜአችንን ሙጣጭ ነው። ለንስሐ የመደብነው ጊዜ ዓለም የማትፈልገውን የዕድሜያችንን ማለቂያ መሆኑ ያሳዝናል። ጉብዝና ለኃጢአት፣ ድካም ለእግዚአብሔር መሆኑ ያሳዝናል። ንስሐ የተወሰነ ዕድሜ የተበጀለት ሳይሆን በደላችንን ባመንን ጊዜ ሁሉ የምንፈጽመው ነው። ሐኪም ቤት ለመሄድ ወሳኙ መታመም እንጂ ዕድሜ አይደለም። ንስሐ ለመግባትም ወጣት አረጋዊ አይልም። ወሳኙ በደልን ማመን ነው። ንስሐ የሌለበት በአጠቃላይ መለወጥን የማይጠይቅ ክርስትናን ብዙዎቻችን እንፈልጋለን። ክርስትናን ግን ከሕይወት ለውጥ መለየት ምድርን ከአየር እንደ መለየት ነው። ኃጢአትን በማሰብ ያለው ሕመም እንዲስማን ብዙዎቻችን አንፈልግም። ሕመም ግን የሚድነው በመደበቅ ሳይሆን ተገቢውን መድኃኒት በመውሰድ ነው። እንዲሁም የሠራነውን ኃጢአት ላለማሰብ በመፈለጋችን ከቅጣት አናመልጥም። ምክንያቱም ኃጢአታችንን አስበን ንስሐ ካልገባን እግዚአብሔር አስቦ ይቀጣናልና።

ብዙ ሰዎች የጸሎትን ኃይል እንደሚጠቀሙ ይናገራሉ። ጸሎቴም፦ «ዕድሜ ለንስሐ ስጠኝ» የሚል ነው ይላሉ። ይህ ዕድሜአቸው ግን ለንስሐ የተሰጣቸው መሆኑን ይዘነጋሉ። በንስሐ

ዕድሜ ላይ ተቀምጦ የንስሐ ዕድሜ መለመን በጣም ምስኪንነት ነው። የተቀበሉትን እንደመለመን ነው። እነዚህ ሰዎች ግን ኃጢአትን እስክንጠግበው ጊዜ ስጠን እያሉ እንጂ ጊዜ ተቸግረው አይደለም።

ብዙ ሰው ንስሐን ሲያስብ በማንኛውም ጊዜ ሊያደርገው የሚችል አድርጎ ነው። ንስሐ ግን ዕድል በመሆኑ ይወሰዳል። ንስሐ የምንገባው በንስሐ ድምፅ ብቻ ሳይሆን የንስሐ መንፈስም ሲሰጠን ነው። ከንስሐ ድምፅ ጋር የንስሐ መንፈስ አብሮ ይመጣል። ስንታዘዝ ንስሐ የመግባትን አቅም እናገኛለን። ካልታዘዝን ግን የንስሐው ትእዛዝ ይቀርና መንፈሱ ይመለሳል። ያ ጥሪም ለቅጣት ያመቻቸናል። ዓለሙ ሁሉ የበዳይ አኩራፊ ሆኖ ተቀምጧል። እግዚአብሔር ደግሞ የሞት መድኃኒት ይዞ በየሰው በር ላይ ቆሞ ያንኳኳል።

በየዕለቱ ከሚገጥሙን የሕይወት ፈተናዎች አንዱ ከሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት መበላሸት ነው። ይቅርታ ማድረግ ፈተናችን ነው። በራሳችን አቅምም ይቅርታን መለማመድ አይቻልም። የእግዚአብሔር ጸጋ ግን ያስችለናል። እግዚአብሔር እኛን ይቅር ለማለት ልጁን ነው ያየው። እኛን ይቅር ለማለት ሰዎችን ሳይሆን ስለበደላችን በመስቀል ላይ የተሰቀለውን ጌታ ነው መመልከት ያለብን። እርሱን ስናይ የይቅርታው ብርሃን ይሳልብንና በቂማችን የምናስከብረውን ወንድነታችንን እናጣዋለን። ለብዙዎቻችን ቂም ጀግንነት ነው። ትልቅ ጀግንነት ግን ይቅርታ ማድረግ ነው። በይቅርታ የሚከብረው እግዚአብሔር ሲሆን እኛም ሰላሙን እንካፈላለን። ዛሬ በታሪክ የምንወቅሳቸው በቀለኞችን እንጂ የይቅርታ ሰዎችን አይደለም። ከሥጋቸው አልፎ በነፍሳቸውም የሚወቀሱት በቀለኞች ናቸው።

ከሁሉ በላይ ሰውን አሳዝነን እግዚአብሔርን ማስደሰት አይቻለንም (ማቴ. 5÷23-26)። ለጸሎት እንቅፋት ከሚሆኑ ነገሮች አንዱ ቂም በቀል ነው። እግዚአብሔር የቂም እሹሩሩን አይወድም። አውርደን እንድንጥለው ይፈልጋል። የቂም ወዳጅ የሚያነደን ሰይጣናዊ የአሳብ ወዳጅ ነው። «ቂም ይዞ ጸሎት፣ ሳል ይዞ ስርቆት» እንደሚባለው ሌሎችን ይቅር ብለን መጸለይ ግድ ነው። ይቅርታን በሚመለከት በስፋት *«ይቅርታ»* በሚለው መጽሐፌ ላይ የተገለጠ በመሆኑ እንድትመለከቱት እጋብዛለሁ። እዎ የጸሎትን ጤናማነት ለመጠበቅ ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር ያለንን ግንኙነት ሰላማዊ ማድረግ ይገባናል።

ጥልቅ ወደ ሆነ የጸሎት ሕይወት ስንገባ እግዚአብሔርን ማየት እንጀምራለን። እግዚአብሔርን ስናይ ራሳችን ያንስብናል።



ራሳችን ብቻ ሳይሆን ትልቅ ስፍራ የሰጠናቸውም ያዝያኖች ያንሱብናል። የተሰወረ ኃጢአታችን ይታየናል። እንደ ኢሳይያስ፡- *«ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ÷ ከንፈሮቻቸውም በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል በመቀመጤ ዓይኖቼ የሠራዊትን ጌታ ንጉሡን እግዚአብሔርን ስለ አዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ!»* (ኢሳ. 6÷5) እንላለን። ኃጢአተኝነታችንን አምነን ስንናዘዝ ልዩ ወደ ሆነ መነቃቃትና ፈውስ እንገባለን። እግዚአብሔር ሲታየን ራሳችን ይታየናል። በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ርቀት ሰፊ ቢሆንም የእግዚአብሔር ብርሃኑ ይሰበናል እንጂ አይገፋንም። ማግኔት ተቃራኒውን እንዲስብ እግዚአብሔርም ቅዱስ ሳለ ኃጢአተኞችን ያቀርባል። የብርሃን ባሕርይው ማራቆት ነው። እግዚአብሔር ግን የሚሰውር ብርሃን ነው።

በክርስትና ሕይወታችን ልዩ የሆነ ደስታና የጸሎት እርካታ የምናገኘው መንፈስ ቅዱስ የተሰወረ ኃጢአታችንን በቃሉ መብራት እንዲያሣየን ስንፈቅድና በዚያም ኃጢአት ላይ ስንናዘዝ ነው። ዓስም ብዙ የሳቅ ፕሮግራሞችን አዘጋጅታ ስንወጣ አኩርፈን እንወጣለን። በንስሐ አልቅሰን ስንነሣ ግን ደስታን እንሞላለን።

ባለንበት ዘመን እውነተኛ የንስሐ ድምጾች እየጠፉ መሆኑ ያሳዝናል። በአደባባይ ላይ የሚንጎማለሉት ሰባክያን የሰውን የስሜት ጣቢያ እየፈለጉ የሚሰብኩ እንጂ የእግዚአብሔርን አሳብ የሚገልጡ አይደሉም። ሕዝቡን ቢገስፁ የአሥራት በኩራት ገቢ የሚቀንስ ወይም አማንያኑ የሚደነብሩ ይመስላቸዋል። ሕዝቡም የእግዚአብሔርን አሳብ ሳይሆን ከሞት የማያድነውን የሰባክያንን ሽንገላ እየሰማ ይመለሳል። የአብያተ ክርስቲያናት መድረኮች ተረት እያጠኑ በሚሰብኩ ብዙ ተራቾች ተጣበዋል። ሕዝቡም ፌዘኛ ሆኗል። አልቅሰው የሚያስለቅሱ ሰባክያን ዛሬ ምነው በተገኙ! ተረት እያጠኑ መድረኩን መዝናኛ ማድረጋቸው እግዚአብሔርን በጣም ያሳዝነዋል። ካህኑ ዔሊ ልጆቹን ለመገሰጽ ሳሳላቸው። ነገር ግን ለመገሰጽ የሳሳንለት ገንዘብ አይሆንምና ልጆቹ የእርሱም የራሳቸውም የእግዚአብሔርም ሳይሆኑ ቀሩ። ዛሬም ለእግዚአብሔር ያልተገዛ ሕዝብ የሰባክያንም ወገን አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ንስሐን ለማወጅ ጠልተው ስለ ምድራዊ ብልጽግና የሚያወሩ እንዳሉ ሁሉ በተቃራኒው ደግሞ አንዳንድ ሰባክያን በንስሐ ስም ሕዝቡን እያስፈራሩ ይዘርፉታል። እነዚህ ሰዎች በሕዝቡ ኃጢአተኝነት የተንገሸገሹ መስለው የሚሰብኩት የከፈቱት ጎተራ እስኪሞላላቸው ነው። ንስሐ ሳንገባ ንስሐን መስበክ ጥቅም የለውም። ንስሐ ምስክር እንጂ የማስታወቂያ ሠራተኛ አትፈልግም።

ሥልጣኔ የምንለው ነገር ኃጢአትን የሚያቆነጅ እንጂ ጽድቅን የሚያግዝ አለመሆኑን በግልጥ እያየነው ነው። ብዙ ዘመናውያን ክርስቲያኖች ለኃጢአት ያላቸው አመለካከት በጣም ለዘብተኛ ነው። በእነርሱ አሳብ የማይተባበሩትን ክርስቲያኖች እንደ አክራሪ ይመለከታሉ። ኃጢአትን የሚያዩት በዲያብሎስ «አትሞቱም» (ዘፍ. 3፥4) በሚል የሸንገላ ዓይን እንጂ እግዚአብሔር ኃጢአትን በሚያይበት ዓይን አይደለም። ነገር ግን ቀራኒዮን ስንመለከት እግዚአብሔር ለኃጢአት ያለውን የፍርድ አቋም እናያለን። በክርስቶስ የተገለጠው የእግዚአብሔር ጸጋም ከኃጢአትና ከዓለማዊ ምኞት ለማምለጥ ነጻነትን የሚሰጥ እንጂ ለኃጢአት የፈቃድ ወረቀት የሚሰጥ በፍጹም አይደለም (ቲቶ ፪፥11-14)። አድርገውና ንስሐ ትገባለህ የሚሉ ሰዎች ብዙ ናቸው። መድኃኒት አለ ተብሎ በቫይረስና በጀርም የሚጫወት ሰው አለ ወይ? መድኃኒት ጥንቃቄን የሚያስቀር አይደለም። ክርስቲያን ሆይ አስተውል! ኢየሱስ ክርስቶስ ያስታረቀው ኃጢአተኞችንና እግዚአብሔርን እንጂ ኃጢአትንና እግዚአብሔርን አይደለም።

አንባቢ ሆይ! የጸሎት ሦስተኛው ክፍል ንስሐ ነው። ንስሐ እምነትም ምግባርም ነው። የራስን ኃጢአተኝነትና የእግዚአብሔርን ምሕረት ማመን በመሆኑ እምነት ይባላል። ከማንኛውም በጎ ምግባር በላይ ጥፋትን ማመን ትልቅ ተግባር በመሆኑ ንስሐ ምግባር ነው። ንስሐ ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር ሰላም መፍጠር መሆኑን የአቡነ ዘበሰማያት ጸሎት ያስገነዝበናል። በርግጥም የምንኖረው ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር ነው። ጸሎት ግንኙነት በመሆኑ ግን ኙነትን ንጹሕ ማድረግ እጅግ ተገቢ ነው። ስለዚህ ኃጢአታችንን በንስሐ ማስወገድ አንዱ የጸሎት ክፍል ነው።



# ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት

## ምልጃ

*«የአንድን ሰው ነውር ስንለማ እግዚአብሔር ይህን እንድሰማ ያደረገኝ ስለዚህ ወንድሜ በማቀርበው ምልጃ ወንድሜን ሊረዳው አስቦ ነው ማለት ይኖርብናል።»*

በሩቅ ዘመን የነበረ አንድ ፈላስፋ ሰዎችን ሰብስቦ «በምድር ላይ የመጨረሻው ባለጠጋ ማን ነው?» ብሎ ጠየቀ። ሰዎችም እንደቆሙበት አቅጣጫ የታያቸውን ገለጡ። አንዳንዶች ገንዘብ ያለው አሉ። ሌሎችም ዘመድ ያለው አሉ። አርቀው ያሰቡ የመሰላቸው እውቀት ያለው አሉ። የቀሩትም ሥልጣን ያለው አሉ። እርሱ ግን እነዚህን ሁሉ ምላሾች አልተቀበለም። ሰዎቹም ፈላስፋውን፦ «ከዚህ ውጭ ምን ይኖራል» አሉት። እርሱም ራሱ የጠየቀውን ጥያቄ ራሱ መለሰ፦ «በምድር ላይ የመጨረሻው ባለጠጋ የሚጸልይለት ሰው ያለው ነው። በምድር ላይም የመጨረሻው ደሃ የሚጸልይለት ሰው የሌለው ነው» አለ ይባላል።

የዚህ ፈላስፋ ቃል እውነት መሆኑን አምናለሁ። እግዚአብሔር ብርታቱን ሰጥቶኝ የምጸልይላቸውን ሰዎች ሳስብ የመጨረሻ ባለጠጋ እንደሆኑ አስብና ደስ ይለኛል። ለወዳጃችን የምንሰጠው ትልቅና የመጀመሪያው የፍቅር ስጦታ ስለ እርሱ መጸለይ ነው። ቀጥሎ ክርስቶስን መስጠት ነው። ለወዳጅ ፖስት ካርድ መስጠት ትንሽ ነው። ወርቅ መስጠትም ጥቂት ነው። ገንዘብ የማይገዛውን ክርስቶስን መስጠት ግን ከሁሉ በላይ ነው። የሌሎችን ጸሎት መፈለግና ለሌሎች መጸለይ ወሳኝ ነገር ነው። እኛም ከሌሎች ጸሎት ነጻ አይደለንም። በቤት ውስጥ የተያያዘው ከሰል አፍኖ ሊገድላቸው ሲል ከደጅ ሰው መጥቶ በሩ ሲከፈት ዳኑ። በዚህ ጊዜ መነኵሲቷ እናት እሳቱን ያቀጣጠለችውን ጓደኛቸውን፦ «በስንት ሰው ጸሎት ተደጋግፋ የቆመችውን ነፍሴን እንዲህ ጉድ ልታደርጊያት ነው ወይ?» ብለው ሲናገሩ ሰማሁ። አዎ እኛም ብንሆን ከሌሎች ጸሎት ነጻ አይደለንም።

ሳናውቃቸው የሚጸልዩልን ሰዎች አሉ። ይልቁንም እኛ ለመንፈሳዊ ሕይወት እንድንወለድ ያማጡልን ሰዎች አሉ። ያለ ምጥ

የሚወለድ የለምና:: የሌሎች ጸሎት ፍሬ መሆናችንን ማሰብ ያስፈልገናል:: እግዚአብሔር እኛን ማሰብ የሚሰጣቸው ሰዎች ስጦታዎቻችን ናቸው::

ምልጃ ስለ ሌሎች መጸለይ ማለት ነው:: ስለምናውቃቸውና ስለምንወዳቸው የእኛ ስለሆኑ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ስለማናውቃቸው ቅርበት ስለ ሌለን በሩቅ ሀገር ስለሚኖሩ ሕዝቦችና መንግሥታት መጸለይ ምልጃ ይባላል:: ካልጸለይን የግላችንን ሰላም ብቻ በመንከባከብ ሰላምን ልናገኝ አንችልም:: የእኛ ሰላም አስተማማኝ የሚሆነው የምናየውና የምንሰማው በጎ ሲሆን ነው:: የሰው ሕይወት የተያያዘ ነው:: የአንዱ ችግር አንዱን ይነካል:: ስለዚህ ስለ ሌሎች መጸለይ በተዘዋዋሪ ስለ ራሳችን መጸለይ ነው:: እግዚአብሔር በምልጃ ጸሎት ብዙ ተአምራትን ለማድረግ ይፈልጋል:: እግዚአብሔር የሚሠራው ምስክር አቁሞ ነውና ስንጸልይ ተአምራቱን እናያለን:: ዛሬ የምናየው ብዙ ሰቆቃና ጭንቅ የትውልዳችን እንደ ዓይን መጥፋት ያለመጸለያችን ውጤት መሆኑን የተገነዘብን ስንቶቻችን እንሆን ይሆን? ስለ ሌሎች ምልጃ ማድረግ:-

## <u>ግዴታ ነው</u>

ምልጃ ማድረግ ግድ ነው:: ለሌሎች ወንጌል መስበክ ግዴታ እንደሆነ ሁሉ ስለ ሌሎች መጸለይም ግድ ነው:: ያልዘራነውን ማጨድ እንደማንችል ሁሉ ያልጸለይንበትንም ፍሬ ከትውልዱ ማየት አይቻለንም:: በርግጥ ጸሎት ተግባርን አይተካም:: ብዙ ሰዎች በኪሳቸው ገንዘብ እያለ ለድሆች ወገኖቻቸው «እንጸልይላችኋለን» ይላሉ:: እውነተኛ የጸሎት ሰዎች ግን መልካም ነገር ለማድረግ ይሽቀዳደማሉ:: «እንጸልይላችኋለን» የሚለው ቃል ደሃ ማባረሪያ መሆኑ ያሳዝናል:: ክርስትና ቃላት ብቻ ሲሆን ይደርቃል:: ደግሞም ደግነትን ያልተለማመደ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ደግነት አምኖ ስለ ሌሎች አይጸልይም:: ቢጸልይም «ፍጥረትህን ራስህ ቻል:: እኔን አታሳቅቀኝ» የሚል ስሜት ያዘለ ነው::

በተቃራኒው ደግሞ ዋናው መልካም ማድረግ ነው መጸለይ አይደለም የሚሉ ሰዎች አሉ:: ጸሎት ግን የመልካም ነገር ኃይል ነው:: ለወገኖቻችን የገንዘብ መባ ብቻ ሳይሆን የጸሎት መባም ልናወጣላቸው ይገባል:: የእኛ እርዳታ የችግሩን ብዛት የሚቀንስ ሲሆን የእግዚአብሔር እጅ ግን የችግሩን ምንጭ የሚያደርቅ ነው::



ይልቁንም አገልጋዮች ለሚያገለግሉት ሕዝብ መጸለይ አለባቸው:: ገበሬ ዘር ዘርቶ በየጊዜው ይንከባከበዋል እንጂ መከርን ጠብቆ አይመጣም:: እንዲሁም የዘራነውን የቃሉን ዘር በጸሎትና በጉብኝት ማጽናት ይገባናል:: እኛ የምናመልከው ለእኔ ሳይል በመስቀል ላይ የሞተውን፣ ለእርሱ በሚታሰብለት ደግሞም በቀልና ፍርድ በሚለመንበት ሰዓት ለጠላቶቹ የማለደውን ጌታ በመሆኑ አብዝተን ስለ ሌሎች መጸለይ ይገባናል (ሉቃ. 23፥34):: ከቃላት ኃይልና ሰዎችንም ከሚያስደስቱ ቋንቋዎች አንዱ «እጸልይላችኋለሁ» የሚለው ቃል ነው:: ሰዎች በጸሎት እንደምናስባቸው ስንነግራቸው ደስታ ይሰማቸዋል:: ይህንን ቃል ግን መጠቀም ያለብን በእውነት የምንጸልይላቸው ከሆነ ብቻ ነው:: እጸልይላችኋለሁ የሚለውን ቃል የምናወጣው እዘኑልኝ ስለ እናንተ እንቅልፍ አጣሁ በሚል ስሜት ከሆነ ይህ ግብዝነት ነው::

በማማከር አገልግሎት ሰዎች አስቃቂ ችግራቸውን ከነገሩኝ በኋላ እኔ የምሸከመው እየመሰላቸው አስጨነቅኋ አይደል? ይሉኛል:: እኔ የራሴንም ሸክም መሸከም የማልችል የደካሞች ራስ ነኝ:: ነገር ግን የሰማሁት የሚከብደኝ እስክጸልይ ነው:: አሁን ግን ችግሮችን መስማት ስጀምር ወዲያው «የሰማይ አምላክ ከአሁን ጀምሮ ስማ» ብዬ ራሴን እንደማስተላለፊያ ቆጥሬ በልቡናዬ እየጸለይኩ እሰማለሁ:: እንደ ችግራቸውም ጥልቀትና ምጥቀት በዘወትር ጸሎቴ አስባቸዋለሁ:: እግዚአብሔር አስደናቂ ነገሮች ሲያደርግ አይቻለሁ:: ገናም አያለሁ:: *«ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና»* (ገላ. 6፥9) የሚለው ቃል ለጸሎትም ይሠራል:: ሰዎች ጸልዩልን ብለውን እሺታችንን ሳንፈጽም መተኛት ኃጢአት ነው:: በርግጥ ሰዎች «ጸልዩልን» ብለውን ያ ጉዳያቸው ተፈጽሞላቸው «አመስግኑልኝ» ብለው ዳግም አይመጡም:: ይህ ትልቅ ነውር ነው:: አገልጋይ ስንሆን የሰዎችን ችግራቸውን ስንሰማ እናስባለን:: ችግሩ መወገዱን ግን መልሰው ስለማይነግሩን ሰዎቹን ባሰብን ቊጥር ያ ችግር ይታወሰናል:: እኛም ብንሆን የክርስቲያኖችን የጸሎት እርዳታ ከጠየቅን በኋላ ሲፈጸም መናገር ተገቢያችን ነው::

ስለ ሌሎች አለመጸለይ ኃጢአት ነው:: ነቢዩ ሳሙኤል የእስራኤል ልጆች ጸልይልን ብለው በጠየቁት ጊዜ *«ደግም መልካሙንና ቅኑን መንገድ አስተምራችኋለሁ እንጂ ስለ እናንተ መጸለይን በመተው እግዚአብሔርን እበድል ዘንድ ይህ ከእኔ ይራቅ»* በማለት ተናግሯል (1ሳሙ. 12፥23):: የሚሽከረከሩ ማሽኖች ቅባት ሲያገኙ በልስላሴው እንደሚሽከረከሩ ምልጃም ጸሎትን የሚያለሰልስ ቅባት ነው::

## እግዚአብሔር እኛን የሚያይበት ነው

ሐዋርያው ጳውሎስ በእስር ላይ ሆኖ ከጻፋቸው መልእክታት አንዱ የፊልጵስዩስ መልእክት ነው። ጳውሎስ በመከራና በፈተና ውስጥ ያሰውን ተወዳጅ ጸሎት ከልምዱ አይቶ ጽፎልናል፡- *«ጌታ ቅርብ ነው። በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ። አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል»* (ፊልጵ. 4፥6-፺ ብሏል።

በመከራ ሰዓት ከመከራው በላይ የሚከብደን ስመከራው ያሰን ፍርሃትና ስጋት ነው። አብዛኛው ምላሻችን ጭንቀት ነው። ጭንቀት ሰመጣው ችግር ወሰድ መከፈል ነው። ጭንቀት የእግዚአብሔርን ፍቅሩን፣ ቸርነቱን፣ ርኅራኄውን መጠራጠር ነው። ስለዚህ ጭንቀት ያሰማመን ኃጢአት ነው። ጭንቀት በራሱ ችግር እንጂ መፍትሔ አይደሰም። ሰደረሰብን መከራና ፈተና መፍትሔው ጸሎት ነው። ሰላምን የምናገኘው ሰእግዚአብሔር ነገራችንን ግልጽ ስናደርግ ብቻ ነው። በመከራ ውስጥ የጸሎት ኃይል ብርቱ ነው።

በመከራ ሰዓት አውጣኝ የሚል ልመና ብቻ ሳይሆን ምልጃና ምስጋናም ወሳኝ መሆኑን ጳውሎስ ይነግረናል። በርግጥ በሚጎረብጥ ሕይወት ውስጥ እያለፍን የራሳችንን ትተን ስለ ሌሎች መማለድ፣ እየታመምን ተመስገን ማለት ከባድ ነው። ነገር ግን ይህን ሕይወት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሳይቶናል። ጳውሎስም አድርጎታል። ደግሞም እግዚአብሔር የማይቻል ነገርን አያዝዘንም። ስለ ራሳችን ጸልየን መልስ ስናጣ ስለ ሌሎች መማለድ የልመናችንን መልስ ያቀርበዋል። ምክንያቱም እግዚአብሔር የሌሎች ችግር ምን ያህል እንደሚሰማን ማወቅ ይፈልጋል። እርሱ የፍቅር አምላክ ነውና ፍቅርን ማየት ይፈልጋል። ሰእኔ ሰእኔ የሚል ጸሎትና ሕይወት በእግዚአብሔር ዘንድ ተወዳጅ አይደሰም።

በመከራችን ውስጥ ከመታወቅ በላይ የሆነውን የክርስቶስን ሰላም ሰመሰማመድ ጸሎት፣ ምልጃና ምስጋና ወሳኝ ነው። ከማጉረምረም መጸሰይ፣ የራሳችንን ችግር አድንቀን ከመመልከት ስለ ሌሎች ችግር መጸሰይ፣ ከማማረርም ተመስገን ማለት ተገቢ ነው። መንፈስ ቅዱስ ራሱ ስለ ሌሎች እንድንጸልይ ያበረታታናል። አንዳንድ ጊዜ እየጸሰይን ብዙ ሰዎች በኅሊናችን ይታወሱናል። እኛም ሰይጣን ያመጣቸው እየመሰሰን እንበሳጫለን። ነገር ግን ሰይጣን በአባትና በልጅ ንግግር መሐል መግባት አይችልም። እነዚህን ሰዎች በኅሊናችን



የሚያመጣው መንፈስ ቅዱስ ነው። «ልጄ ያንተን ጉዳይ ሰእኔ ተወው። ይልቁንም ሰእገሌ ጸልይለት ማሰቱ ነው።» እኛም የራሳችንን ጉዳይ ትተን ስለ እነርሱ ስንጸልይ ልባችን በተስፋና በመንፈሳዊ ደስታ ይሞላል። የጸሎታችንም ሰዓት ይረዝማል። አዎ ስለ ሌሎች ስንማልድ እግዚአብሔር የእኛን ጉዳይ ያየዋል።

## ሰላም የምናገኝበት ነው

በነፋስ ላይ ሻማ የሰኮሰ ሰው ተጠንቅቆ እንደሚይዝ ሁሉ ብዙ ሁከት ባሰበት ዓሰም ላይም ሰላምን ያገኘ ሰው ተጠንቅቆ ይይዛል። የራሱን ሰላም ሰመጠበቅ ሲል ሰሌላው ሰላም ይሰጣል። በርግጥም ሰዎች ሰላም የሚሰጡን ውስጣቸው ሰላም ሲሆን ብቻ ነው። ከታወኩ ያውኩናል። ይልቁንም ነገሥታት በክርስቲያኖች ጸሎት ካልታገዙ ሰይጣን ባወካቸው ቍጥር ሕዝቡን ያውካሉ። የሚያጠፉትም እንደ እቅማቸው ብዙ ነው። ስሰዚህ ከሁሉም በላይ ሰነገሥታትና ሰአስተዳዳሪዎች ጸሎትና ምልጃ ሊደረግ ይገባዋል። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን የሞቱትን ነገሥታት ስም ጠርታ በጸሎት ስታስብ ጸሎትና ምልጃ የሚያስፈልጋቸውን ያሉትን ነገሥታት ግን በስማቸው ልትጸልይላቸው አሰመቻሏ በጣም ያሳዝናል። ያሉት ነገሥታት ቤተ ክርስቲያን ሰእነርሱ ያላትን ፍቅር በምን ይወቁት?

በእውነት በገዢዎች የሚደርሰው ጥፋት የክርስቲኖች በጸሎት መድከም ነው። የእኛን ድርሻ ሳንወጣ እነርሱን መውቀስ ከንቱ ነው። አብዛኛው ሰዓታችንን የምናባክነው የመሪዎችን ነውር በማውራት ነው። ክፉ ናቸው በማሰት ጨዋ አላደረግናቸውም። ጥቂት ብንጸልይላቸው ግን እግዚአብሔር አእምሮአቸውን ሲባርክ እናይ ነበር። ሰውን ስንባርከው ቡሩክ፣ ስንረግመው ርጉም መሆኑ የተፈተነ እውነት ነው። አንድ ሰው ሲናገር፡- «ውሻን ስንጠቍመው ሄዶ እንደሚነክስ ሰውንም ስንነቅፈው ሰይጣን እንዲነክሰው እየጠቆምን ነው። ከነቀፍነው በኋላ ሰውዬው በክፋቱ ብሶበት እንጂ ተሻሽሎ አናየውም። ሰምን? ብንል ሰሰይጣን ውጊያ አሳልፈን ስሰሰጠነው ነው። የአንድን ሰው ነውር ስንሰማ እግዚአብሔር ይህን እንድሰማ ያደረገኝ ስሰዚህ ወንድሜ በማቀርበው ምልጃ ወንድሜን ሊረዳው አስቦ ነው ማሰት ይኖርብናል» ብሏል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ሰጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክቱ፡- *«እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ*

*ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ»* (1ጢሞ. 2፥1-3) ብሏል:: ሐዋርያው በነበረበት ጊዜ የነበረው ንጉሥ ክርስቲያኖችን በማሳደድ የታወቀው ኔሮን ቄሣር ነበር:: ጳውሎስንም ወደፊት የሚገድለው ይህ ንጉሥ ነው:: ጳውሎስ ግን እንዲጸለይለት አዘዘ:: ስለ ነገሥታትና በየአጥቢያው ስለተቀመጡ አስተዳዳሪዎች ካልጸለይን ሰይጣን ባወካቸው ጊዜ ሁሉ ያውኩናል:: ስለዚህ ለመሪዎች የምንጸልየው ጸጥና ዝግ ብለን ለመኖር ነው:: ስለ ሌሎች ስንጸልይ ራሳችንም ተጠቃሚዎች እንሆናለን:: ምልጃ የጸሎታችን ብቻ ሳይሆን የክርስትናችንም ዘይቤ ነው::

## ፍቅር ነው

በኃጢአት ፈተና ውስጥ ስንገባ የጸሎትን ኃይል የሚጠቀሙ ክርስቲያኖችን በጸሎት እርዱኝ ስንል ፈተናችን ይርቃል:: እግዚአብሔር ራሳችንን ስለማዋረዳችን ዳግመኛም ሌሎች ስለ እኛ በፍቅር ያቀረቡትን ልመና በማሰብ ፈተናችንን ያርቅልናል:: ከዚህ ሁሉ በላይ ለራሳችን ከባድ መስሎ የታየን ነገር ስንከፋፈለው ቀላል ይሆናል:: የአገራችን ምሳሌ:- «አምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ፣ ለአምሳ ሰው ጌጡ ነው» ማለቱ ለዚህ ነው:: ያዕቆብ በመልእክቱ ምልጃ ፍቅር መሆኑን ይገልጣል:- *«እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ፥ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች . . .»* (ያዕ. 5፥16-18) ብሏል:: እግዚአብሔር ስለ ጥቂቶች ልመና ብዙዎችን ይምራልና የእኔ ጸሎት ምን ያመጣል? ብለን ጸሎትን በእኛ አቅም ወስነን እንዳናስንፍ እግዚአብሔር ብልሃቱን ይስጠን:: ዓለም በሰፊ ችግር ውስጥ የወደቀችው የእኔ አስተዋጽኦ ምን ይቀርፋል በሚሉ ሰዎች ምኝነት ነው:: ምንጮች ሲተባበሩ ትልቅ ወንዝ ይሆናሉ::

ሰይጣን ትሕትና በሚመስል ነገር ብዙዎችን የጸሎት ትጥቃቸውን እንዳስጣለ እናውቃለን:: «የእኔን ጸሎት ተዉት» በማለት ብዙዎች መጸለይ አቊመዋል:: ጸሎት ግን እግዚአብሔር ተስፋውን የሚፈጽምበት የጸጋው መንገድ ነው:: በርግጥ ንስሐ ካልገባን ጸሎታችን ይታሰራል (ኢሳ. 59፥1-2):: በዘወትር ኑሮአችን ግን ትሕትና በሚመስል መስነፍ የእኔ ጸሎት ምን ሊያመጣ ነው? ብለን መቀመጥ ተገቢ አይደለም:: ዓለም የችግር ማጠራቀሚያ የሆነችው «የእኔ ድርሻ ምን ሊለውጥ ነው?» በማለት መልካም ነገርን የናቁ ሰዎች በመብዛታቸው ነው:: ብዙ ትንንሾች አንድ ትልቅ ነገር እንደሚፈጥሩ መረዳት ለብዙዎች አልተቻላቸውም:: በጸሎትም



እንዲሁ ነው:: አንድን ነገር ማድረግ አለመቻል ሁሉንም ነገር ማድረግ አለመቻል ማለት አይደለም:: ማድረግ ለሚችለው ጌታ ማሳሰብ ከማድረግ በላይ ነው::

በምልጃ ጸሎታችን ላይ እግዚአብሔር ምን ያህል ንቁ እንደሆነ ይሰማኛል:: ብዙ ሰዎች ጸልይልን ብለውኝ እሺ እልና እረሳለሁ:: ታዲያ እነዚያ ሰዎች በሌላ ቀን እግዚአብሔር ጸሎትህን ሰምቶ ፈጸመልኝ ብለው ደስታቸውን ሲነግሩኝ በራሴና በእግዚአብሔር እገረማለሁ:: በፍጡር ዝንጉነት በእግዚአብሔር ሰሚነት! ይህን ሳስብ እግዚአብሔር የምልጃ ጸሎትን ምን ያህል እንደሚሰማና እንደሚወድ እኛን ተክቶ እንደሚሠራ አስባለሁ::

## ባለ አደራ ነን

በወታደር ቤት ሠራዊቱ ሲተኛ የሚጠብቅ ተረኛ ዘብ አለ:: ይህ የሌሊት ተረኛ ተኝቶ ከተገኘ ያንን ሁሉ ሠራዊት ለሞት አሳልፎ ሰጥቷልና በሞት ይቀጣል:: ሕዝቡ በብዙ ነገር እንዳንቀላፋ እናያለን:: ስለዚህ ለሕዝቡ ለመጸለይ ባለ አደራ ነንና መትጋት ይገባናል:: በዛሬ ዘመን ቤተ ክርስቲያንም ድንዛዜ ላይ እንዳለች እያየን ነውና በዚህ የቀን ሌሊት በሆነ ዘመን ተግተን በመጸለይ ትውልድን ከወራሪ ማዳን ይገባናል:: እግዚአብሔር ባለ መጸለይ ከንጉሡ ይልቅ ቄሱን፣ ከዓለማውያን ይልቅ እኛን ይታዘባል::

*«ስለ ኤዶምያስ የተነገረ ሸክም:: አንዱ ከሴይር:- ጉበኛ ሆይ፥ ሌሊቱ ምን ያህል ነው? ጉበኛ ሆይ፥ ሌሊቱ ምን ያህል ነው? ብሎ ጠራኝ:: ጉበኛውም:- ይነጋል ደግሞም ይመሻል፤ ትጠይቁ ዘንድ ብትወድዱ ጠይቁ፤ ተመልሳችሁም ኑ አለ»* (ኢሳ. 21፥11-12)::

ጉበኛ የከተማን በር የሚጠብቅ የሌሊት ዘብ ነው:: በመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ ከተሞችን በግንብ መቅጠር የተለመደ ነው:: በከተማው ቅጥር በር ላይም ረጅም ማማ ተሠርቶ ጉበኛ ይቀመጣል:: ሕዝቡና ንጉሡ ተኝተው ሳለ ጠላት ቢመጣ ጉበኛው ድምፁን በማሰማት ያነቃል:: ክርስቲያን ጉበኛ ነው:: ሕዝቡና መንግሥቱ ሲተኙ በጸሎት ይጠብቃል:: ጉበኛ ትልቅ ኃላፊነት የተሸከመ ነው:: ክርስቲያንም ስለ ሌሎች በጸሎት እንዲቆም አደራ የተቀበለ ነው::

የአቡነ ዘበሰማያት ጸሎት ምልጃም አለበት:: *«አባታችን ሆይ» «ስጠን» «ይቅር በለን» «አታግባን» «አድነን»* የሚሉት የአቡነ

ዘበሰማያት ቃሎች ግላዊነትን ሳይሆን ሌሎችንም የሚመለከቱ ናቸው:: «አባቴ ሆይ» ሳይሆን «አባታችን ሆይ» የሚለው አጠራር ጸሎተኛው ብቻውን ሳይሆን የእግዚአብሔር አባነት የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ይዞ እየቀረበ መሆኑን የሚያመለክት ነው:: ስለዚህ ስለ ሌሎች መጸለይ ወይም ምልጃ የጸሎታችን አንዱና የማይቀረው ክፍል ነው:: ጸሎት ምስጋናን፣ ልመናን፣ ንስሐና ምልጃን ያጠቃልላል:: የአንድ የተሟላ ጸሎት መገለጫው እነዚህ ተግባሮች ናቸው::



# ምዕራፍ ዐሥራ ሰባት

## እግዚአብሔር ይመልሳል

*«የመሻታችን ሁሉ አምላክ ነህና፣ የፍላጎታችን ሁሉ መገኛ ነህና፣ የተትረፈረፈ በረከት ያለህ አምላክ ነህና፣ የሕይወትን አቅጣጫ እንድታሳየን የልብሶችህን ዘርፍ ይዘን እንለምንሃለን::»*

ከዓመታት በፊት በደቡብ ሱዳን ለተከሰተው ረሀብ የአሜሪካ መንግሥት አስፈላጊውን እርዳታ እሰጣለሁ ብሎ በዜና ማሰራጫዎች አስነገረ:: ከዚህ በኋላ ያደረገው ነገር ቢኖር፣ በገበያ እጦት ምክንያት ሊከስር ያለን የታኮ ጫማ ፋብሪካ ምርቶች በሙሉ ገዝቶ ወደ ደቡብ ሱዳን ላከ:: ለረሀብተኛው ሕዝብም ታኮ ጫማን በማከፋፈል የታኮ ጫማውን ፋብሪካ ከክስረት አዳነ::

እግሩን ለበላው ሰው ራሱን ማከክ ለችግሩ መፍትሔ እንደማይሆንለት ሁሉ ትልቁ ጥያቄው ምግብ ለሆነለት ሰው ጫማ አድርግ ብሎ መስጠትም በመራቡ ላይ መሳለቅ ነው የሚሆነው:: ይህም ጌታ:- *«ከእናንተ፥ ልጁ እንጀራ ቢለምነው፥ ድንጋይን የሚሰጠው ከእናንተ ማን ሰው ነው?»* ብሎ የተናገረውን ቃል እንድናስታውስ ያደርገናል (ማቴ. 7፥9):: አዎ ማንም ለገዛ ልጁ ራበኝ ሲለው ድንጋይ ለመስጠት ባይፈልግም ላልወለደው ልጁ ግን ድንጋይ ከመስጠት እንደማይመለስ ይህ ታሪክ ያሳየናል:: እግዚአብሔር ግን ጥያቄአችንን በተገቢውና በማትረፍረፍ ይመልሳል:: እርሱ ከአባትም ከመንግሥትም ይለያል::

ዓይንን የፈጠረ እግዚአብሔር ያያል፣ ጆሮን የፈጠረ እግዚአብሔር ይሰማል:: ጸሎታችን ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን ለማስረዳት ስለሚሞክር ጣዕም ያጣል:: እግዚአብሔር ከእኛ በላይ የነገሮችን አካሄድና ጉዳት ያውቃል:: ጸሎታችን እግዚአብሔር እንዲራራልን የምንማፀንበት እንጂ እንዲገባው የምናስረዳበት ከሆነ ስህተት ነው:: እርሱ ጆሮን የፈጠረ ነው ይሰማል:: ዓይንን የፈጠረ ነው ያያል:: የርኅራኄን ጸጋ ለልጆቹ የሚሰጥ እርሱ ይራራል::

ዛሬ እየበላን ያለነው በረከት የረሳነው የጸሎት መልስ ነው። በልጅነታችን ወይም ከዓመታት በፊት ጸልየናል። የጸለይነውንም ረስተነዋል። እግዚአብሔር ግን የስማውን ስለማይረሳ ይኸው አድርጎልናል። እርሱ የከረመ በረከትን በማብላት የታወቀ ነው።

እናቶቻችን «ያንተ ጆሮዎች ጸሎትን አፍስሰው አያውቁም» እያሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል። ዳግመኛም «ያንተ ጆሮ ኩክ የለውም» ይሉታል። ኩክ በጆሮአችን ውስጥ የሚገኝ ሙጫ የሚመስል ነገር ነው። ኩክ ከበዛ ጆሮን ስለሚደፍን ለመስማት ያስቸግራል። የልጆቹን ልመና ለመስማት ግን የእግዚአብሔር ጆሮዎች የተከፈቱ ናቸው። እናት በብዙ ጫጫታ ውስጥ የልጇን ድምፅ ትለያለች። ጫጫታ በበዛበት በዚህ ዓለም ላይም እግዚአብሔር የልጆቹን ድምፅ ይለያል። የልጆቹን ጉድለት በሙላት፣ ልቅሶአቸውን በሳቅ፣ ትካዜያቸውን በደስታ ሲለውጥ ጸሎታቸውን ይሰማል። በገበያ ስፍራ፣ በጎዳናም እየጸለይን ስንንቀሳቀስ እግዚአብሔር ይሰማናል። እኛ ለመጸለይ ካልቸገረን እግዚአብሔር ለመስማት አይቸገርም። በብዙ ጫጫታ ውስጥ እግዚአብሔር የልጆቹን ድምፅ ይሰማል።

ገበሬው ዘሩን ሲዘራ በቤት የተቀመጠውን እህል አውጥቶ በሜዳ ይበትነዋል። የዘር ወቅት ከላይ ዝናብ ከሥር ማጥ ያለበት አስጨናቂና አሳዛኝ ወቅት ነው። ወቅቱም ብዙ ስጋትና ጨለማ ያለበት ነው። የዘሩ መከር ሲደርስ ግን ጨለማው በብርሃን፣ ማጡ በለምለም ሣር፣ እንባው በሳቅ፣ ዘሩ በብዙ ፍሬ፣ ችግሩ በበረከት ይተካል። ይህ የጸሎት ምሳሌ ነው። እልፍኛችንን ዘግተን፣ በድብቅ በዳዬ ሄደን፣ በዕንባ በጭንቀት ተውጠን የጸለይነው ጸሎት መከሩ ሲደርስ ታላቅ ደስታ መንፈሳዊ ግብዣ ያለበት ነው። ነቢዩ ዳዊት ይህን ሲገልጥ:- *«በልቅሶ የሚዘሩ በደስታ ይለቅማሉ። በሄዱ ጊዜ፥ ዘራቸውን ተሸክመው እያለቀሱ ተሰማሩ! በተመለሱ ጊዜ ግን ነዶአቸውን ተሸክመው ደስ እያላቸው ይመጣሉ»* (መዝ. 125፥ 5-6) ብሏል። መከራው በራሱ ጊዜ ያልፋል ብለው የማይጸልዩ ነገር ግን የጊዜን ቸርነት የሚጠባበቁ ሰዎች ጊዜ የእግዚአብሔር አገልጋይ እንጂ ጊዜ በራሱ ሰጪ ነሺ አለመሆኑን ተረድተው ምነው በጸለዩ! ምነው በተባረኩ!

- ጸሎት ዘር ነውና መከር አለው።
- ጸሎት እንባ ነውና ሳቅ አለው።
- ጸሎት ትግል ነውና ድል አለው።
- ጸሎት ጩኸት ነውና መልስ አለው።
- ጸሎት መተንፈስ ነውና ሕይወት አለው።
- ጸሎት ንግግር ነውና ማስተዋል አለው።



- ጸሎት መራቆት ነውና ጸጋ አለው።
- ጸሎት መንበርከክ ነውና ማሸነፍ አለው።

በየዕለቱ የምናገኘው የጸሎታችን መልስና ተአምራት የተሞላው የእግዚአብሔር ሥራ የእግዚአብሔርን መኖር የሚመሰክር ሲሆን የእኛ ንም እምነትና መደገፍ ዕለት ዕለት የሚጨምር ነው። እኛ የምናይበትን ዓይን የፈጠረ እግዚአብሔር ያያል። እኛ የምንስማበትን ጆሮ የፈጠረ ጌታ ይሰማል። እኛ የምንራራበትን ልብ የፈጠረ አምላክ ይራራል። እርሱ ጸሎትን ሰምቶ መመለሱ የህልውናው ክብር ነው። ጸሎታችንን የሚሰማው ስለ ቸርነቱ እንጂ ስለ እኛ ብቁነት አይደለም። የማንንም ጸሎት ሰምቶ እንዳልሰማ አያልፍም። የማንንም ልመና አይንቅም። ለፈለጉት ሁሉ የሚገኝ፣ ለለመኑት ሁሉ የሚቸር ደግ አምላክ ነው።

ብዙ ጊዜ ጸሎታችን እግዚአብሔርን ለማስረዳት ስለሚሞክር ጣዕም ያጣል ብለናል። እግዚአብሔር ከእኛ በላይ የችግሩን ምንነት ያውቃል። ጸሎታችን እንዲራራልን መማፀኛ እንጂ እግዚአብሔር እንዲገባው የምናደርግበት ማብራሪያ በፍጹም አይደለም። እርሱ እንድንሰማ ጆሮን የፈጠረ ነውና የሚለምኑትን ይሰማል። ከአሕዛብ ጣኦታት የሚለየው በሕያውነት እኛን መስማቱ ነው (መዝ. 115 በዕብራይስጥ ቊ. 5)።

በእውነት ዛሬ እየበላን ያለነው በረከት የረሳነውን የጸሎት መልስ ነው። በልጅነታችን ወራት ወይም ከዓመታት በፊት የጸለይነውን እኛ ረስተነዋል። የስማው እግዚአብሔር ግን ስለማይረሳ የከረመ በረከት፣ ከተጠመቀ የቆየ የወይን ጠጅ ያቀርብልናል። በነቢዩ በኢሳይያስ:- *«የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ለሕዝብ ሁሉ በዚህ ተራራ ላይ ታላቅ የሰባ ግብዣ፥ ያረጀ የወይን ጠጅ፥ ቅልጥም የሞላባቸው የሰቡ ነገሮች፥ የጥሩና ያረጀ የወይን ጠጅ ግብዣ ያደርጋል»* (ኢሳ. 25፥6) ይላል።

ለእግዚአብሔር የዘመናት ርዝማኔ ጸሎታችንን አያስረሳውም። ለዚህ ታላቅ ምሳሌ የሚሆነን የእግዚአብሔር ሰው ነቢዩ ሙሴ ነው። ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ብዙ ጊዜ ቃል ለቃል የተነጋገረ ነቢይ ነው። ይህ ሙሴ የእግዚአብሔርን ድምፅ በጆሮው መስማት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ማየት ፈለገ። ይህ ናፍቆቱ በእግዚአብሔር ፊት የተወደደ ቢሆንም እግዚአብሔር ግን በባሕርይው አይታይምና ልመናው ለጊዜው መልስ አላገኘም። እግዚአብሔር የማይታየው ስለ ሌለ ወይም አፋር ስለሆነ አሊያም ስለሚፈራ ሳይሆን ፍጡር በግርማ

መለኮቱ፣ በክብረ መንግሥቱ አይቶት መኖር ስለማይችል ነው:: ቃሉ እንደሚናገር እግዚአብሔር *«የሚያጠፋ እሳት ነውና»* (ዕብ. 12፥29፤ ዘዳ. 4፥24):: የፀሐይን ብርሃኗን እንጂ ራሷን ፀሐይን ማየት እንደማንችል ከፀሐይ ሰባት እጅ የሚያበራውን እግዚአብሔርንም በመለኮታዊ ክብሩ ማየት በፍጹም አይቻለንም:: መላእክቱ ሁሉ የሚያመልኩት በማየት ሳይሆን በማመን ነው:: ሊያዩት ስለሚናፍቁ በእርሱ መልክ የተፈጠረውን አዳምን ባዩ ጊዜ ተደስተዋል::

እግዚአብሔርም ክብሩን ለማየት ለናፈቀው ለሙሴ *«... ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም ...»* (ዘፀ. 33፥17-23) አለው:: እግዚአብሔር ለሙሴ ይህን ምላሽ ቢሰጠውም ልመናውን ግን አልረሳበትም:: ወንድሙ አሮንና እህቱ ማርያም ሙሴን በተቃወሙ ጊዜ እግዚአብሔር ለሙሴ ተከራከረ:- *«ቃሌን ስሙ በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር፥ እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጥለታለሁ፥ ወይም በሕልም እናገረዋለሁ:: ባሪያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም፤ እርሱ በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው:: እኔ አፍ ለአፍ በግልጥ እናገረዋለሁ፥ በምሳሌ አይደለም፤ የእግዚአብሔርንም መልክ ያያል ...»* (ዘኁ. 12፥6-8)::

ሙሴ ሞቷል ስለዚህ ማንም አይታዘበኝም ብሎ እግዚአብሔር የሙሴን ልመና አልተወውም:: እግዚአብሔር ጸሎትን የሚመልሰው ስለ ሰጠው የተስፋ ቃል ሲሆን ተስፋውንም ሞት እንኳ አያግደውም:: እኛ ሞትን እንፈራለን፣ እግዚአብሔር ግን ከሞት እንኳ አሥነሥቶ ተስፋውን ሊፈጽምልን ስለሚችል ሞትን አይፈራም::

በደብረ ታቦር ከተጸለየ አንድ ሺህ ዓመት ያለፈውን ጸሎት እግዚአብሔር ሲፈጽም እናያለን:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ተገልጦ የማይታየው ባሕርዩ ታየ:: የማይዳሰሰውና የማይደፈረው ማንነቱ በሥጋ ትሑት ሆነ:: በዚህ ጊዜ የሙሴን ጸሎት አስታወሰ:: ሙሴን ከመቃብር አስነሥቶ ፊቱን እንዲያይ አደረገው:: ደብረ ታቦር ሥጋውን ብቻ በማየት መለኮታዊ ጌትነቱን ማየት ላልቻሉ ደቀ መዛሙርት ክብሩን የገለጠበት ደግሞም መለኮት ብቻ ሆኖበት ሊያየው ላልቻለው ሙሴ ሰው ሆኖ የታየበት ነው (ማቴ. 17፥1-13)::

በአንዳንድ አገሮች ላይ ዛሬ የሚታየው በረከት የቀደሙት አባቶቻቸው ያለቀሱትና የጸለዩት የጸሎታቸው መከር እንደሆነ እናውቃለን:: አሁን ያለው ትውልድ ይህ በረከት የማይገባው ቢሆንም እግዚአብሔር ግን የአባቶቻቸውን ዕንባ አስቦ የከረመ በረከት ያበላቸዋል:: ልመናችን በዘመናችን ብቻ ሳይሆን ከዘመናችንም ውጭ በሌለንበትም ዘመን ይፈጸማልና ተግተን የጸሎትን ዘር መዝራት



ያስፈልገናል:: «የሚያየኝ ሞቷል ማን ይታዘበኛል?» የሚል ሰው ነው:: እግዚአብሔር እንደ ሰው ለትዝብት ሳይሆን ለታማኝነቱ ይሠራል:: የጸለየው ሰው በሕይወተ ሥጋ ባይኖርም ጸሎቱን ይፈጽማል:: ደግሞም ዘመናት ቢረዝሙ እግዚአብሔር ጸሎታችንን አይረሳም::

በደብረ ታቦር ሙሴን ብቻ ሳይሆን ኤልያስንም እናገኛለን:: ኤልያስ በስማርያ ከተነሡት ታላላቅ ነቢያት አንዱ ነው:: ያለ ፍርሃት ንጉሡንና ሕዝቡን የገሰፀ፣ ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ሰማይ ዝናብ እንዳይሰጥ የገዘተ፣ በአምላኩ ተወራርዶ ዝናብ ያመጣ ታላቅ ነቢይ ነው:: ንጉሡና ሕዝቡ እግዚአብሔር እርሱ አምላክ ነው ብለው ለእግዚአብሔር ሰገዱ:: ኤልያስ ግን ይህ በሆነ ማግስት የንግሥቲቱን ዛቻ ሰምቶ የብርታቱ ጉልበት ተሰበረ:: ተስፋው ተመታ:: የሚሄድበትን ሳያውቅ ጭው ባለው በረሃ መንከራተት ጀመረ:: ትልቅ ነገር ያየ ቢሆንም በትንሽ ነገር እጅ ሰጠ:: በመጨረሻም ሞትን ለመነ (1ነገሥ. 19፥4):: ኤልያስ ሞትን ሲለምን ብቻዬን ቀረሁ ብሎ ነበር:: ነገር ግን እርሱ የማያውቃቸው ሰባት ሺህ ድብቅ ሠራዊቶች ነበሩ (1ነገሥ. 19፥18):: የምሠራው የለም ብሎ ቢያስብም ከእርሱ በኋላ የሚተካውን ነቢይና የእስራኤልን ንጉሥ መቀባት ነበረበት (1ነገሥ. 19፥15-17):: ይህን ታላቅ ሥራ አስቀምጦ ሞትን መመኘቱ ይገርማል:: እግዚአብሔር ግን የኤልያስን ጸሎት በፈቃዱ አርሞና አትርፎ ሰማው:: እንዲሞት ሲለምን እግዚአብሔር ሞትን ሳያይ ነጠቀው (2ነገሥ. 2፥11):: ልመናውን በቀጥታ አልፈጸመለትም ፈቃደ እግዚአብሔር አረመችለት:: እግዚአብሔርም አትረፍርፎ ሰማው:: በደብረ ታቦር ኢየሱስን ለማየት ከሙሴ ጋር እድምተኛ ሆነ:: የሕያዋንና የሙታን ጌታ የሆነውን ኢየሱስን አየው:: እግዚአብሔር ልመናችንን የሚመልሰው በለመነው ልክ ሳይሆን አትርፎ ነው:: ጳውሎስ ይህን ሲገልጥ:- *«እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው፥ ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን»* (ኤፌ. 3፥20-21) ብሏል::

አንዲት እንግሊዛዊት ፀሐፊ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን የማይሰማ ለሚመስላቸው ሰዎች:- «አንድ ሳጥን አዘጋጁ:: ጸሎታችሁን ጽፋችሁ በዚያ ሳጥን ውስጥ ክተቱ:: በዓመቱ ብትከፍቱት ልመናችሁ ሁሉ ተፈጽሞ ታገኙታላችሁ:: ጸሎታችሁን እግዚአብሔር ያልሰማችሁ የሚመስላችሁ ስለምትረሱት ነው» ብላለች:: የታወቁ ክርስቲያኖች የጸሎት መዝገብ እንደ ነበራቸው ይታወቃል:: በአጠገቤም

የማውቃቸው ክርስቲያኖች ልመናቸውን በጽሑፍ ያስፍሩታል:: አብረን ስናገላብጠው እግዚአብሔር ልመናቸውን በአስደናቂ ሁኔታ ፈጽሞት እናገኛለን:: ጸሎታችንን የምናሰፍርበት መዝገብ ያስፈልገናል:: የዚህ መዝገብ ጠቀሜታው ብዙ ነው:: እግዚአብሔር አስተውለን ስንጸልይና የጸለይነውን ስናስታውሰው የከበረና ታላቅ ነገር ያደርግልናል:: በሁለተኛ ደረጃ የጸሎት መዝገባችንን ስናገላብጥ የተመለሰ ጸሎታችንን መመልከት እምነትን ይጨምርልናል:: ዳግመኛም ለጸሎትም ያበረታናል::

፪

## እግዚአብሔር ጸሎትን ይመልሳል

አብርሃምን በመቶ ዓመቱ የልጅ አባት አድርጎታል:: ሣራን አለምልሟታል፣ የጥርጣሬ ሳቋን እውነተኛ ሳቅ አድርጎላታል:: ሃናን ከንቀት አድኗታል:: ዳዊትን ከእረኝነት ወደ ዙፋን አውጥቶታል:: የዘካርያስንና የኤልሳቤጥን ነቀፌታ አስወግዷል:: እነዚህ ሁሉ ሕያዋን ምስክሮች «እግዚአብሔር ይሰማል» ይሉናል:: ስለዚህ ተግተን መጸለይ ይኖርብናል:: ባንጸልይም ፀሐይ ይወጣል፣ አየር ይነፍሳል፣ ሌሊቱ ይነጋል:: ካልጸለይን ግን የማንቀበላቸው በረከቶች አሉና ተግተን መጸለይ ይገባናል:: እግዚአብሔር ዛሬም የብዙ ልጆቹን ጸሎት እየመለሰ ነው:: እኛ አገልጋዮች የእግዚአብሔር ጠበቆች ሳንሆን ምስክሮች ነን:: ደካሞችን ብርቱ፣ ሞኞችን ጠቢብ፣ አንካሶችን ጽኑ፣ ጎባጦችን ነጻ፣ ሀዘንተኞችን ሳቂታ ሲያደርግ፤ አልቻልንም ባሉበት ነገር ለብዙዎች መቻል ሲሰጥ አይተናል:: በሰዎች ኑሮ ላይ ብቻ ሳይሆን የእኛንም ቤት በጸሎት ሲያከናውን ተመልክተናል:: እግዚአብሔር የማንም ጸሎት ባለ ዕዳ አይደለም::

አንድ ሰው «በጸሎት ወደ እግዚአብሔር አደባባይ መጥተን ባዶ እጃችንን አንመለስም:: ጸሎታችንን ለመመለስ ጊዜው ባይደርስ እንኳ ከእግዚአብሔር አደባባይ እግሮቻችን በረከት ይዘው ነው የሚወጡት:: እግዚአብሔር ልጆቹን በነጻ መስደድ አይሆንለትም» ብሏል:: ሌላውም ሰው:- «በችግራችንና በመፍትሔው መካከል ያለው ርቀት ከጉልበታችን እስከ መሬት ድረስ ነው» ብሏል::



# ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት

## የጸሎት ጌጥ

*«ጸሎት የጸሎት ቃላት ብቻ ሳይሆን የጸሎት መንፈስ ያስፈልገዋል::»*

የጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች የተጻፈው ብዙ የእውነት ፈርጦች ያለበት ነው:: ከዚያ ውስጥ አንዱ *«ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና»* (ፊልጵ. 2፥13) የሚለው ነው:: ቃሉ ግልጽ ነው ምኞታችሁም፣ ተግባራችሁም የእናንተ አይደለም ነው የሚለን:: ቅን አስተሳሰብ፣ ጨዋነት፣ በጎ ዕቅድ በውስጣችን ስላለ ኩራት ይሰማን ይሆናል:: ነገር ግን ይህን በውስጣችን ያስቀመጠ እግዚአብሔር ነው:: የተመኙትን ማድረግም በእግዚአብሔር ነው:: ከዓመታት በፊት እንዲህ እያልኩ እጸልይ ነበር:- «ጌታ ሆይ የእኔ አሳብ ሆኖ አያውቅም፤ በአሳቤ አንተ አስብበት:: የእኔ ቃል ፈውሶ አያውቅም፤ በንግግሬ አንተ ተናገርበት:: የእኔ ጅምር አልቆ አያውቅም፤ በጅምሬ አንተ ፈጽምበት::»

የፊልጵስዩስ መልእክትን የሚጋራ ሌላም ክፍል አለ:- *«ሳይጠሩ እመልስላቸዋለሁ፥ ገናም ሲናገሩ እሰማለሁ»* (ኢሳ. 65፥24):: ለእስራኤል ከተሰጡ ድንቅ ተስፋዎች አንዱ ይህ ነው:: ተስፋው የሚመለከተው የጸሎት ሰዎችን ነው:: ተስፋው ጸሎት አያስፈልግም አይደለም የሚለው:: ሕፃን ልጅ ገና ቃላት ሳያዋቅር ወላጆቹ የሚፈልገውን አውቀውለት እንደሚያደርጉ እግዚአብሔርም ፍላጎታችሁን የማውቀው ጸልያችሁ ስትፈጽሙ ሳይሆን ገና ስትዘጋጁ ነው ማለቱ ነው:: ገና ለመጸለይ በራችንን ስንዘጋ፣ ለመስገድና ለመንበርከክ እጃችንንና ጉልበታችንን ስናዘጋጅ እግዚአብሔር አድምጦናል:: ከዚያ በኋላ ያለው ለእኛ እንደ ጸለይን እንዲሰማንና እንድንደሰት ነው:: አንድ ልዩና የሚያምነን ወዳጅ መለመን ስንጀምር ልመናችንን ገና ሳንጨርስ በልቡ ፈርዶ ይሰጠናል:: ቃላትን አስጨርሰው የሚሰሙን ራቅ ያሉ ሰዎች ናቸው:: እግዚአብሔር ግን ገና ሳንጠራው ይመልስልናል፣ ገና ስንናገር ይሰማናል:: እርሱ የቅርብ አምላክ ነውና (ፊልጵ. 4፥6)::

ጸሎትን የሚያስውቡ ብዙ ጌጦችና ዘርፎች አሉ:: እነዚህም የጸሎት ጣምራዎች ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ:: እነዚህ ጣምራዎች ከጸሎት ጋር ጋርዮሽ ሲሆኑ ኃይል፣ ጣዕምና ድል አላቸው:: እነርሱም:-

* ጸሎትና ጾም
* ጸሎትና ዕንባ
* ጸሎትና ምግባር
* ጸሎትና ዜማ
* ጸሎትና ጽሞና ናቸው::

## ጾም

ጾም መጽሐፍ ቅዱሳዊ የአምልኮ መሣሪያ ነው:: እንዲህ የምንለው ጾምን ስው ሠራሽ ወይም የሃይማኖት ተቋማት ሥርዓት አድርገው የሚመለከቱ ሰዎች ስላሉ ነው:: በብሉይና በሐዲስ ኪዳን የነበሩ የእግዚአብሔር ሰዎች በጾምና በጸሎት መሣሪያ እንደ ተጠቀሙ እናነባለን:: እነዚህ የእግዚአብሔር ሰዎች ጾምና ጸሎትን ለተለያየ ግዳጅ ማስፈጸሚያ ተጠቅመውበታል:: የመጀመሪያው ለታላቅ ተልእኮ መግቢያ አድርገውታል:: ሙሴ ኦሪትን ሲቀበል ዐርባ ቀንና ዐርባ ሌሊት በደብረ ሲና ጾሟል (ዘፀ. 34፥28):: ዛሬም ከእግዚአብሔር ዘንድ መለኮታዊ ምሪትን ለመቀበል የሚሹ ምእመናን በጾምና በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ይሆናሉ:: ሙሴ በጾምና በጸሎት በመቆየቱ ኦሪትን ተቀበለ፣ ፊቱ በራ:: እንዲሁም እውነተኛ ጾምና ጸሎት በምናደርግበት ጊዜ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃላት ለራሳችንና ለወገኖቻችን እንይዛለን:: ደስታችንም የላቀ ይሆናል:: የመሸነፍ ምልክት የሆነው የፊት መከፋት አይታይብንም:: ድግሷን እንደ ተወጣች ሴት፣ ዘመቻውን እንደ ፈጸመ ወታደር፣ ራእዩን እንዳሳካ ንጉሥ ብሩህ እንሆናለን::

የብሉይ ኪዳን መካከለኛ ሙሴ ኦሪትን ሲቀበል በታላቅ አምልኮ ውስጥ እንደ ነበረ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ የሚሆን ኢየሱስ ክርስቶስም (ዕብ. 12፥24) አዲስ ኪዳንን ከመስበኩ በፊት ዐርባ ቀንና ዐርባ ሌሊት ጾሟል (ማቴ. 4፥1-11)::

ጾሙም በታላቅ ጸሎትና በእግዚአብሔር ቃል የተቀናጀ ስለ ነበር የሰይጣንን ተግዳሮት ድል ነሥቶበታል:: አዳምና ሔዋን በገነት ውስጥ የወደቁባቸውን ፈተናዎች ጌታ በበረሃ ውስጥ አሸነፋቸው:: በጾምና



በጸሎት ከቆየ በኋላ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች እያለ መስበክ ጀመረ::

ደቀ መዛሙርቱም የሙሴንና የክርስቶስን አብነት ተከትለው አገልጋዮችን ከጾምና ከጸሎት በኋላ ይሾሙ ነበር (ሐዋ. 13፥3):: የወደፊት የአገልግሎት መንገዳችንን ከምንጠርግበት መንገድ አንዱ ጾምና ጸሎት ነው:: ወደ ታላቅ ተልእኮ ከመግባታችን በፊት ጾምና ጸሎት ማድረግ ተገቢ ነው:: ብዙ መንፈሳውያን ወገኖቼ ወደ ትዳር ከመግባታቸው በፊት፣ ልጅ ከመውለዳቸው በፊት የጾም የጸሎት ጊዜ ሲይዙ አይቻለሁ:: ከፊታችን ያሉትን የአገልግሎት ጊዜዎች በጾምና በጸሎት ሆነን ስናስረክብ ልዩ የሆነ ድል እናገኛለን:: ለዚህም ሕያዋን ምስክሮች ነን:: አንድ ወንድሜ ከዓመታት በኋላ አገኘሁትና በጣም እንደሚፈልገኝ ነገረኝ:: በመቀጠልም:- «ባለቤቴ አርግዛለች፣ እኔ እግዚአብሔርን ሳላዝነው ኖርኩኝ:: እኔ የምወልደው ደግሞ እንዲያሳዝነው አልፈልግምና አብረን ጾም ጸሎት እንድንይዝ እለምንሃለሁ» ብሎ ተማጸነኝ::

ጾምና ጸሎት ለግልና ለብሔራዊ ንስሐ ትልቅ መሣሪያ ነው:: ግለሰቦች የኃጢአት ሸክም ሲከብዳቸው ስርየትን ለመለመን ኃይልን ለመጠየቅ ጾምና ጸሎትን ይጠቀማሉ:: በአገር ላይም መዓትና መቅሰፍት ሲመጣ በጾምና በጸሎት በምህላ ንስሐ ይገባሉ:: የነነዌ ሰዎች በዚህ መንገድ የቀረበውን መዓት ሲያርቁ፣ የራቀውን ምሕረት ሲያቀርቡ እናነባለን (ዮና. 3.)::

በየዘመናቱ የነበሩ የእግዚአብሔር ሰዎች ለመንፈሳዊ ዕድገት ጾምና ጸሎትን ያዘወትሩ እንደ ነበረ ታሪካቸው ይነግረናል:: በጾም የታገዘ ጸሎት ወደ ክርስቶስ ሕማምና መከራ የሚወስድ መንገድ፣ የዕንባን ምንጭ የሚነድል መፈንቀያ፣ መሰበርንና ልባዊ ትሕትናን የሚሰጥ ነው:: በጾም ሰዓት ያለው ጸጥታ ከእግዚአብሔር ህልውና ጋር ለማውጋት በብርቱ ይጠቅማል::

ጾም ትርጉሙ በተሰበረ ልብ ሆነን ወደ እግዚአብሔር መቅረብና መጸለይ ነው:: በጾማችን ቀን መብልን ሁሉ፣ በጾማችን ወራት ኃይል ሰጪ ምግቦችን የምንተወው ሥጋችንን በማድከም በትሕትና ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ እንዲያስችለን ነው:: የነፍስ ተመስጦ ከበላይ፣ ሥጋ ከታች የሚሆንበት፣ እየደከምን የምንበረታበት ነገር ቢኖር ጾም ነው:: ምግብን የምንተወው ኋላ የምንመገበውን መብል እንደ ርኩስ ቆጥረን ሳይሆን ሥጋችንን ለማድከምና የቍርስ የምሳችንን ወጪ ለተራቡት ለመስጠት ነው:: ጾም ቍጠባ አይደለም:: የረሀብተኞች

ረሀብ እንዲሰማን በፈቃዳችን የምንራብበትና ለሌሎች የምናካፍልበትም ነው።

የጾም ዓላማው ይህ ብቻ አይደለም። ከእግዚአብሔር ጋር ብርቱ ጉዳይ ይዞ ራስንና አገርን ይቅር ማሰባል ነው። በመንፈሳዊው ዓለም ጾም ጸሎት እንደ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ይቆጠራል። ስለዚህ ወደ ጾምና ጸሎት ከመግባታችን በፊት ርእስ መያዝ፣ ይቅር መባባልና ንስሐ መግባት ግዴታ ነው። ጾም ሕያው ማዕድ እንጂ ባህል ወይም ልማድ አሊያም ታሪክ ማዘከሪያ አይደለም። ጸሎት ብቻውን ሊቀርብ ይችላል፣ ጾም ግን ያለ ጸሎት በፍጹም ሊቀርብ አይችልም። በእውነት ጸሎት ከጾም ጋር ሲገናኝ ኃይል አለው። ጣዕሙም አይሰለችም።

## ዕንባ

በዓለም ላይ ብዙ ቋንቋዎች አሉ። በድምፅ ከሚገለጠው ቋንቋ ባሻገር የምልክት፣ የሥዕል ቋንቋዎች አሉ። ከዚህ ሁሉ በላይ በቋንቋ የማይግባቡ ሰዎችን የሚያግባባ አንድ መንፈሳዊ ቋንቋ አለ። እርሱም ፍቅር ነው። ይህ ብቻ አይደለም ዕንባም ቋንቋ ነው። ጸሎታችን በልብ፣ በቃል፣ በጩኸት፣ በእንብርክክ በመዳህ ሊገለጥ ቢችልም ዕንባ ግን ትልቅ መግለጫው ነው።

ከቃል በላይ የሆኑ ነገሮችን የምንገልጥበት ቋንቋ ዕንባ ነው። የጠለቀ ስሜትን ለመግለጥ ቃላት አቅም የላቸውም። ዕንባ ግን ቃላትን ተክቶ ያለ ቃላት ይናገራል። በጣም ደስ ሲለንና በጣም ስናዝን የመግለጫው ቋንቋችን ዕንባ ነው። ዕንባ የጥልቅ ሀዘንና የጥልቅ ደስታ መግለጫ ነው። ጸሎትን ጣዕም ከሚሰጡት ነገሮች አንዱ ዕንባ ነው። ዕንባን ከማንም በላይ የሚያይ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር በኃይሉ ብዙ ውቅያኖስን በአንድ እርምጃ መሻገር ይችላል። አንዲት ዘለላ ዕንባን ግን አያልፍም። በእውነት ዕንባ ድምፅ የሌለው መሣሪያ ነው።

ዕንባ ነፍስን የሚያጠራ ውኃ ነው። ልመናንን በእግዚአብሔር ፊት ለማፍሰስ ዕንባ አጋዥ ነው። በጌታ ፊት ደንዳናውን ልባችንን ለማቅለጥ ዕንባ እሳት ነው። በመለኮት ፊት ራሳችንን ለማዋረድ ዕንባ ኃይል ነው። ስለ ሌሎች ለመራራት ዕንባ ጭካኔን የሚጥል ነው። ቍርጥ ልመናን ለማቅረብ ዕንባ መንገዱ ነው። የዕንባ ስጦታ ካለን ማበርታት፣ ከሌለንም እንዲሰጠን መለመን ይገባናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዕንባ ዝናብ የታጠቡ ሰዎችን እናነባለን። ዕንባቸውን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር የሰጣቸውን ፈጣን መልስም እናነባለን



(1ሳሙ. 1፥12-18)። ወዴት እንደሚለቀስ ለሚያውቁ ዕንባ ፍትሕን ያወርዳል። ጸሎት ከዕንባ ጋር ኃይል አለው።

የቀደሙት አባቶች «ወንድ ልጅ ካለቀሰ፣ ሴት ልጅ ከሰገደች እግዚአብሔር ይለመናል» ይላሉ። ወንድ ዕንባ ይቸግረዋል። ደራሲው እንዳሉት ሴት ልጅ ደግሞ «ዕንባ ናና ሂድ የምትለው ሎሌዋ ነው።» ወንድ ልጅ መስገድ ወይም መሸነፍ አይከብደውም። ሴቶቹ በሚነግሩት የውሸት ታሪክ እንኳ አሸከር ሆኖ ይኖራል። ሴት ልጅ ግን መሸነፍ አትፈልግም። አቅም አንሷት የፈለገችው ባይሆን እንኳ ዘመኗን በሙሉ አትቀበልም። ለዚህ ነው ደጋጎቹ አባቶች «ወንድ ልጅ ካለቀሰ፣ ሴት ልጅ ከሰገደች እግዚአብሔር ይለመናል» ያሉት።

## ምግባር

ጸሎት የምግባር ኃይል እንጂ የምግባር ምትክ አይደለም። ጸሎታችን ኃይል ያለው እንዲሆን ከመልካም ምግባር ጋር መታገዝ አለበት። በጎ እንዲደረግልን ስንለምን በጎ ማድረግንም እየተለማመድን ሊሆን ይገባዋል። የማንችለውን እንዲፈጽምልን ስንጠይቅ የምንችለውንም በመፈጸም ሊሆን ይገባል። ይልቁንም እግዚአብሔር የእኛን ልመና ለመስማት ለጎረቤታችን ችግረኛ ያለንን የርኅራኄ ስሜት ማድመጥ ይፈልጋል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዋና ዋና ከሆኑት የአምልኮ መንገዶች አንዱ በጎ ምግባር መሆኑን ተናግሯል። በማቴ. 6. ላይ እንደምናነበው ከጾምና ከጸሎት ጋር ምጽዋት አምልኮ መሆኑን እናነባለን። ከጾምና ከጸሎት በፊትም ምጽዋት ቀዳሚ ሆኖ ተጠቅሷል። በብሉይ ኪዳን ዘመን አምልኮ በመሥዋዕት አማካይነት ይካሄድ ነበር። በአዲስ ኪዳን ካሉት መንፈሳዊ መሥዋዕቶች አንዱ ሌሎችን መርዳት ወይም ካለን ላይ ማካፈል ነው (ዕብ. 13፥16)።

ከዕለታት በአንዱ ቀን ለጸሎት ወደ ቤተ ክርስቲያን ስሄድ አንድ ገንዘብ የሚለምነኝ ልጅ ሲመጣ ልቤ ሸሸው። ይህ ወጣት ሣንቲም አይቀበልም። አንድ ብርም ስሰጠው ብዙ ቀን አኩርፎኛል። ሳይሰናበተኝ ሄዷል። ይህ ወጣት ታዲያ ወደ እኔ ሲመጣ ልቤ ገሸሸ አለው። ወዲያው በልቤ፡- «አንተ ልትለምን እየሄድክ የሚለምንህን ለምን ትሸሻለህ? አንተ የምትለምነው እርሱ የሚለምንህን መጠን አይደለም። በዚህ አትመለስም» አለኝ። ወዲያው የእግዚአብሔርን

ይቅርታ ስመንኩኝ:: ያንን ወንድሜን እንደ እግዚአብሔር እንግዳ አስተናገድኩኝ::

በየዕለቱና በየቦታው እንድንሠራው የሚጠብቀን ብዙ በጎ ሥራ በዝቷል:: በጎ ሥራ የአንድ ታላቅ ቀን አጋጣሚ ሳይሆን በየዕለቱ በአጠገባችን ያለ ነገር ነው:: ያዘኑትን ማጽናናት፣ በክፉ ሥራ ለጠፉት ምክር መለገስ፣ በልባቸው የተሸነፉትን አይዟችሁ ማለት፣ ካለን ላይ ቀንሰን ለተራበ ማብላት፣ ... በየዕለቱ የከበበን ተግባር ነው:: ጸሎት የአንደበት ሥራ ብቻ ሳይሆን የቲግባርም ፍሬ ነው:: ብዙ መጸለይ መቻል ጥቂት በጎ ነገር መሥራት አለመቻል በጣም ምስኪንነት ነው:: ትልቅ መሐን ምግባረ ቢስ (ፍሬ) የሌለው ነው::

ብዙ ጊዜ እውነተኛውን ደሃ መለየት አልቻልንም እያልን ስስታችንን ምክንያታዊ ለማድረግ እንፈልጋለን:: እውነተኛውን ችግረኛ መለየት መልካም ቢሆንም እግዚአብሔር ግን የሚያየው ለስማነው የችግር ድምፅ ልባችን የሰጠውን ርኅራኄ ነው:: እግዚአብሔር የሚያየው «ራብኝ» ለሚለው ቃል ልባችን የሰጠውን ምላሽ እንጂ ስውዬው ይገባዋል አይገባውም የሚለውን አይደለም:: ምጽዋታችንም ዘርና ሃይማኖትን የለየ መሆን በፍጹም የለበትም:: ይልቁንም መለመን ያፈሩትን የሚያይ ጥልቅ ዓይን ያስፈልገናል:: የአገራችን ሰው:-

«በካባ ውስጥ ያለ ረሀብ፣
በድሪቶ ውስጥ ያለ ጥጋብ፣
በጎፈሬ ውስጥ ያለ ጽድቅ አይታወቅም» የሚለውን ማስብ አስብን::

## ዜማ

በስሆሳስ ወይም በፀጥታ ሊቀርቡ ከማይችሉ የአምልኮ መንገዶች አንዱ ዜማ ነው:: ዜማ ድምፅ ማውጣት ስለሚጠይቅ በጸሎት የሚደረግ ምስክርነት ነው:: ዜማ ኃይል አለው:: በቅድስና ቃላት የከበረ ዜማ ደግሞ ከዚህ አዳፋ ዓለም ኅሊናን ወደ ንጹሑና ሰማያዊ ዓለም የመንጠቅ ኃይል አለው:: ብኩንና ጽኑ የሚሆነውን የሰው ልብ ዜማ ያሸንፈዋል:: ራሱንና አካባቢውን ረስቶ በተመስጦ በመንፈሳዊ ክንፍ እንዲበርር ያደርገዋል:: ጸሎትን እያስዋበ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛል:: ዜማ ጸሎተኛውን ከመላእክት ጋር የእግዚአብሔርን ዙፋን እንዲከብብ ያደርገዋል::



ዜማ የደረቀ አጥንትን የሚያለመልም መንፈሳዊ ቅባት ነው:: በጣዕመ ጸሎት ረጅም ሰዓት ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር ዜማ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው:: ኅሊናን ሰብስቦ በተሰበረ ልብ ለመማለድ ዜማ አጋዥ ነው:: ዜማ የዕንባ ማጠራቀሚያውን ጋን ስለሚነካ ያ ድምፅ አልባ ቋንቋ (ዕንባ) መፍሰስ ይጀምራል::

ጸሎታችንን በቃላት ብቻ ሳይሆን እየጸለይን አሁን በሚመጡልን ዜማዎች ማቅረብ ወደ ጣዕመ ጸሎት ይወስዳል:: ይህ ዜማ ከዚህ በፊት የማናውቀው ቀይቶም የምንረሳው መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠን ዜማ ነው:: ዜማው እንጉርጉሮ የሚመስል ልብንና አፍን የሚያስተባብር መንፈስን የሚነካ የዕንባን ምንጭ የሚነድል እንደሆነ የጸሎት ሰዎች ያውቁታል:: እየተናገርንለት ያለው ዜማ የተደረሱ የዘማርያንን ዜማ አይደለም:: እርሱም መልካምና አስፈላጊ ነው:: እያነሣን ያለነው ግን ያለ ግጥም፣ ያለ ኖታ ሕግ የሚቀርበውንና ትኩስ ምግብ የሆነውን ዜማ ነው:: መንፈስ ቅዱስ ይህን መሻታችንን ካወቀ ዜማ ይሰጠናል:: ጸሎታችን በጸሎት መንፈስ እንዲሆን ይህ ዜማ ይረዳናል:: ልብ አድርጉ ጸሎት የጸሎት ቃላት ብቻ ሳይሆን የጸሎት መንፈስ ያስፈልገዋል:: ለዚህ ከሚረዱን ነገሮች አንዱ ዜማ ነው::

## ጽሞና

ጽሞና እግዚአብሔርን የመጠባበቅ ፀጥታ ማለት ነው:: ጸጥታ ስንል ትርጉሙ እንዳያንስብን ያሰጋል:: ድምፅ አልባ የሆነ ፀጥታ አለ:: ይህ ጸጥታ ግን ያስፈራል:: ጽሞና የምንለው ግን የእግዚአብሔርን ሀልውና የምናጣጥምበት የፀጥታ ጊዜ ነው:: ይህ ለመንፈሳዊ ዕድገትና ምሥጢራትን ለመመርመር ወሳኝ ነው:: ዓለም ባሕርይዋ ጫጫታ ነው:: በፀጥታ በምንሆንበት ጊዜ ከዓለም እንወጣለን:: ስለዚህ ዓለም ራሷ ትታየናለች:: አዲስ አበባ አዲስ አበባ ውስጥ ሆነን አትታየንም:: እንጦጦ ላይ ስንወጣ ግን በደንብ ትታየናለች:: ዓለም በዓለም ውስጥ ወይም በጫጫታዋ ውስጥ ሆነን አትታየንም:: ስንወጣ ግን በደንብ ትታየናለች::

እግዚአብሔር ከልጆቹ ጋር በሕያውነት ከሚገናኝባቸው መንገዶች አንዱ ጽሞና ነው:: እግዚአብሔር ለሚጠባበቁት ልዩ አምላክ ነው:: በእርጋታ ለሚቀመጡም ትልቅ መምህር ነው:: ስንጠባበቀው ያናግረናል:: የልባችንን መስታወት በደሙ እየወለወለ ማየት እንድንችል ያደርገናል:: ምሥጢራትን ይገልጥልናል:: የዘመንን ምልክት ይነግረናል:: የቃሉን ፍቺ ያበራልናል:: ሕይወታችን ግርግር የሞላበት የተዋከበ ከሆነ እግዚአብሔር ሊያናግረን አይችልም:: ፍቅር

ንጹሕ ጊዜ ይፈልጋል። እግዚአብሔር ፍቅር ነውና ያልተቀላቀለ ጊዜ ይፈልጋል። በፀጥታ ውስጥ አብሮን ይሆናል። እንዲህ ያሉ ጊዜዎችን በሕይወታችን ሲያጣ በደዌ ጥሎ በወኅኒ አስቀምጦ ብቻችንን ያገኘናል። ቀጣዩ ጉዞ እንዲታየን ፀጥታ ወሳኝ ነውና።

ከሕዝብ ጋር ከሚያገናኘን ተግባራችን መለስ ብለን ከእግዚአብሔር ጋር በፀጥታ መቆየት አለብን። ልብ በሉ የመኪና ጎማ ነፋስ የሚሞላው እየሄደ ሳይሆን ቆሞ ነው። ቆም ብለን ኃይልን መሞላት ግድ ነው። ነቢዩ ዳዊት በመዝሙር 1 ላይ ስለ ጽሞና ሲናገር፡- *«ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፥ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል። እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደ ተተከለች፥ ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ፥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል፤ የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል»* ይላል። «ያስባል» የሚለው ጽሞናን ወይም ማሰላሰልን የሚገልጥ ነው። ቃሉን በማሰላሰል ውስጥ ያለ ጽሞና ፍሬያማ ሕይወትን ከማምጣቱም ባሻገር ለተግባራችን ሁሉ መከናወንን ይሰጠናል። ተግባር የሚከናወነው በመንከውከው ሳይሆን በጽሞና ለእግዚአብሔር በማስረከብ ነው።

በነቢዩ በኢሳይያስ፡- *«እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ፤ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፤ ይሮጣሉ፥ አይታክቱም፤ ይሄዳሉ፥ አይደክሙም»* (40፥31) ይላል። ንስር ኃይሉ ሲደክምበት ጭው ካለ ገደል ላይ ተገልሎ ለአርባ ቀናት ያህል ይቀመጣል። ከዚያ በኋላ ኃይሉ ታድሶ በከፍታዎች ላይ መብረር ይጀምራል። እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁም እንዲሁ በታደሠ ኃይል እንደሚኖሩ ይገልጣል። ንስር ሮጦ ይታከታል፣ ሄዶ ሄዶም ይደክማል። በእግዚአብሔር ህልውና ፊት ጽሞና ያላቸው አማንያን ግን ከዘመን ዘመን መንፈሳዊ ግለታቸውን እንደ ጠበቁ ይኖራሉ።

እንባቢ ሆይ! ጸሎታችን ጣዕም እንዲኖረው ከጾም፣ ከዕንባ፣ ከዜማ፣ ከምግባርና ከጽሞና ጋር መያያዝ አለበት።



# ምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ

# የጸሎት እንቅፋቶች

*«ጸሎት የቀኑ አደጋ ስላስፈራን፣ የሌሊቱ ዘራፊ ስላሳሰበን ዋስትና የምንጠይቅበት ሳይሆን የጸሎት ዋነኛ ዓላማው ናፍቆትን መወጣት ነው።»*

ዋላ የውኃ ምንጭን በጣም ትናፍቃለች። ከወራጁ ላይ ሳይሆን ከምንጩ ላይ ትሆናለች። ዋላ ከመውደድ አልፋ ስለምትናፍቅ ከውኃ ምንጭ አጠገብ አትታጣም። ብትፈለግ የምትገኘው ከምንጩ አጠገብ ነው። ይህን ስለሚያውቅ አንበሳ እንኳን የሚጠብቃት ከምንጩ አጠገብ ነው። ከእርካታዋ አጠገብ ያደባባታል። ዋላም ምንም እንኳ አንበሳው ከምንጩ አጠገብ እንደሚጠብቃት ብታውቅም ናፍቆቷ ግን ብርቱ በመሆኑ የአንበሳውን መኖር ያስረሳታል። ከምንጩም ትጠጣና ልትሄድ ብላ ተመልሳ እዚያው ትገኛለች። ከምንጩ ውጭ ሌላ ማራኪ ነገር አይታያትም።

ነቢዩ ዳዊት፡- *«ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ፥ አቤቱ፥ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች። ነፍሴ ወደ ሕያው አምላክ ተጠማች፤ መቼ እደርሳለሁ? የአምላክንስ ፊት መቼ አያለሁ?»* (መዝ. 41/42/፥1-2) ብሏል። የዋላ ናፍቆት ተራ ናፍቆት ሳይሆን ዋጋ የሚያስከፍል ናፍቆት ነው። ዋላ የአንበሳን መኖር እያወቀች ወደ ውኃው ምንጭ ትሄዳለች። ነቢዩም እንዲሁ ዋጋ በሚያስከፍል ናፍቆት ጌታውን ናፈቀ። ከጌታው ጋር የሚገናኝበት ያ ሰዓት እንደ ውኃው ምንጭ የሚያረካው ነበር። ነገር ግን እርካታው አጠገብ አንበሳ ይጠብቀዋል። «ለእኛ ጊዜ ስጠን እግዚአብሔር ከትዳርና ከልጅ በላይ ነው ወይ?» የሚሉ ፍቅር የሚመስሉ ድምፆች፣ «እንዴት እንደዚህ ትዘምራለህ? ክብርህን አትጠብቅም ወይ?» የሚሉ ክሶች ቢበዙበትም ዳዊት ግን ናፍቆቱን ደልሎ ማለፍ አልሆነለትም። አንድ ሰው፡- «እንደ እንደ ዳዊት ከዘመርን፣ እንደ ሜልኮል የሚያሽሟጥጡ አይጠፉም» ብሏል። አዎ አንበሳው ዋላን መጠጥ ቤት ስለማያገኛት እዚያ አይጠብቃትም። ዝሙት ቤት ስለማያገኛት እዚያ አይጠብቃትም። እርካታዋ ክርስቶስ ጋ ስለሚያገኛት ግን እዚያ ይጠብቃታል። በምንም ከመታማት በክርስቶስ መታማት እንዴት ክብር አለው!

አምልኮ በፈለግን ጊዜ ወይም ትርፍ ሰዓት ስላገኘን ብቻ የምናደርገው ሳይሆን፡-

1. ናፍቆትን
2. መዋጋትን ይጠይቃል።

እግዚአብሔር ሊናፍቀን ይገባል። እግዚአብሔር ካልናፈቀን ተወዳጅ ጸሎት ማቅረብ አይሆንልንም። የናፍቆታችን ኃይልም አንበሳውን እንድንነቀው ሊያደርግ ይገባዋል። ጸሎት ግዳጅን መወጫ አይደለም። የናፍቆት እርካታ ነው። አንድ ወጣት፡- «ጸሎት ጉዳይ እንጂ ግዳጅ አይደለም» ብሏል። ናፍቆት የሚናፈቀው እስካልተገኘ ዕረፍት የማይሰጥ፣ በመርሳትም ማለፍ የማይቻል ነው። ናፍቆት መጠማት ነው። ብርቱ በሆነ በሚያቃጥል ስሜት እግዚአብሔርን መፈለግ ነው። ናፍቆት ስለሚያስቸኩል ደቂቃው ዓመት፣ ሰዓቱም ምእት የሆነ ያህል ይረዝማል። ነቢዩ፡- *«ነፍሴ ወደ ሕያው አምላክ ተጠማች፤ መቼ እደርሳለሁ? የአምላክንስ ፊት መቼ አያለሁ?»* ያለው ይህ ስሜት ተሰምቶት ነው። እንዲህ ባለ ሁኔታ የማያመልክ ክርስቲያን ከጸሎት ምንጭ ሊረካ አይችልም። አለመርካቱ ብቻ ሳይሆን እንደዚህ የሚጠሙ ሰዎችን ሲያይ ስለማይገባው ይቃወማል።

ብዙ ሰዎች ሲነጋ «በሰላም ያሳደርከኝ በሰላም አውለኝ» ብለው ከቤት ይወጣሉ። ሲመሽ «በሰላም ያዋልከኝ በሰላም አሳድረኝ» ብለው ይተኛሉ። ጸሎት ለእነርሱ ወታደራዊ ሰላምታ ለአዛዥ እንደ ማቅረብ ነው። ያ ግን ግዴታና ደንብ ስለሆነ የሚደረግ ሥነ ሥርዓት እንጂ ናፍቆት አይደለም። ጸሎት ግን ናፍቆት ነው። የናፈቅነውን ሰው ስናገኘው ሁሉንም ነገር እንረሳለን። ሰዓታችንን ማየትና መቍነጥነጥ አቁመን እንረጋጋለን። አውርተን አንጠግብም። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ዝም ብለን እናየዋለን። ነፍሳችን በፍቅር ኃይል በከፍታዎች ላይ መብረር ትጀምራለች። ድልም ሰልፍ ይዞ ለእኛ ሊገብር የመጣ ይመስለናል። ከእግዚአብሔር ጋር በናፍቆት ስንገናኝም የሚሆነው ልክ እንደዚህ ነው። ጸሎት የቀኑ አደጋ ስላሰፈራን፣ የሌሊቱ ዘራፊ ስላሳሰበን ዋስትና የምንጠይቅበት ሳይሆን የጸሎት ዋነኛ ዓላማው ናፍቆትን መወጣት ነው።

ማንኛውንም ነገር እንደምናከናውነው ጸሎትንም በቀላሉ ማድረግ አንችልም። ጸሎት ውጊያ አለው። ምሳችንን ለመብላት ምንም ፈተና የለብንም። ለመጸለይ ግን ብዙ መሰናክሎች አሉ። አንበሳው ከእርካታችን አጠገብ ይጠብቀናል። እንዳንጸልይ በማድረግ እርካታችንን ይወስዳል። እርካታ ስናጣ በኃጢአት ኳስ እንደምንጫወት ከዚያም



የጎሊና ወቀሳ ሲያንገላታን መኖርን እንደምንጠላ በደንብ ያውቀዋል። አንበሳው የሚፈልገው ዋላን ማወክ ወይም ከውኃው ምንጭ አደናቅፎ ከእርሷ ጋር ለመጫወት ሳይሆን የሚፈልገው ሕይወቷን ለማጥፋት ነው። ሰይጣንም የሚዋጋው በረከታችንን ሳይሆን ሕይወታችንን ነው።

በጸሎት ላይ ያሉትን መሰናክሎች በሦስት ከፍለን ማየት እንችላለን።

1. ከጸሎት በፊት ያለ መሰናክል
2. በጸሎት ሰዓት ያለ መሰናክል
3. ከጸሎት በኋላ ያለ መሰናክል

## ከጸሎት በፊት ያለ መሰናክል

አለመጸለይ ረዳት እያለ መድከም፣ ሰጪ እያለ መደኸየት፣ ንጉሥ እያለ መጠቃት ነው። ሰዎች ከቀሙን ንብረት ይልቅ ባለመጸለይ የምናሰወስደው ጸጋ ይበዛል። አንድ ቄስ አንድ አገልጋይን «እባክዎ በጸሎት አስቡኝ» ይሏቸዋል። አገልጋዩም ደንግጠው «ምነው ቄሶቹ ተነሡብዎት ወይ?» ቢሏቸው «አይ እነርሱ የሚነሡት እኔ በጸሎት ስደክም ነው። ኧረ ሌላ ጉዳይ ነው» አሏቸው። ስንደክም የሚነሡ ብዙ ነገሮች አሉ። ሰይጣን እንዳንጸልይ በብዙ ነገሮች ይታገለናል። ለዚህ ውጊያውም ሥጋንና ዓለምን ይጠቀማል። ከጸሎት በፊት ያለ መሰናክል ምንድነው? ስንል፡-

### ለጸሎት ጊዜ አለ መስጠት

ለጸሎት የመደብነው ጊዜ ሌላ ጉዳይ ከገጠመን ልንተወው የምንችለው በተጠባባቂ ሰዓት ላይ ያለ ጊዜ ነው። ነገር ግን ከነፍስ የሚበልጥ ጉዳይ ከእግዚአብሔርም የሚበልጥ ወዳጅ የለምና ለእግዚአብሔር ጊዜ መስጠት ይገባናል። ዮናስ ሥራዬ እግዚአብሔርን ማምለክ ነው (ዮና. 1፥9) ያለው ልብ የሚነካ ነው። እግዚአብሔርን ማምለክ ትልቅ ሥራ ነው። ሥራ የውዴታ ግዴታ ነው። አምልኮም እንዲሁ የውዴታ ግዴታ የሆነ ልናከናውናቸው ከሚገቡ ተግባራት የመጀመሪያው ነው። አሥራት በኩራት እግዚአብሔር ከሰጠን ነገር ሁሉ እንጂ ከገንዘባችን ብቻ የምናወጣው አይደለም። ስለዚህ እግዚአብሔር ከሰጠን ጊዜ ላይ የጊዜ አሥራት ልናወጣ ይገባል። በአንድ ቀን (24 ሰዓት) ውስጥ እንኳን ከሁለት ሰዓት በላይ የጊዜ አሥራት አለብን።

ለእግዚአብሔር ጊዜ አለመመደብ አንዱ የጸሎት እንቅፋት ነው። በመደብነው ጊዜ ላይ ደግሞ በይሉኝታ ጊዜውን ማሳለፍም አንዱ ፈተና ነው። በዚያ ሰዓት ላይ የሚፈልጉን ሰዎች ይበዛሉ። እንግዶች በቤታችን ይመጣሉ። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ቀጠሮ አለኝ ብለን ወደ ጸሎት እልፍኛችን መግባት አሊያም እነርሱን መጋበዝ ይገባል። ሥራችንን የሚያከብሩልን ወዳጆቻችን የጸሎት ጊዜአችንንም ሊያከብሩ ይገባቸዋል። እኛ ያላከበርነውን ማንም አያከብረውምና በዚህ ጉዳይ ቆራጦች መሆን ይገባናል። እግዚአብሔር ከምንም ነገር በላይ ጊዜ እንድንሰጠው ይፈልጋል። ፍ

## ስንፍና

ስንፍና ሠርተን ስለ ደከመን የሚመጣ ሳይሆን የልብ ወይም የአስተሳሰብ ሽባነት ነው። በእግዚአብሔር ፊት ታካች ልብ የተጠላች ናት። ልባችን ሲደክም አካላችንም ይደክማል፤ ልባችን ሲበረታ አካላችንም ይበረታል። ለመጸለይ ከምንቸገርበት ነገር አንዱ ስንፍና ነው። በአገራችን የሚነገር ታሪክ አለ። አንድ ሰነፍ ልጅ እናቱ ትልከዋለች። የሚላክበት ቦታ ውሎ ገባ የሆነ ሩቅ ስለ ነበር አሰበውና ሳይሄድ ውሎ ምሽት ላይ ላይ ወደ ቤቱ መጣ። እናቲቱም የሄደ መስሏት «ደርሰህ መጣህ ወይ?» ብትለው «አልሄድኩም» አላት። «ለምን?» ብትለው «ሳሰበው ሳሰበው ደከመኝ» አላት ይባላል።

አንዳንድ ጊዜ ኑሮችን ሩጫ የበዛበት ይሆንና ጠዋት ተዋክበን እንወጣለን። የሮጥንበትን ሳይሆን የተሰጠንን እንደምንቀበል ስለማንረዳ ጸሎትን የሚተው፣ ትጋት የሚመስል መክነፍ ውስጥ እንገባለን። ምሽትም ለመጸለይ ስናስብ «ደክሞሃል ተኛ» የሚል ድምፅ ከውስጣችን እንሰማለን። የሚገርመው ስንተኛ እንቅልፍ አይወስደንም። ስንገላበጥ ስንገላበጥ የቴሌቪዥን ድምፅ ስንሰማ እንነቃለን። አምስት ደቂቃ ለመጸለይና መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ የደከመን ሰዎች የሕዝብ መዝሙር እስኪዘመር ቴሌቪዥኑ ላይ እናፈጣለን። «ተኛ የዋልክበትን ውሎ እንኳን እግዚአብሔር ሰውም ይረዳዋል» የሚለው ድምፅ የአሳቢነት ድምፅ በመሆኑ ከሥጋችን የመጣ እንጂ ከሰይጣን የመጣ ስለማይመስለን ብዙ ጊዜ እንሳሳታለን። አዎ ሰይጣን አሳቢ ነው። ላያስተኛን ተኙ ይለናል። ስንፍናን በመላው ሕይወታችን ልንዋጋው ይገባል። እኛ በተፈጥሮአችን ተቀምጠን ስንነሣ የምንታደስ ሆነን ስለ ተፈጠርን የትላንቱን ወይም የጠዋቱን ድካም አስታውሰን አሁን ለመጸለይ መድከም የለብንም። የኀሊና ነገር ደካሞች ያደርገናልና መንቃት ይገባናል።



## ኩርፊያ

ሰው ሰውን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርንም ያኮርፋል። ሰው ጸልዮ መልስ በማጣቱ፣ ጠላቶቹ እየበረቱ እርሱ ፍርድ በማጣቱ፣ የሚወደውን ነገር ለእግዚአብሔር አደራ ብሎ ያ ነገር በመጥፋቱና በሌላም ጉዳዮች እግዚአብሔርን ያኮርፋል። ስለዚህ «አልጸልይም፣ ጸልዬ ምን አገኘሁ» ይላል። የሰው ልጅ እግዚአብሔር እንደ ሰጠው የሚያውቀው በጣም ትንሹን ነው። ራሱ እግዚአብሔር እንደ ሰጠን የሚያውቀው ግን ብዙ ነገር አለ። የሰው ልጅ እንዳለፈው የሚያውቀው በጣም ትንሹን ነው። እግዚአብሔር ግን እንዳሳለፈን የሚያውቀው ብዙ መሰናክል አለ። «እግዚአብሔር ሆይ አንተ እንዳደረክልኝ በምታውቀው ልክ ተመስገን» ማለትም ይገባናል። ራሱን ብቻ የሚያዳምጠው ሰው ግን እግዚአብሔርን ያኮርፋል። ምሥጢሩ ቢገባው ግን ስለ ተከለከለው ነገር ያለማቋረጥ በዘመረ ነበር። አዎ ከጸሎት እንቅፋቶች አንዱ ኩርፊያ ነው።

## ጊዜ ማጣት

ያለንበት ዘመን ሰዎች የተወጠሩበትና ትንፋሻቸውን ለመዋጥ ጊዜ ያጡበት ዘመን ነው። ይህ ግን የሚመስል ነገር እንጂ እውነተኛ ነገር አይደለም። ሩጫው ብዙ፣ ውጤቱ ትንሽ የሆነበት ዘመን በመሆኑ ማስተዋል ያስፈልጋል። ብዙ ወገኖች የጊዜ ምስኪን ሆነዋል። የማይመጸወት ደሃ የጊዜ ችግረኛ ነው። ጊዜ ግን የእግዚአብሔር ስጦታ በመሆኑ ፍጹምና በቂ ነው። ስለዚህ ችግሩ ያለው ከጊዜው ሳይሆን ከአጠቃቀማችን ነው።

ኑሮዬ ይበቃኛልን ካልተለማመድን እንኳን ለነፍሳችን ለሳሳንለት ለሥጋችንም ምንም አናተርፍም። ያጠራቀምነውን የምንበላው እየመሰለን ዛሬን የሩጫ፣ ነገን የዕረፍት ጊዜ ነው እያልን እናቅዳለን። ነገር ግን ይህች ዓለም ማንን እንዳሳረፈች እኛን ታሳርፋለች? ዕረፍት ያለው ከጸሎት ምንጭ አጠገብ በመቀመጥ ነው። መማር መሥራት መልካም ቢሆንም ለፍርሃት ማስታገሻ ሁለት ትምህርት ብዙ ሥራ መጀመር ግን ድካም ብቻ ነው። እግዚአብሔር ያልተማሩትንም ያውም የተማሩትን አሽከር አድርጎ ያኖራቸዋል። መሥራት የማይችሉትንም ወዳጅ ሰጥቶ ያኖራቸዋል። ሩጫህን እግዚአብሔር እንዲቀድምበት ጸልይ እንጂ ብቻህን አትሩጥ። ለትዳርህ፣ ለልጆችህ፣ ከሁሉ በላይ ለእግዚአብሔር ጊዜ ይኑርህ!

ለዓለም የመደብነው ብዙ ጊዜ እርካታው ትንሽ ሲሆን ለጸሎትና ለቃሉ የመደብነው ጥቂት ደቂቃ ግን እርካታው ብዙ ነው:: ከጸሎት በፊት ያለው መሰናክል ለጸሎት ጊዜ አለመስጠት፣ ስንፍና፣ ኩርፊያ፣ ጊዜ ማጣት የሚጠቀሱ ናቸው::

## በጸሎት ሰዓት ያለ መሰናክል

### የአሳብ መበታተን

ወደ ገበያ አዳራሽ በምንሄድበት ጊዜ የምንፈልጋቸውን ዕቃዎች መዝግበን ከሄድን በቀላሉ አንሥተን እንወጣለን:: ዝርዝሩን ሳንይዝ ከሄድን ግን የዓይን አዋጅ ሆኖብን አንዱን ሳንይዝ እንደ ተንቀዋለልን ጊዜው ይሄዳል:: እንዲሁም ወደ ጸሎት ከመግባታችን በፊት ስለ ምን እንደምናመሰግን፣ ስለ ምን እንደምንለምን፣ ስለ ምን ንስሐ እንደምንገባ፣ ስለ እነማን እንደምንማልድ ርእስ መያዝና መጻፍ ይኖርብናል:: ይህን ሳናዘጋጅ ጸሎት ብንጀምር የምንይዘው የምንጨብጠውን አጥተን አሳባችን ይሰራጭብናል::

የአሳብ መበታተንን የሚያመጣው ሌላው ነገር ፀጥታ ማጣት ነው:: ወደ ጸሎት በምንገባበት ጊዜ የአካባቢው ፀጥታ አስተማማኝ ቢሆን መልካም ነው:: ስልኮቻችንን ማጥፋት ሌላው ቀርቶ ኃይል ያላቸውን ዝማሬዎች ትቶ መንፈስን የሚገዙ የንስሐ ብለን የምንጠራቸውን የጽሞና ዝማሬዎችን መጠቀም መልካም ነው:: በጸሎት ሕይወት እያደግን ስንመጣ ግን በጫጫታ ውስጥም መጸለይ እንችላለን::

አጼ ቴዎድሮስ ሰዎችን ሰብስበው «አቡነ ዘበሰማያትን አፍ ከልብ ሆኖ የሚጸልይ ባገኝ በቅሎዬን እሸልመዋለሁ» አሉ:: አንድ ሰውም «እኔ እጸልያለሁ» አለ:: ሲፈጽምም «እውነቱን ንገረኝ አፍ ከልብ ሆነህ ጸልየሃል?» ቢሉት «ጃንሆይ በመካከሉ ላይ በቅሎዋን የሚሸልሙኝ ብቻዋን ነው ወይስ ከነኮርቻዋ ነው? ብዬ አስቤአለሁ» አላቸው:: እርሳቸውም እውነቱን ተናግረሃል ብለው በቅሎዋን ክነኮርቻዋ ሸለሙት ይባላል:: በአገራችን ሊቅነቱ መንፈሳዊነት፣ ጸሎቱ ተመስጦ የለውም:: ለምን? ስንል ልባችንን ለቅዱሱ መንፈስ የማንሰጥ ጠንካሮች ስለሆንን ነው::

### ከሳሽነት

በጸሎት ላይ ስንሆን ካሉብን እንቅፋቶች አንዱ እየጸለይን የማይጸልዩትን ሰዎች ውስጣችን ይከስሳል:: ይህን ክስ እያመነው



ስንመጣ ውስጣችን እየታበየ ይመጣል:: ይህ ደግሞ የጸሎትን ሕይወት ክፉኛ ይጎዳል:: ጾምና ጸሎትን የሚያበላሸው ነገር የሌላውን አለመጾምና አለመጸለይ ሲያሳይ ነው:: እማሆይ ሌሊት ቆመው አቁጣሮ ያደርሳሉ:: አንድ ተማሪ ተኝቶ ያኮርፋል:: እማሆይ በዚህ ጊዜ ይኸዋ ጌታዬ እኔ ጻድቂቱ ቁሜ እጸልያለሁ:: ይህ ተማሪ ተጋድሞ እንቅልፉን ይልጣል አሉ ይባላል:: ጸሎት ኩራትን ከወለደ የመንፈስ ሥራ መሆኑ ቀርቶ የሥጋ ሥራ ሆኗል ማለት ነው::

በሉቃስ 18. ላይ የምናገኛቸው ሁለት ጸሎት አቅራቢዎች የጸሎትን መስመር ቢጠቀሙም አንዱ ተጠቅሞ አንዱ ከስሮ ተመልሰዋል:: ፈሪሳዊው ጽድቁን አወራ፣ ቀራጩ ኃጢአቱን ተናዘዘ:: በእግዚአብሔር ፊት ጽድቅን ከማውራት ኃጢአትን መናዘዝ ጥቅም እንዳለው ይህ ታሪክ ያስገነዝበናል::

### ግብዝነት

ግብዝ ማለት አስመሳይ ማለት ነው:: ግብዝ በመድረክ ላይ የሚተውን ተዋናይ ማለት ነው:: የመድረክ ተዋናይ ራሱ እስኪታለል ገፀ ባሕርዩን ይወርሳል:: በጸሎት ላይም ብዙ ግብዞች አሉ:: ዓላማቸው ጸሎተኛ በመባል የመበለቶችን ቤት መዝረፍ ነው:: በጌታችን ዘመን እነዚህ ሰዎች ነበሩ:: ጌታም:- *«እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን በጸሎት ርዝመት እያመካኛችሁ የመበለቶችን ቤት ስለምትበሉ፥ ወዮላችሁ፤ ስለዚህ የባሰ ፍርድ ትቀበላላችሁ»* (ማቴ. 23፥14) ብሏቸዋል:: ለእኛም:- *«ስትጸልዩም እንደ ግብዞች አትሁኑ፤ ለሰው ይታዩ ዘንድ በምኵራብና በመንገድ ማዕዘን ቆመው መጸለይን ይወዳሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል:: አንተ ግን ስትጸልይ፥ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ያስረክብሃል»* (ማቴ. 6፥5-6) ብሎናል::

ጸሎት የሥጋና የነፍስ በረከትን ከእግዚአብሔር የምንቀበልበት እንጂ ምድራዊ ደሞዝን ክሰዎች በመቀበል ዋጋውን የምናሳንስበት አይደለም:: ሰው ቢሰጥ ፍላጎትን እንጂ በረክትን (ደስታን) መስጠት አይችልም:: በጸሎት የምንቀበለው ግን በረከትን ነው:: ግብዞች እያኵተመተሙ መጸለይ፣ አውራውን እንደ ተከተለ ንብ ንን ማለት ይወዳሉ:: በዓውደ ምሕረት ላይ ቆመው ያነበንባሉ:: በአትርሱኝ ገንዘብ ጅምር ቤታቸውን ይጨርሳሉ:: የተበላሸ መኪናቸውን ያሠራሉ:: የጸሎት መንፈስ የላቸውም:: እግዚአብሔርም አይታያቸውም:: የሰው

ቦርሳ እስኪከፈት ኮስተር ብለው ይጸልያሉ:: ይህን ሥርዓት አሳከበራችሁም ብለው በፈጠራ ትምህርት ይገስጻሉ:: ደጋግመው እንዲመጡላቸው «በቤትሽ አንድ ችግር ይታየኛል» ይላሉ:: በቤቱ አንድ ችግር የሌለው ማን አለና? ራሱን ግብዝ ጸሎተኛ ያደረገው ችግር ነው:: ችግር ይታየኛል፣ ጉዳያችሁ አይሳካም ዓይነ ጥላ አለባችሁ፣ ምቀኛ ጎረቤት. . . እያለ ያምታታል:: ደርግ ከመጣ የተወረሰበት ባለቤትና የወረሰው ሰው ለአንድ አዳር ተስማምተው አያውቁም:: እነዚህን ሰዎች እየነካኩ በግድ አዋቂና የበቁ ይሆናሉ:: ሕዝባችንም ድራማ ስለሚወድ፣እየገደሉትም ይወዳቸዋል:: የአሪት ፈሪሳዊ ብቻ ሳይሆን ስንት ክርስቲያን ፈሪሳዊ አይተናል::

አንድ መነኩሴ እንዲህ ብለው ሲናገሩ ሰምቻለሁ:- «ሠርቶ መብላት ሲያቅተው መነንኩ ይላል:: ሆድ አይመንን ሲርበው ይመጣል:: የበላባትን ከተማ ወዮልሽ ባቢሎን ይላታል:: ጆንያው እህል እስኪሞላ ነው:: ሲያልቅ ተመልሶ ይመጣል::»

በእርግጥ ግብዞቹ በየስፍራው አሉ:: በየአብያተ ክርስቲያናቱም ሞልተዋል::: ያልታያቸውን ይታየኛል የሚሉ ብዙ ሐሳውያን በዛሬው ዘመን ፈልተዋል:: ልዩነቱ ግእዝና እንግሊዝኛ የሚናገር ሌባ ካልሆነ ሐሰተኞች በመልክአ ምድር ተወስነው አልተቀመጡም:: ካልተማሩትም እናት አባቶቻችን ላይ ይህን እናያለን:: ሲቃውንቱ በስውር ስለሚጸልዩና የጸሎት ድራማ ስለማይሠሩ ሕዝቡ ቢጠላቸውም ግብዝነት ግን ያለ መማርና የመንፈሳዊ ዋጋን ምድራዊ ለማድረግ ከሚፈልግ ስንኩል አስተሳሰብ የተወለደ ነው::

## አዚም

አጋንንት በጸሎት ሰዓት ብርቱ ማዛጋትን፣ እንቅልፍን፣ ድንዛዜን በመዝራት ጸሎታችንን ይዋጋሉ:: ይህን መቀበል አይገባንም:: በማይሰበረው የሃይማኖት በትር በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መገሰጽ ይገባናል:: በዘመናት ሁሉ የቅዱሳን የድል ምሥጢር የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው (የሐዋ. 16፥18):: ዓለሙ በክፉ ስለ ተያዘ እኛም የምንኖረው በፈንጂ ወረዳ በተመሰለው ዓለም መካከል ስለሆነ ውጊያ አለብን:: ወታደር ዘወትር እንደሚዋጋ ሆኖ ታጥቆ እንደሚወጣ ክርስቲያንም ታጥቆ መዋጋት ይኖርበታል:: የጸሎታችን አንዱ ክፍልም የርኩሳን መናፍስትን እንቅስቃሴ የሚዋጋ መሆን አለበት::



## የሚበቃንን አለመለመን

አንድ ብር ችግሮን የዓለምን የመጀመሪያ ባለጠጋ የሆነውን ሰውዬ ብናገኘው የቸገረንን ያንን አንድ ብር ብቻ አንጠይቀውም:: ዳግመኛ ሳላገኘው እችላለሁ ብለን ወይም ከእርሱ አንድ ብር ከምቀበል በችግር ብሞት ይሻለኛል ብለን የምንጠይቀው ጫን ያለ ገንዘብ ነው:: የሚያስፈልገን ከተሟላ ለአሁን ይበቃናል የሚል መርህ በውስጣችን የለም:: እግዚአብሔርንም የቸገረንን ነገር ብቻ መጠየቅ አይሆንልንም:: አንድ ጊዜ ተቀብለን ዳግመኛ ሳለመጠየቅ ደህና ነገር የምንለውን እንለምናለን:: ጸሎት ግን የማያቋርጥ ግንኙነት በመሆኑ የሚያስፈልገንን እየጠየቅን ቤተሰባዊውን ኑሮ ከእግዚአብሔር ጋር እንቀጥላለን:: አንዲት ሕፃን ልጅ ጓደኛዋን «ጸሎት የሚያልቀው መቼ ነው?» ብላ ስትጠይቃት ጓደኛዋ ሕፃንም:- «ቁርስ የሚያልቀው መቼ ነው?» በማለት ጥያቄዋን በጥያቄ መልሳለች::

# ከጸሎት በኋላ ያለ መሰናክል

## ተስፋ መቍረጥ

ከጸሎት በኋላ ካሉ እንቅፋቶች አንዱና ዋናው ተስፋ መቍረጥ ነው:: የዝሆን አዳኞች ዝሆኑ የሚደገፍበትን ግንድ ይገዘግዛሉ:: ዝሆኑም ሲደገፈው ከዛፉ ጋር አብሮ ይወድቃል:: አዳኞቹም በቀላሉ ይገድሉታል:: የሰውም ድጋፍ ተስፋ ነው:: ተስፋው የተገዘገዘን ሰው መጣል ለሰይጣን በጣም ቀላል ነው:: ሰይጣን የሚዋጋን እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅርና የሰጠንን ተስፋ እንድንጠራጠር በማድረግ ነው:: እግዚአብሔር እንደሚወደውና ተስፋው እንደሚፈጸም የተጠራጠረ ምእመን ሳይነካ ይወድቃል:: በጸሎታችን ላይም መልሱ ሲዘገይ ሰይጣን ተስፋ በማስቆረጥ፣ አማራጭ መንገዶችን እንድንጠቀም በመገፋፋት ይዋጋናል:: አንድ አባት «ሰይጣን እግዚአብሔር ከለከለህ እያለ አሳስቀምጥ አለኝ:: እኔም እርሱ ከለከለኝ አንተ እስቲ አዝነህ ስጠኝ ስለው ከእኔ ራቀ» ብሰዋል::

እግዚአብሔር የጸሎታችንን መልስ ሲሰጠን ሲመጣ ከጸሎት ስፍራችን ላይ እንዳንገኝ ሰይጣን ይዋጋናል::

## <u>መከራ ማብዛት</u>

በመጸለያቸው እነ ዳንኤል በአንበሳ ጉድጓድ ውስጥ እንደ ተጣሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል:: በርግጥ የእግዚአብሔር ሰው መከሰስ ያለበት ስለ መልካም ሥራው ሲሆን ይገባዋል (1ጴጥ. 4፥15):: በአሕዛብ መካከል የሚኖሩ ክርስቲያኖች፣ አንዱ አማኒ አንዱ ከሀዲ በሆኑ ባለ ትዳሮች መካከል መጸለይ መከራ ያመጣል:: ሰይጣን ኃይልንና ፍቅርን በመጠቀም ከእግዚአብሔር እንድንርቅ ይዋጋናል:: ስለዚህ ክርስቲያን ብልህ መሆን አለበት:: ማንኛውም የአካል ክፍል ተቆርጦ መኖር ይቻላል:: ከአንገት በላይ ተቆርጦ ግን መኖር አይቻልምና ክርስቲያን ሆይ ራስህን (ክርስቶስን) እንዳታስነካ ተጠንቀቅ! ወዳጅ ቢሄድ ወዳጅ ይተካል:: ኃይለኛም በሚበልጥ ኃይለኛ ይሸነፋል:: ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ለዘላለም ይኖራል::

## <u>እግዚአብሔርን ተባባሪ ማድረግ</u>

*«የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ»* (ዘፀ. 20፥7) የሚለው ቃል በሐሰተኛ መሐላ እርሱን የስህተታችን ተባባሪ እንዳናደርግ የሚያስጠነቅቅ ነው:: ብዙ ሰዎች ስህተትን ለምነው በሥጋ መንገድ ሲሆንላቸው እግዚአብሔር አደረገልኝ ብለው ምስጋና ያስነግራሉ:: እግዚአብሔር ግን በጽድቅ ምስክርነት እንጂ በዓመፃ ምስክርነት አይከብርም:: ለምሳሌ:- አንዲት ሴት እስላም ባል አግብታ «ባሌን የሰጠኝ እግዚአብሔር ነው» እያለች ስትመሰክር ሰምተናል:: መጽሐፍ ግን *«ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ»* (1ቆሮ. 6፥14) ይላል:: ባሏን የራሷ ከማድረጓ በፊት ባሏን የክርስቶስ ማድረግ ነበረባት:: የእኛን እናጣዋለን:: እግዚአብሔር ጋ ያለውን ግን አናጣውም:: የጸሎት ፍሬ ያልሆኑ ነገሮችን ፍሬ አድርጎ ማውራት ተገቢ አይደለም:: ዳኛን አታለው በነጻ የሚወጡ ሰዎች እግዚአብሔር አወጣን ቢሉ እግዚአብሔርን የስህተታቸው ተባባሪ ማድረጋቸው ነው:: ስህተትን ብንጸልይም ልክ አናደርገውም:: እግዚአብሔርም ከዓመፃ ጋር አይተባበርም::

## <u>ማነጻጸር</u>

እየጸለዩ ፈተና የሚበዛባቸው ሰዎች ድሮ በማልጸልይበት ዘመን ሰላም ነበርኩኝ መጸለይ ከጀመርኩ ግን ውጊያ በዛብኝ ይላሉ:: በምንጸልይበት ዘመን ውስጣችን ሰላም ሲኖረው አካባቢው ግን ይናጣል:: በማንጸልይበት ዘመን ግን አካባቢው ሰላም ቢመስልም ውስጣችን ግን የታወከ ነው:: በምንጸልይበት ዘመን ከእግዚአብሔር



ጋር ሰላም አለን ስለዚህ ከዲያብሎስ ጋር ውጊያ አለብን:: እርሱ ደግሞ ሥጋችንን እንጂ ነፍሳችንን መጉዳት አይችልም:: በማንጸልይበት ዘመን ግን ከእግዚአብሔር ጋር ጦርነት ከዲያብሎስ ጋር ሰላም ነበርን:: ስለዚህ ሥጋችን እንጻራዊ ሰላም ሲኖረው ነፍሳችን ግን ፍርድን ትጠባበቅ ነበር:: የቱ ይሻላል? ለደቡብ አፍሪካ ሕዝብ ከአፓርታይድ ዘመን ሰላምና ከዛሬው ውጣ - ውረድ የቱ ይሻላል? ነጻነት በቁሳቁስ አይለካም::

ያለ መጸለይ ዘመን ቢሻልማ ወደ መጸለይ ባልመጣን ነበር:: ስለምንረሳ ነው:: ሰይጣን ጸሎታችንን ለማደናቀፍ ያለ የሌለ ኃይሉን በመጠቀም ይዋጋናል:: ነገር ግን የእርሱ ትጥቅ አላቂ ነውና ተግተን መዋጋት ይገባናል እንጂ መዘናጋት አይገባንም:: በጸሎት አጋንንትን መውጋት ብቻ ሳይሆን አጋንንትም እንዳንጸልይ ይዋጉናል::

አንድ አባት:- «ምሳችንን የምንበላው እግዚአብሔር እንዳይቀየመን ብለን ነው?» ብለው ከጠየቁ በኋላ «አይደለም ለመኖር ግድ ስለሆነ ነው:: እንዲሁም የምናመልከውና በጎ የምንሠራው ለራሳችን ብለን ነው» ብለዋል::

ጸሎት እንቅፋቶች አሉት:: እነዚህ እንቅፋቶችም ከጸሎት በፊት በጸሎት ጊዜና ከጸሎት በኋላ የሚነሡ ናቸው:: ውጊያዎች ቢያስመርሩንም ለጸሎት ግን ያተጋሉ:: እግዚአብሔር በዘመናት ሁሉ ያለ መውጊያ አልተመለከም:: ሰዎች ካልተወጉ አያመልኩም:: ውጊያዎች የውስጣችንንና የውጩን ነገር አጥርተን እንድናይ ወደ እግዚአብሔርም እንድንጮህ ያደርጉናል:: ከዓመታት በፊት ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመግባት ደጃፉ ላይ ሰደርስ አንድ ሰው የለማኟን ልጅ እየሳመ «ልጅሽ ቆንጆ ነበረች:: ምን ዋጋ አለው አፍንጫ ነሣት እንጂ» ቢላት ለማኟም:- «አይ ጌታዬ ጎዶሎ ከሌለማ እግዚአብሔር ይረሳል» ስትለው ሰምቻለሁ::

# ማጠቃለያ

ጸልዩ የሚሉት ቃላት በተሰያየ ስፍራ ተጠቅሰዋል። መጸለይ ትእዛዝ ነው። መጸሰይ ሰተሰያዩ ሰዎች የተሰጠ ጸጋ አይደለም። ክርስቲያን ሁሉ ሲያከናውነው የሚገባ ነው። መጸለይ አምልኮ ነው። ስሰዚህ አምላክ ወደ ሆነውና የሥጋ ለባሽን ጸሎት ወደ ሚሰማው (መዝ. 64፥1-2)፣ በቦታዎች ወደ ማይወሰነው አምላክ (ዮሐ. 4፥23-24) መጸሰይ ይገባናል። እግዚአብሔር ሲያደርግልን የሚፈልጋቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ነገር ግን እስክንጸልይ ያዘገያቸዋል። ምክንያቱም የእግዚአብሔር የሆነውን ለማግኘት መጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት ያስፈልጋል። ዳግመኛም እግዚአብሔር አደረገልን ብሰን ሰማመስገን አስቀድመን የጸሎትን ደጅ ጥናት ማድረግ አሰብን።

ጸልዩ የሚሰው ቃል ያስደንቃል። ፍጡር በባሕርይው ልመና አይወድም። ይሰሰቻል። እግዚአብሔር ብቻ ስንሰምነው ፍቅራችንን ያረጋግጣል። ከጸሎት ሌላ በትእዛዝ አንቀጽ የተቀመጠው ሌላው ቃል ‹‹ደስ ይበላችሁ›› (ፊልጵ.4፥4) የሚሰው ቃል ነው። ደስታ ትእዛዝ ነው። መደሰት በማን? ስንል ‹‹በጌታ ደስ ይበላችሁ›› ይላል። ሰመደሰት ግን በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት ያስፈልጋል።

ነቢዩ ዳዊት ‹‹ለኢየሩሳሌም ሰላምን ለምኑ›› (መዝ. 121÷6) ብሏል። ኢየሩሳሌም ማሰት የሰላም ከተማ ማሰት ነው። ኢየሩሳሌም ግን ከተመሠረተችበት ቀን ጀምሮ እንደ ስሟ ሆና አታውቅም። የውጊያ ከተማ ናት። ዛሬም የኢየሩሳሌም ጎዳናዎች በስጋት የሚረገጡ ናቸው። እስራኤል መሲሑ የሚወጣበት ዘር በመሆኑ ሰይጣን ገና ከጥንት ይህን ዘር ሰማጥፋት ወጥቷል። በብዙ ትግልና ውጊያ ውስጥ ይህ ዘር ቢያልፍም መሲሑ መጥቶ ተወሰደ። ዓሰምንም አዳነ። በታረደው በግ ዓሰም ሲጠግብና የነፍስ ሰላም ሲያገኝ ኢየሩሳሌም ግን ገፍታው ይኸው ሰላምን ተርባለች።

መሲሑ የዓሰም ፍስሐ ቢሆንም ኢየሩሳሌም ግን ዛሬም በሰይጣን በትር ትደበደባለች። ከመሲሑ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት በፊትና መሲሑ ክርስቶስ ከመጣ በኋላም መከራ እየተቀበለች ያለችው ከሰይጣን በቀል የተነሣ ነው። ኢየሩሳሌም መሲሑን ዛሬም ሳትቀበል



የሰይጣን በትር የሚያርፍባት ከሆነ መከራ የምትቀበሰው ሰክርስቲያኖች ነው። ስሰዚህ ክርስቲያኖች ሰኢየሩሳሌም ዕዳ አሰባቸው ማሰት ነው። ዕዳቸውንም በጸሎት መክፈል ይኖርባቸዋል። ሰዚህ ነው ‹‹ለኢየሩሳሌም ሰላምን ለምኑ›› የተባሰው። ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ራሱ ክርስቶስ፣ ድንግል ማርያም የተገኙት ከእስራኤል ነው።

እግዚአብሔር ተስፋ የሰጠው ሕዝብ ገና አላረፈም። በዙሪያው ያሉት አሕዛብ የአንድ ቀን ምሳ ቢሆንላቸው ይመኛሉ። መሣሪያቸውን ሠርተው ኢየሩሳሌም ይደርሳል ብሰው የርቀት መስኪያ አድርገዋታል። ይህ ተስፋ የተቀበሰ ሕዝብ ሰላም ካላገኘ ዓሰም ሰላም አያገኝም። የኢየሩሳሌም ሁከት የዓሰም ሁከት ነው ። የኢየሩሳሌም ሰላም የዓሰም ሰላም ነው። ሰዚህ ነው ‹‹ለኢየሩሳሌም ሰላምን ለምኑ›› የተባሰው። በጸሎት ውስጥ የዓሰም ሰላም ተቀምጧል። ሰላም በውይይት፣ በድርድር፣ በመፈክር፣ በውል አይመጣም። ሰላም ክርስቶስ ነው። የክርስቶስን ሰላም በእርሱ በማመንና ተግቶ በመጸሰይ መሰማመድ ያስፈልጋል። ይህን ውብ ሰላም ሳናይ እንዳንሞት እግዚአብሔር ይርዳን!

ጌታችንም ‹‹ነገር ግን ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ›› (ማቴ. 24÷20) አለ። መንገድ ባሰበት በበጋው ወራት መሰደድ መልካም ነው። ውሃ በሞላበት ክረምት መሸሽ ግን ከባድ ነው። ሰንበትም የዕረፍት ቀን ነው። እስራኤል በሰንበት ቀን የትም ስሰማይሄዱ ብዙ ጊዜ ጠላቶቻቸው ጥቃት አድርሰውባቸዋል። መንገድ በሌሰበትና በማይሸሽበት ቀን መሰደድ ከባድ ነው። ከመከራም መከራ ይመረጣል። ወዳጅ ያሰበት መከራ፣ መንገድ ያሰበት ስደት ምቹ ነው። ስደቱ የማይቀር ቢሆን እንኳ በሚመች መንገድና ቀን እንዲሆን ጸልዩ ተባሰ። ጸሎት ወደ ፈተና እንዳንገባ ይረዳል። ወደ ፈተናም ስንገባ የመውጫውን መንገድ ያሳያል። በጸሎት የማይቻሉ ነገሮች ሲቻሉ፣ ተራራ ሲናድ እናያሰን። በግል ሕይወታችንም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ገና በጸሎት ኃይል አልተጠቀምንም ማሰት ነው። በጸሎት ኢየሩሳሌምን መንካት፣ በዝግ ቀኖች መንገድ ማስከፈት ይቻላል።

ጌታችን ፡- *‹‹መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ለመከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት››* (ሉቃ. 10÷2) አለ፡፡ መከር የደረሰ እህል ነው፡፡ ስለዚህ የሚሰበስብ ሠራተኛ ያስፈልገዋል፡፡ ሰብሳቢ የሚፈልግ ብዙ የተበተነና ያዘነ ሕዝብ በዙሪያችን አለ፡፡ ሰዚህ መፍትሔው የሚሰበስቡ አገልጋዮችን እንዲሰጠን መለመን ነው፡፡ *ሥራው* የእግዚአብሔር ነው፡፡ ታዲያ ሠራተኛ ለምን አይልክልንም? እስከንጸልይ እየጠበቀ ነው፡፡ ሰብሳቢ አባቶችን እንዲሰጠን መጸሰይ ያስፈልጋል፡፡ በጸሎት የሚያገለግሉንን አገልጋዮች እኛም ማገልገል እንችላለን፡፡ ጸልየን ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንሄድ የሚያቆስለንን ሳይሆን የሚፈውሰንን ቃል ከአገልጋዮች እንሰማለን፡፡

ዳግመኛም የተወደደው ጌታችን፡- *‹‹ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ››* (ማቴ. 26÷41) አለ፡፡ ሐዋርያቱ ከፊታቸው የገጠማቸው ፈተና ምንድነው? ጌታን የመካድ ትልቅ ፈተና ነው፡፡ ስለዚህ ጸልዩ ተባሉ፡፡ ጸሎታቸው ‹‹እስከ መጨረሻው እንድከተልህ እርዳኝ፡፡ ከራሴ አድነኝ›› የሚል ነው፡፡ ከቤት ስንወጣ ልብሱን እያያችሁ ብለን ለዘበኞች አደራ እንላለን፡፡ ልጄን እያያችሁ ብለን በጣም ለምንወዳቸው አደራ እንላለን፡፡ ራሴን አደራ ብለን ግን ለየትኛው ወዳጅ እንሰጠዋለን? እኔን አደራ የምንለው ለሞተልን ጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ጸልዩ!

አነቃቅቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይሁን፡፡ አሜን፡፡